# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት
# ወደ ሮሜ ሰዎች

## መግቢያ

### ጸሐፊው

የዚህ መልእክት ጸሐፊ ሐዋርያው ጳውሎስ ነው (1፥1 ይመ)። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን፣ ይህን መልእክት የጻፈው ጳውሎስ በመሆኑ ላይ አንዳችም የተቃውሞ ድምጽ አላነሳችም። መልእክቱ ከጳውሎስ ሕይወት ጋር የሚዛመዱ ብዙ የታሪክ ማጣቀሻዎች ይገኙበታል። የአስተምህሮቱም ይዘት ሐዋርያው ከጻፋቸው ሌሎች መልእክቶች ጋር ሲነጻጸር፣ የጳውሎስ አመለካከት ጐልቶ ይታይበታል።

### መልእክቱ የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

ይህ መልእክት በ57 ዓ.ም. መጀመሪያ ሳይጻፍ አልቀረም። ጳውሎስ አገልግሎት ይሰጥባቸው ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት የተሰበሰበውን ገንዘብ በችግር ላይ ለነበሩት የኢየሩሳሌም ምእመናን ያደርስ ዘንድ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ለመመለስ በተዘጋጀበት በሦስተኛው የወንጌል ጕዞው ላይ የነበረ ይመስላል (15፥25-27 ይመ)። በ15፥26 ላይ ጳውሎስ በመቄዶንያና በአካይያ ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የርዳታውን ገንዘብ ተቀብሎ እንደ ነበረ ተጠቅሶአል፤ ስለዚህ በዚያን ጊዜ በቆሮንቶስ ወይም ከዚያ በፊት እዚያው ይኖር ነበር። በሦስተኛው የወንጌል ጕዞው፣ አንደኛ ቆሮንቶስን በጻፈበት ወቅት ጳውሎስ በቆሮንቶስ አልነበረም (ከ1ቆሮ 16፥1-4 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ሁለተኛውንም መልእክቱን ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈበት ጊዜ (2ቆሮ 8-9)፣ የገንዘብ መዋጮው ጕዳይ ገና ዕልባት አላገኘም ነበር፤ ስለዚህ የሮሜ መልእክት የተጻፈው ከአንደኛና ከሁለተኛ ቆሮንቶስ መልእክት (ከ55 ዓ.ም. ገደማ) በኋላ ሳይሆን አልቀረም።

የክንክራኦሷን ፌበንንና (6፥1) የጳውሎስን አስተናጋጅ ጋይዮስን (16፥23) የሚጠቅስ በመሆኑ፣ ይህ መልእክት የተጻፈው በቆሮንቶስ ወይም ከቆሮንቶስ ዐሥር ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው በክንክራኦስ ይመስላል። ጋይዮስ እንዲሁም ኤርስጦስ (16፥23፤ 2ጢሞ4፥20)፣ የቆሮንቶስ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

### የመልእክቱ ተደራስያን

የዚህ መልእክት የመጀመሪያ ተደራስያን፣ ብዙ አሕዛብ ይገኙባቸው የነበሩ የሮም ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ናቸው (1፥7)፤ የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባላት የነበሩ አይሁድ ግን ዝቅተኛ ቍጥር ነበራቸው (4፥1፤ ም 9-11 ይመ፤ በተጨማሪም የ1፥13 ማብ ይመ)። ጳውሎስ ምናልባት በመጀመሪያ ለሮም ቤተ ክርስቲያን የላከው ጠቅላላ መልእክቱን ነበር፤ ከዚያም በኋላ በየቦታው ለማሠራጨት ሲባል እርሱ ወይም ሌላ ሰው መልእክቱን አሳጥሮ (ም 1-14 ወይም 1-15) ሳይጠቀምበት አልቀረም፤ የ2 ጴጥ 3፥15 ማብ ይመ።

### የመልእክቱ መሪ ሐሳብ

በሮም መልእክት የጳውሎስ ዋነኛ መሪ ሐሳብ፣ ለሰው ዘር ሁሉ ለአይሁድም ሆነ ለአሕዛብ (1:16-17) እኩል የተሰጠው የእግዚአብሔር ድነትና ጽድቅ፣ ማለትም መሠረታዊው ወንጌል ነው። አንዳንድ ሰዎች የመልእክቱ መሪ ሐሳብ "በእምነት መጽደቅ" እንደ ሆነ ቢያመለክቱም፣ ከዚህ ሰፋ ያለ ሐሳቡን ይበልጥ ይገልጻል። "ከእግዚአብሔር የሆነ ጽድቅ" (1፥17) በሚለው ውስጥ በእምነት መጽደቅ የሚለው ሐሳብ ተካቶበታል፤ እንደ በደል፣ ቅድስና፣ ዋስትናና የመሳሰሉትን ተዛማጅ ሐሳቦችም በውስጡ ዐቅፎአል።

ጳውሎስ መልእክቱን የሚጀምረው የሰውን ልጅ ሁሉ መንፈሳዊ ሁኔታ በመቃኘት ነው። አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ኀጢአተኞች መሆናቸውንና ድነት እንደሚያስፈልጋቸው ተረድቶአል። ያም ድነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስና በመስቀል ላይ በፈጸመው የቤዛነት ሥራ አማካይነት ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው። ድነት የሚገኘው በእምነት ሲሆን፣ የአብርሃም ምሳሌነት እንደሚያሳየው፣ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ሁልጊዜ ግንኙነት የሚያደርገው በዚሁ መንገድ በእምነት አማካይነት ነው። ድነት የመጀመሪያ የክርስቲያን ሕይወት ተሞክሮ እንደ መሆኑ መጠን፣ አማኝ ከኀጢአት፣ ከሕግና ከሞት እንዴት ነጻ እንደሚወጣና ይህም ነጻነት ለአማኝ የሚሰጠው፣ አማኙ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር በሚኖረው ኅብረትና መንፈስ ቅዱስ በልቡ አድሮ በሚሰጠው ኀይል እንደሆነ ጳውሎስ ደረጃ በደረጃ ያብራራል። ምንም እንኳ በዚህ ዘመን ባለማመን ሁኔታ ውስጥ ብትገኝም፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ የማዳን ዕቅድ ውስጥ እስራኤል ቦታ እንዳላትም ያመለክታል። አሁን አሕዛብ ይድኑ ዘንድ ስፍራ በመልቀቋ፣ ያመኑት ጥቂቶቹ ቢሆኑም፣ "እስራኤል ሁሉ የሚድኑበት" (11፥26) ጊዜ ይመጣል ይላሉ። መልእክቱ የሚደመድመው አማኞች ሁሉ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በዓለም ውስጥ በበጎ ሥነ ምግባር እምነታቸውን ተግባራዊ ያደርጉት ዘንድ በማሳሰብ ነው። ከጳውሎስ መልእክቶች መካከል የወንጌልን ይዘትና ለአሁኑም ሆነ ለመጪው ዘመን የሚኖረውን ትርጕም፣ እንደ ሮሜ መልእክት በጥልቀት የሚያብራራ የለም።

**የመልእክቱ ዐላማ**

ጳውሎስ ይህን መልእክት እንዲጽፍ ያደረጉት ዐላማዎች የተለያዩ ናቸው:-

1. ወደ ፊት በሮም ለሚያደርገው ጒብኝትና ወደ እስጳንያ ለወንጌል ተልእኮ ለሚያደርገው ጒዞ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት (1፥10-15፤ 15፥22-29)፣
2. ከዚህ ቀደም ገና ሐዋርያዊ ትምህርት ላልተሰጣት ቤተ ክርስቲያን፣ መሠረታዊ ትምህርተ ድነትን ለመስጠት፣
3 በእግዚአብሔር አጠቃላይ የመቤዠት ዕቅድ ውስጥ፣ የአይሁድንና የአሕዛብን ግንኙነት ለማብራራት ነው:: ከአይሁድ ወገን የነበሩት የአመጋገብን ሕግ በመጠበቅ ላይ ያተኰሩ ስለ ነበር (14፥2-6)፣ በብዙኀኑ የአሕዛብ ክርስቲያኖች ዘንድ ይናቁ ነበር (14፥1)::

ጳውሎስ ይህን መልእክት ሲጽፍ፣ ምናልባት በቆሮንቶስ (ሐሥ 20፥2-3) ሦስተኛው ሐዋርያዊ ጒዞው ላይ የነበረ ይመስላል:: በምሥራቅ ሜድትራንያን የነበረው ሥራ ከብዙ በጥቂቱ ተጠናቆ ስለ ነበር (15፥18-23)፣ ጳውሎስ የሮምን ቤተ ክርስቲያን ለመጐብኘት ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው (1፥11-12፤ 15፥23-24 ይመ):: በዚህ ጊዜ ግን ወደ ሮም ለመሄድ አልቻለም፤ ምክንያቱም ከአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት የተሰበሰበውን ገንዘብ እርሱ ራሱ ለማድረስ ፈልጎ ስለ ነበር ነው:: ስለዚህ ወደ ሮም በመሄድ ፈንታ፣ ወደ ፊት እግረ መንገዱን እስጳንያ ከሚፈጽመው ሐዋርያዊ ተልእኮ ጋር አያይዞ እነርሱንም ስለሚጐበኛቸው፣ በሮም የሚገኙትን ክርስቲያኖች ዝግጁ ለማድረግ ይህን መልእክት ጽፎ ላከላቸው (15፥23-24 ይመ):: ጳውሎስ ወደ ሮም ሄዶ ለማገልገል ለብዙ ዓመታት ይመኝ ነበር (1፥13-15 ይመ)፤ ይህም መልእክት በዚያ ከተማ ለነበረው የአገልግሎት ዕቅዱ፣ ጥንቃቄ የተሞላበትና ተገቢ ፈር የተከተለ የትምህርተ መለኮት መግቢያ በመሆን ጠቅሞታል:: በሮም ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ስላልነበረው፣ በዚያ ስለ ተከሠተው ችግር አይናገርም (ይሁን እንጂ 14፥1-15፥13 ይመ፤ በተጨማሪ ከ13፥1-7፤ 16፥17-18 ጋር ያነጻጽሩ)::

**የመልእክቱ ልዩ ባሕርያት**

1. ከጳውሎስ መልእክቶች ሁሉ እጅግ በጣም የተቀናጀ የአጻጻፍ ሥርዐትን ይከተላል፤ ከመልእክትነት ይልቅ ዝርዝር ሁኔታን ያካተተ የትምህርተ መለኮት አጻጻፍ ባሕርይ ይታይበታል::
2. በክርስትና አስተምህሮ ላይ ያተኵራል፤ በዚህ መልእክት ውስጥ አጽንዖት የተደረገባቸው ትምህርተ መለኮታዊ መሪ ሐሳቦች ብዛታቸውና አስፈላጊነታቸው የሚደነቅ ነው፤ እነዚህም:- ኀጢአት፣ ድነት፣ ጸጋ፣ እምነት፣ ጽድቅ፣ መጽደቅ፣ ቅድስና፣ ቤዛነት፣ ሞትና ትንሣኤ ናቸው::
3. ብሉይ ኪዳንን በሰፋት ይጠቅሳል፤ ጳውሎስ በመልእክቶቹ አዘውትሮ ከብሉይ ኪዳን ቢጠቅስም፣ በተለይ በሮሜ መልእክት ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ሐሳቡ በእነዚህ ጥቅሶች ላይ ተመርኵዞ ተብራርቶአል (በተለይም ም 9-11 ይመ)::
4. ለእስራኤል እጅግ የማሰብ ሁኔታ ይታይበታል፤ ጳውሎስ እስራኤል አሁን ስላለችበት ሁኔታ፣ ከአሕዛብ ጋር ስላላት ግንኙነትና ስለ መጨረሻዋ ጽፎአል::

**አስተዋፅኦ**

1. መግቢያ (1፥1-15)
2. መሪ ሐሳብ፤ ከእግዚአብሔር የሆነ ጽድቅ (1፥16-17)
3. የሰው ዘር ሁሉ ጽድቅ አልባነት (1፥18-3፥20)
    - ሀ. አሕዛብ (1፥18-22)
    - ለ. አይሁድ (2፥1-3፡8)
    - ሐ. እጣሬ ሰዎች ሁሉ (3፥9-20)
4. ጽድቅ በእምነት በክርስቶስ መገኘቱ (3፥21-5፥21)
    - ሀ. በክርስቶስ (3፥21-26)
    - ለ. በእምነት (3፥27-4፥25)
        - (1) መርሕ መመሥረቱ (3፥27-4፥25)
        - (2) መርሑ መብራራቱ (ም 4)
    - ሐ. የጽድቅ ፍሬ (5፥1-11)::
    - መ. እጣሬ፤ ጽድቅ የለሽ ሰው ከእግዚአብሔር የጽድቅ ስጦታ ጋር ሲነጻጸር (5፥12-21)
5. ጽድቅ መሰጠቱ፤ ቅድስና (ም 6-8)፤
    - ሀ. ከኀጢአት ባርነት ነጻ መሆን (ም 6)
    - ለ. ከሕግ ርግማን ነጻ መሆን (ም 7)
    - ሐ. በመንፈስ ቅዱስ ኀይል መኖር (ም 8)
6. የእግዚአብሔር ጻድቅነት መገለጡ፤ የእስራኤል መተው ችግር (ም 9-11)
    - ሀ. የመተዉ ፍትሐዊነት (9፥1-29)
    - ለ. የመተዉ ምክንያት (9፥30-10፥21)


ሐ. ችግሩን የሚያረግቡ እውነታዎች (ም 11)
(1) መተዉ ሁሉን የሚመለከት አለመሆኑ (11፥1-10)
(2) መተዉ የመጨረሻ አለመሆኑ (11፥11-24)
(3) የእግዚአብሔር የፍጻሜ ዐላማ ምሕረት መሆኑ (11፥25-36)

7. ጽድቅ ተግባራዊ መሆኑ (12፥1-15፥13)
ሀ. በአካሉ፤ በቤተ ክርስቲያን (ም 12)
ለ. በዓለም ውስጥ (ም 13)
ሐ. በደካማና በብርቱ ክርስቲያኖች መካከል (14፥1-15፥13)

8. መደምደሚያ (15፥14-33)

9. በጎ አስተያየት መስጠትና ሰላምታ (ም 16)

በ64 ዓ.ም የሮም ከተማ አብዛኛው ክፍል በእሳት በመቃጠሉ፣ ኔሮ ከተማዋን ያቃጠሏት ክርስቲያኖች ናቸው በማለት ስላሳበባቸው በክርስቲያኖች ላይ ታላቅ ስደት አስነስቶ ነበር። ሕዝቡ ግን ጥፋተኛው ኔሮ መሆኑን በመገንዘብ፣ በጨዋታ ስፍራ ያለ አግባብ መከራ ለደረሰባቸው ክርስቲያኖች ያዘኑ እንደነበር የዘመኑ ታሪክ ያመለክታል።




# ሮም
## በጳውሎስ ዘመን

ሮም ከፖለቲካዊ ጠቀሜታ፣ ከመልክአ ምድራዊ አቀማመጧና ከውበቷ የተነሣ የሮማውያ ግዛት ዋነኛ ከተማና መዲና ልትሆን ችላለች።

በወጣ ገባ ኩረብቶች ግርጌና በጉብታዎች («ሰባቱ ኩረብቶች») ላይ የተቈረቈረችው እንዲሁም በቲበር ወንዝ መታጠፊያ በስተ ምሥራቅ የምትገኘው ሮም እጅግ የታወቀችው በሕዝቧ ድንቅ ሕንጻዎች፣ በምድር ሥር በሚሄዱ ታላላቅ የውሃ ቦዮች፣ በመታጠቢያ ስፍራዎች፣ በቲያትር ቤቶችና እስከ ክፍላተ አገር በሚዘልቁ አውራ ጐዳናዎች ነበር። (የቲበር ወንዝ ከሜዲትራንያን ባሕር 29 ኪ.ሜ. ያህል ይርቃል።) ከተማዋ በ4ኛው ምእተ ዓመት ቅ.ክ. የነበራት የቈዳ ስፋት በ«ሰርቪያ» ቅጥር የተከለለ ነበር። በመጀመሪያው የክርስቲያኖች ምእተ ዓመት ግን ከተማዋ እጅግ ከመስፋፋቷ የተነሣ የጥንት ቅጥሯን አልፋ ያለ ምንም ከለላ በታላቅነቷ ተንጣላ ትገኝ ነበር።

በከተማዋ ውስጥ ጐልተው ከሚታዩ ቦታዎች፦ በላዩ ላይ የጁፒተርና የጁኖ አብያተ ጣዖታት የተሠሩበት የካፒቶላይን ኩረብታና የነገሥታት አብያተ መንግሥታት ያቈጠቈጡበት የፓላታይን ኩረብታ ናቸው፤ ከእነዚህም አንዱ «ወርቃማው ቤት» በመባል የሚታወቀው የኔሮ ቤተ መንግሥት በፓላታይን ላይ ይገኝ ነበር። በሁለቱ ኩረብቶች ግርጌ የግዛተ ዓፄው ማእከል የነበረው «የሮም ፎረም» የተባለው ታላቅ የስብሰባ ቦታ ይገኝ ነበር።

ሮም አንዳንድ ጊዜ የሰው ልጅ ሥራ ሁሉ ቍንጮ ናት ስትባል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የፍጥረተ ዓለም ሁሉ ጉድፍ ከየአቅጣጫው የሚሰበሰብበት ቈሻሻ ማጠራቀሚያ ተብላለች።

በሕንጻዎቿ አሠራር የሕዝብ ኩራት ለመባልና በከተማ ነክ ማኅበራዊ ሕይወቷ፣ ከዘመናችን የከተማ ኑሮ የሞራል ዝቅጠት ባላነሰ፣ በውድቀት አፋፍ ላይ ያለች ከተማ ለመባል ምክንያቶች ነበሯት።

ሐዋርያው ጳውሎስ ወደዚች ከተማ የገባው አፒያ በተባለው አውራ መንገድ ነበር። እርሱም በመጀመሪያ በቁም እስረኝነት በዚያ ኖረ። ለጥቂት ጊዜ በነጻነት ከኖረ በኋላ ደግሞ፣ በፎረሙ አጠገብ በነበረው «ማመርታይም» በተባለው በምድር ሥር በሚገኝ እስር ቤት ተፈርዶበት ተጣለ። ጳውሎስ ከቤተ መንግሥት እስከ እስር ቤት ለሚገኘው ሰው ሁሉ ወንጌልን ሰብኳል። በትውፊት እንደሚነገረው ጳውሎስ ከሮም ምተማ ውጭ በኦስያ መንገድ ላይ በሚገኝ ቦታ ላይ ሞት ተፈርዶበት በ68 ዓ.ም ተገድሏል።

1 ጳውሎስ፣ የክርስቶስ ኢየሱስ ባሪያ፣ ሐዋ
ርያ ሊሆን የተጠራና ለእግዚአብሔር ወንጌል
የተለየ፤ 2ስለዚህ ወንጌል በነቢያቱ በኩል በቅ
ዱሳት መጻሕፍት አስቀድሞ ተስፋ ተሰጠ::
3ወንጌሉም ስለ ልጁ፣ በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለ
ሆነ፣ 4በቅድስና መንፈስ[ሀ] ደግሞ ከሙታን በመ
ነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ስለ
ተገለጠው[ለ] ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ነው:: 5በእርሱ በኩል ስለ ስሙ ከአሕዛብ
ሁሉ መካከል ሰዎችን በእምነት አማካይነት
ወደሚገኘው መታዘዝ ለመጥራት ጸጋንና ሐዋ
ርያነትን ተቀበልን:: 6እናንተ ራሳችሁም ለኢ
የሱስ ክርስቶስ እንዲሆኑ ከተጠሩ መካከል
ናችሁ::

7በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ለመ
ሆን ለተጠራችሁ በሮም ላላችሁ ሁሉ፤ ከአ
ባታችን ከእግዚአብሔር፣ ከጌታም ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን::

## ሮምን ለማየት የጳውሎስ ናፍቆት

8ከሁሉ አስቀድሜ፣ እምነታችሁ በዓለም
ሁሉ በመሰማቱ፣ ስለ ሁላችሁም አምላኬን
በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ:: 9ዘወትር
ምን ያህል እንደማስባችሁ፣ የልጁን ወንጌል
በመስበክ በሙሉ ልቤ የማገለግለው እግዚ
አብሔር ምስክሬ ነው፤ 10በጸሎቴ ሁልጊዜ
አስባችኋለሁ፤ አሁን ደግሞ በመጨረሻ በእግዚ
አብሔር ፈቃድ ወደ እናንተ እንድመጣ መንገድ
ይከፈትልኝ ዘንድ እጸልያለሁ::
11እንድትጸኑ የሚያስችላችሁን መንፈሳዊ
ስጦታ አካፍላችሁ ዘንድ፣ ላያችሁ እናፍቃ
ለሁ:: 12ይኸውም እናንተና እኔ በእያንዳን
ዳችን እምነት እርስ በርሳችን እንድንበረ
ታታ ነው:: 13ወንድሞች ሆይ፣ በሌሎች
አሕዛብ ዘንድ እንደ ሆነልኝ፣ በእናንተም
ዘንድ ፍሬ እንዳገኝ ብዙ ጊዜ ዐቅጄ እንደ
ነበርና፣ ሆኖም ግን፣ እስከ አሁን ድረስ
መከልከሌን እንድታውቁ እወዳለሁ::
14ግሪኮች ለሆኑትና ላልሆኑት፣ ለጥበበኞ
ችና ለማያስተውሉ፣ ዕዳ አለብኝ፤ 15በሮም ለም
ትኖሩ፣ ለእናንተም ወንጌልን ለመስበክ የምጓ
ጓው ለዚህ ነው::
16በወንጌል አላፍርም፤ ምክንያቱም ለሚያ
ምን ሁሉ ለድነት የሚሆን የእግዚአብሔር ኀይል
ነው፤ ይህም በመጀመሪያ ለአይሁድ፣ ቀጥሎም
ለአሕዛብ ነው:: 17በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ
ተገልጦአልና፤ ጽድቁም ከመጀመሪያ እስከ
መጨረሻ በእምነት[ሐ] የሆነ ነው፣ "ጻድቅ በእምነት
ይኖራል" ተብሎ እንደ ተጻፈው::

## የእግዚአብሔር ቍጣ በሰዎች ላይ

18በክፋታቸው እውነትን ዐፍነው በሚይዙ፣
በዐመፃቸውና በክፋታቸው ሁሉ ላይ የእግዚ

1፥1 ሐሥ9፥15፤ ሮሜ15፥16፤1ቆሮ1፥1፤ 2ቆሮ2፥12፤11፥7፤1ተሰ2፥8:9፤ 1ጴጥ4፥17
1፥2 ሉቃ1፥70፤ ሐሥ 13፥32፤ ቲቶ1፥2፤ ሮሜ3፥21፤ገላ3፥8
1፥3 ማቴ1፥1፤ ዮሐ1፥14፤ ሮሜ 9፥5፤
1፥4 ማቴ4፥3፤ ሐሥ2፥24፤ 1ቆሮ1፥2
1፥5 ሐሥ9፥15፤ 6፥7፤ሮሜ16፥26፤ 1ጢሞ1፥14፤
1፥6 ይሁዳ1፤ ራእ17፥14
1፥7 ሐሥ9፥13፤ ሮሜ8፥39፤1ቆሮ1፥3፤ ኤፌ1፥2፤1ተሰ1፥4፤1ጢሞ1፥2፤ቲቶ1፥4፤ 1ጴጥ1፥2
1፥8 ሮሜ10፥18፤ 16፥19፤1ቆሮ1፥4፤ ኤፌ1፥16፤1ተሰ2፥13፤ 2ተሰ1፥3፤ 2ጢሞ1፥3፤
1፥9 ኢዮ16፥19፤ ኤር42፥5፤2ቆሮ1፥23፤ገላ1፥20፤ፊል1፥8፤1ተሰ2፥5:10፤ 2ጢሞ1፥3፤
1፥10 ቍ13፤ 1ሳሙ12፥23፤ ሉቃ18፥1፤ሐሥ 1፥14፤ ሐሥ18፥21፤ ሮሜ15፥32፤ ኤፌ1፥16፤ፊል1፥4፤ ቈላ1፥9፤2ተሰ1፥11፤ 2ጢሞ1፥3፤ ፊሞ4
1፥11 ሮሜ15፥23፤ 1ቆሮ1፥7፤12፥1-31
1፥13 ሮሜ11፥25፤7፥1፤15፥22:23
1፥14 1ቆሮ9፥16
1፥15 ሮሜ15፥20
1፥16 ዮሐ3፥15፤ ሐሥ3፥26፤13፥46፤ ሮሜ2፥9:10፤ 1ቆሮ1፥18፤2ጢሞ1፥8፤
1፥17 ዕን2፥4፤ ሮሜ3፥21፤9፥30፤ ፊል3፥9፤ገላ3፥11፤ዕብ10፥38
1፥18 ዮሐ3፥36፤ ሮሜ5፥9፤ኤፌ5፥6፤ቈላ3፥6፤1ተሰ1፥10፤ ራእ19፥15

ሀ4 ወይም *በቅድስናው መንፈስ*
ለ4 ወይም *የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ስለ ተሾመ*
ሐ17 ወይም *ከእምነት ወደ እምነት*

1፥1 *ጳውሎስ*፤ በጥንት ዘመን፣ ጸሐፊዎች ስማቸውን በሚጽፉት ደብዳቤ መጀመሪያ ላይ ይጠቅሱ ነበር፣ በበለጠ ሁኔታ ስለ ጳውሎስ ለመረዳት የሐሥ 9፥1፤ የፊል 3፥4-14 ማብ ይመ:: *ባሪያ*፤ ይህ ቃል በግሪኩ ሁለት ትርጕሞች አሉት፤ የመጀመሪያው "ባሪያ" ሲሆን፣ የራሱን ኑሮ ለመኖር ነፃነት የሌለው፣ ሙሉ በሙሉ ለጌታ ፈቃድ የተሰጠ ማለት ነው፤ ሁለተኛው፣ "አገልጋይ" ሲሆን፣ በራሱ ፈቃድ ጌታውን ለማገልገል ምርጫ ያደረገ ማለት ነው፤ የዘፀ 14፥31፤ የመዝ 18 ርእስ፤ የኢሳ 41፥8-9፤ 42፥1 ማብ ይመ:: *ሐዋርያ*፤ ልዩ በሆነ መንገድ በክርስቶስ የተሾመ ነው (የማር 6፥30፤ የ1ቆሮ 1፥1፤ የዕብ 3፥1 ማብ ይመ):: *ወንጌል*፤ የማር 1፥1 ማብ ይመ::

1፥2 *በነቢያቱ*፤ ይህ ቃል በቀጥታ የሚያመለክተው የትንቢት መጻሕፍት ጸሐፊዎችን ብቻ ሳይሆን፣ በጠቅላላ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ኢየሱስ ትንቢት የተናገሩትን ሁሉ ነው (የሉቃ 24፥27:44 ማብ ይመ):: *ቅዱሳት መጻሕፍት*፤ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ያመለክታል::

1፥4 *በቅድስና መንፈስ*፤ ከሥላሴ አንዱ ስለ ሆነው ስለ መንፈስ ቅዱስ ያሳስባል::

1፥7 *ቅዱሳን*፤ በግሪኩ የዚህ ቃል መሠረታዊ ሐሳብ የሆነው "ቅድስና" የሚል ቃል ነው:: ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋ የተነሣ ለእግዚአብሔር የተለዩ ቅዱሳን ናቸው፤ ስለሆነም ከኀጢአትና ከዓለም ርኵሰት በመራቅ፣ በኑሮአቸው ከዕለት ወደ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ አብልጠው እየተቀደሱ መመላለስ ይገባቸዋል (የ1ቆሮ 1፥2 ማብ ይመ):: *ጸጋና*፤ የዮሐ 4፥2፤ የገላ 1፥3፤ የኤፌ 1፥2 ማብ ይመ:: *ሰላም*፤ የዮሐ 14፥27፤ 20፥19፤ የገላ 1፥3፤ የኤፌ 1፥2 ማብ ይመ::

1፥8 *አመሰግናለሁ*፤ በጳውሎስ የደብዳቤ አጻጻፍ ስልት ብዙውን ጊዜ ቀዳሚ ሥፍራ ይዞ የሚገኘው ምስጋና ነው (1ቆሮ 1፥4፤ ኤፌ 1፥16፤ ፊል 1፥3፤ ቈላ 1፥3፤ 1ተሰ 1፥2፤ 2ተሰ 1፥3፤ 2ጢሞ1፥3፤ ፊሞ 1፥4 ይመ):: *በኢየሱስ ክርስቶስ*፤ ክርስቲያን ልመናን ብቻ ሳይሆን ምስጋናንም ይዞ ወደ እግዚአብሔር ሲቀርብ በክርስቶስ በኩል መሆን አለበት (ዮሐ 15፥16 ይመ):: *በዓለም ሁሉ*፤ ወንጌል የተሰበከበትን ማንኛውንም ሥፍራ ያመለክታል::

1፥9 *የልጁን ወንጌል*፤ "የእግዚአብሔር ወንጌል" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው (ቍ 1)::

1፥12 *እርስ በርሳችን*፤ የጳውሎስ ልባዊ ትሕትና በሮም ክርስቲያኖች ለመገልገልና እነርሱንም ለማገልገል በነበረው ፍላጎቱ ታይቷል::

1፥13 *ፍሬ*፤ በጀማሪ ክርስቲያኖችና በነባር ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚታየውን መንፈሳዊ ዕድገት ያመለክታል:: *በሌሎች አሕዛብ ዘንድ ... በእናንተም ዘንድ*፤ በሮም ቤተ ክርስቲያን የነበሩት ክርስቲያኖች በአብዛኛው ከአሕዛብ ወገን እንደ ነበሩ ያሳያል::

1፥14 *ግሪኮች*፤ በሮም ግዛት ላቲን ተናጋሪ ነዋሪዎች ቢሆኑም፣ የግሪክ ቋንቋን የሚናገሩ ወይም የግሪኮችን አኗኗር ዘይቤ የሚከተሉ አሕዛብ ናቸው:: *ግሪኮች ... ላልሆኑት*፤ አነጋገራቸው ለተወላጅ ግሪክኛ ተናጋሪዎች ትርጕም አልባ በመሆኑ፣ ያል ሠለጠኑ እንደሆኑ ይነገራል፤ እነዚህም ሰዎች ጳውሎስ ወንጌልን የሰበከላቸው ሌሎቹ የአሕዛብ ወገን ነበሩ::

*1፥16-17*፤ የዚህ መጽሐፍ መሪ ሐሳብ በዚህ ክፍል ይገኛል::

1፥16 *አላፍርም*፤ በሮም ግዛት ዋና ከተማ እንኳ ወንጌልን ለመስበክ እንዳላፈረ ያሳያል (ቍ 15 ይመ):: *ወንጌል*፤ የማር 1፥1 ማብ ይመ:: *በመጀመሪያ*፤ በጊዜ አንጻር ብቻ ሳይሆን፣ የወንጌልን በረከት በማግኘት ከሌሎች ቀዳሚ መሆንን ያመለክታል:: መዳን ከአይሁድ ነው (ዮሐ 4፥22)፤ መሲሕ የተገኘውም ከዚሁ ወገን ነው:: አስቀድሞ "የእግዚአብሔር ቃል" (3፥2)፣ ኪዳኖች፣ ሕግ፣ በመቅደስ የማምለክ ሥርዐት፤ የመለኮት ክብር መገለጥና መሲሐዊ ትንቢቶች የመጡት ለእነሱ ነው (9፥3-5):: አይሁድ እነዚህን ጥቅሞች ለማግኘት ቀዳሚ የሆኑት፣ ከሰው ሁሉ የተሻሉ ስለ ሆኑ ወይም እግዚአብሔር ስለ አደላላቸው አይደለም፤ ነገር ግን ዓለምን በወንጌል መድረስ ይቻል ዘንድ፣ በተራቸው ወንጌልን ለሌሎች የማድረስ ኀላፊነት የሚወስዱ የተወሰኑ ሕዝቦችን ከተወሰነ ቦታ ይዞ መነሣት አስፈላጊ በመሆኑ ነው::

1፥17 *ጽድቅ*፤ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት "በትክክለኛ ሁኔታ" ላይ ሆኖ መገኘት ማለት ነው (የ 2፥13፤ የ3፥21:24 ማብ ይመ)፡

*1፥18-3፥20*፤ ጳውሎስ፣ ከእግዚአብሔር የተገኘውን ጽድቅ መሪ ሐሳብ ለማጕላት (1፥17፤ 3፥21-5፥21)፣ ሁሉ ኀጢአትን በመሥራ

ስብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣል፤ 19ስለ ስግዚ
ስብሔር ሊታወቅ የሚቻለው ለእነርሱ ግልጽ
ነው፤ ምክንያቱም ስግዚስብሔር ለእነርሱ ግልጽ
አድርጎታል:: 20ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የማ
ይታየው የስግዚስብሔር ባሕርይ ይኸውም ዘላለ
ማዊ ኀይሉና መለኮትነቱ፣ ከፍጥረቱ በግልጽ
ይታያል፤ ስለዚህ ሰዎች ማመካኛ የላቸውም::
21ስግዚስብሔርን ቢያውቁም እንኳ፣ እንደ
ስምባክነቱ አላከበሩትም፤ ምስጋናም አላቀረ
ቡለትም፤ ነገር ግን ሐሳባቸው ፍሬ ቢስ ሆነ፤
የማያስተውል ልባቸው ጨለመ:: 22ጥበበኞች
ነን ቢሉም፣ ሞኞች ሆኑ፤ 23የዘላለም ስም
ባክን ክብር ምዉት በሆነው ሰው፣ በወፎች፣
በእንስሳትና በምድር ላይ በሚሳቡ ፍጥረት
መልክ መስለው ለወጡ::
24ስለዚህም ስግዚስብሔር በኀጢአት በተሞላው
የልባቸው ምኞት እርስ በርሳቸው የገዛ አካ
ላቸውን እንዲያስነውሩ ቅድስና ለሌለው ሩካቤ
ሥጋ አሳልፎ ሰጣቸው:: 25የስግዚስብሔርን እው
ነት በሐሰት ለወጡ፤ በፈጣሪ ፈንታ ፍጡር
አመለኩ፤ አገለገሉም፤ ፈጣሪም ለዘላለም
የተመሰገነ ነው፤ አሜን::
26በዚህም ምክንያት ስግዚስብሔር አሳፋሪ
ለሆነ ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም
እንኳ ለባሕርያቸው የሚገባውን ግንኙነት
ባሕርያቸው ላልሆነው ግንኙነት ለወጡ::
27እንደዚሁም ወንዶች ለባሕርያቸው የሚገ
ባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በር
ሳቸው በፍትወት ተቃጠሉ፤ ወንዶች ከወንዶች

1፥19 ሐሥ14፥17
1፥20 መዝ19፥1-6፤
ሮሜ2፥1
1፥21 ዘፍ8፥21፤
ኤር2፥5፤17፥9፤
ኤፌ4፥17:18
1፥22 1ቆሮ1፥20:
27፤3፥18:19
1፥23 ዘዳ4፥16:17፤
መዝ106፥20፤ኤር2፥
11፤ ሐሥ17፥29
1፥24 ቍ26:28፤
መዝ81፥12፤ኤፌ4፥1
9፤ 1ጴጥ4፥3
1፥25 ኢሳ44፥20፤
ኤር10፥14፤13፥25፤1
6፥19:20፤
ሮሜ9፥5፤11፥36፤
2ቆሮ11፥31፤
1፥26 ቍ24:28፤
ዘሌ18፥22:23፤ኤፌ4
፥19፤1ተሰ4፥5፤
1፥27 ዘሌ18፥22፤
20፥13፤1ቆሮ6፥18
1፥28 ቍ24:26
1፥29 2ቆሮ12፥20፤
1ጢሞ 5፥13፤
ያዕ3፥2፤3፤ዮሐ10
1፥30 2ጢሞ3:2
1፥31 2ጢሞ3፥3
1፥32 መዝ50፥18፤
ሉቃ11፥48፤ሐሥ8፥1፤
22፥20፤ ሮሜ6፥23፤
2፥1 2ሳሙ12፥5-7፤
ማቴ7፥1:2፤ሮሜ
1፥20፤

ጋር ነውር ፈጸሙ፤ ለክፉ አድራጐታቸውም
የሚገባቸውን ቅጣት በገዛ ራሳቸው ላይ
አመጡ::
28ከዚህም በላይ በሐሳባቸው ስግዚስብሔርን
ማወቅ አይጠቅምም በማለታቸው፣ መደረግ
የማይገባውን እንዲያደርጉ ስግዚስብሔር ለማ
ይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው:: 29በሁሉም
ዐይነት ዐመፃ፣ ክፋት፣ ስግብግብነትና ምግባረ
ብልሹነት ተሞልተዋል፤ ቅናትን፣ ነፍስ
ገዳይነትን፣ ጥልን፣ አታላይነትንና ተንኰልን
የተሞሉ ናቸው፤ ሐሜተኞች፣ 30ስም አጥፊዎች፣
ስምባክን የሚጠሉ፣ ተሳዳቢዎች፣ ትዕቢተኞችና
ትምክሕተኞች ናቸው፤ ክፋትን የሚሠሩበትን
መንገድ ያውጠነጥናሉ፤ ለወላጆቻቸው አይታ
ዘዙም:: 31የማያስተውሉ፣ ውል የሚያፈርሱ፣
ርኅራኄ የሌላቸውና ጨካኞች ናቸው:: 32ይህን
የሚያደርጉ ሁሉ ሞት ይገባቸዋል የሚለውን
ትክክለኛ የሆነውን የስግዚስብሔርን ሕግ ቢያ
ውቁም፣ እነዚህን ነገሮች ማድረግ ብቻ ሳይ
ሆን፣ እንዲህ የሚያደርጉትንም ያበረታታሉ::

## የስግዚስብሔር ጻድቅ ፍርድ

2 ስለዚህ አንተ በሌላው ላይ የምትፈርድ፣
የምታመካኝበት የለህም፤ በሌላው ላይ
በምትፈርድበት ነገር ሁሉ፣ ራስህን ትኰንና
ለህ፤ ፈራጅ የሆንኸው አንተ ያንኑ ታደር
ጋለህና:: 2እንደዚህ በሚያደርጉትም ላይ
የስግዚስብሔር ፍርድ ትክክለኛ መሆኑን እናው
ቃለን:: 3እንግዲህ አንተ ሰው በሌሎች ላይ

ታቸው ከእግዚአብሔር ብቻ የሚሰጠው ጽድቅ እንደሚያስፈልጋቸው በማሳየት፣ ያሉበትን ሁኔታ ለይቶ ይገልጣል:: የአሕዛብን ኀጢአት (1፥18-32) እና የአይሁድን ኀጢአት (2፥1-3፥8) ለየብቻ ካሳየ በኋላ የሁሉንም ኀጢአት፣ ይኸውም የአሕዛብንና የአይሁድን ኀጢአተኛ መሆን ይገልጻል (3፥9-20)::

*1፥18-20፤* ፍጥረታዊው ዓለም የእግዚአብሔርን ክብር ስለሚገልጽ (መዝ 19፥1)፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ወይም ስለ ክርስቶስ ያልሰማ እንኳ ቢሆን፣ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ካልሰጠ፣ ይቅርታ የለውም::

1፥18 ***የእግዚአብሔር ቍጣ፤*** በቂ ምክንያትና ተጨባጭ ነገር ሳይኖረው ከሰዎች እንደሚወጣው ቍጣ ሳይሆን፣ ቅዱስ ከሆነው የእግዚአብሔር ባሕርይና ፈቃድ ጋር የሚቃረነውን ኀጢአት ለመቈጣት ከእግዚአብሔር የሚወጣ እውነተኛ የጥላቻ ስሜት ነው፤ አደራረጉም ቅዱስ ነው:: ***ይገለጣል፤*** የእግዚአብሔር ቍጣ የተጠበቀው በክፉዎች ላይ ለሚሰጠው ለመጨረሻው ፍርድ ቀን ብቻ ሳይሆን (1ተሰ 1፥10፤ ራእ19፥15፤ 20፥11-15)፣ በአሁኑ ዘመንም እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን ለኀጢአታቸው አሳልፎ በመስጠቱ ይገለጣል (ቍ 24፥32):: ***እውነትን፤*** በአፈጣጠር ሥርዐት ውስጥ ስለ እግዚአብሔር የተገለጸው እውነት ነው::

1፥21 ***እግዚአብሔርን ቢያውቁም፤*** በአፈጣጠር ሥርዐት ውስጥ የሆነውን የእርሱን መገለጥ በማየት እግዚአብሔርን ዐውቀዋል (ቍ 19-20):: እነዚህ ሰዎች ጣዖት አምላኪዎች መሆናቸውና (ቍ 23) በአፈጣጠር ሥርዐት በኩል እግዚአብሔርን ማወቃቸው አሕዛብ እንደ ነበሩ ያመለክታል:: ***ምስጋናም አላቀረቡለትም፤*** ከእግዚአብሔር ስለሚቀበሏቸው ምድራዊ በረከቶች፣ ማለትም ለፀሓይ ብርሃን፣ ለዝናብ፣ ለአዝርዕትና ለመሳሰሉት እግዚአብሔርን አላመሰገኑትም (ማቴ 5፥45፤ ሐሥ 14፥17 ይመ)::

1፥23 ***ክብር፤*** ልዩ የሆነው የእግዚአብሔር ክብር (ኢሳ 48፥11 ይመ)፤ በተለያዩ ፍጥረታት የተመሰሉትንና ራሱ የፈጠራቸውን አማልክት በእግዚአብሔር ቦታ በማምለኩ፣ በኀጢአት የወደቀው ሰው ሊያየው ያልቻለው የእግዚአብሔር ክብር ነው::

1፥24:26:28 ***እግዚአብሔር ... አሳልፎ ሰጣቸው፤*** ከመተላለፋቸው የተነሣ ኀጢአት እንዲሠለጥንባቸው ተትተዋል::

1፥25 ***አሜን፤*** "የተባለው ነገር ትክክለኛና እርግጠኛ ነው" ወይም "እንደ ተባለው ይሁን" ማለት ሊሆን ይችላል:: (9፥5፤ 11፥36፤ 15፥33፤ 16፥27፤ እንዲሁም የዘዳ 27፥15 ማብ ይመ፤ ከ1ነገ 1፥36 ጋር ያነጻጽሩ)::

1፥26 ***ሴቶቻቸውም፤*** ሚስቶቻቸው የሆኑትን ሴቶች ብቻ ማለት ላይሆን ይችላል::

*1፥27፤* ወንድ ከሌላ ወንድ ጋር የሚያደርገው የግብረ ሥጋ ግንኙነት በእግዚአብሔር ፊት ኀጢአት ነው፤ ብሉይ ኪዳንም ይህንኑ ድርጊት ያወግዛል (ዘሌ 18፥22 ይመ)፤ እንዲህ ዐይነቱ ድርጊት ሰው በሞራል ከመውደቁና ከእግዚአብሔር ከመራቁ የተነሣ የሚፈጽመው ኀጢአት ነው (ዘፍ 19፥4-5 ይመ)::

1፥28 ***እግዚአብሔርን ማወቅ፤*** ቍ 19፥21 ይመ:: ***ለማይረባ አእምሮ፤*** ድርጊታቸው ክፉ ሐሳባቸውንና ምኞታቸውን ተከትሎ ይመጣል (ቍ 21፤ ማር 7፥20-23 ይመ)::

1፥32 ***ቢያውቁም፤*** ዐመፅ የተሞላበት ባሕርያቸው፣ የእግዚአብሔርን ሕግ ካለማወቅ የተነሣ ሳይሆን እንደ ራሳቸው ፈቃድ ለመሄድ ከመመኘትና እግዚአብሔርን ካለመታዘዝ የመነጨ ነው:: ***ያበረታታሉ፤*** ሌሎች በሚያደርጉት ኀጢአት ከማዘን ይልቅ፣ በመተላለፋቸው መደሰትና መስማማት እንዲገፉበትም ማደፋፈር እጅግ የከፋ ኀጢአት ነው::

*2፥1-16፤* በዚህ ክፍል፣ እግዚአብሔር ፍርድ በሚሰጥበት ጊዜ መመሪያዎች ምን እንደ ሆኑ ጳውሎስ እንደሚከተለው ያቀርባል:: ይኸውም 1) በእውነት (ቍ 2) 2)በየሰው ተግባር (ቍ 6-11) እንዲሁም 3) በአንድ ሰው የመረዳት መጠን (ቍ 12-15) ላይ የተመሠረተ ነው:: ሐዋርያው የአይሁድን ኀጢአት የሚገልጸው እነዚህን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ነው (ቍ 17-29)::

2፥1 ***የምታመካኝበት የለህም፤*** ጳውሎስ ስለ መፍረድ የሚያስተምረው ትምህርት ኢየሱስ ካስተማረው ትምህርት ጋር ይስማማል (የማቴ 7፥1 ማብ ይመ)፤ ይህም በመሠረቱ መፍረድን የሚቃወም ሳይሆን፣ በግብዝነት የሚሰጠውን ፍርድ የሚነቅፍ ነው:: ***ፈራጅ የሆንኸው አንተ፤*** በብሉይ ኪዳን የተገለጠውን የእግዚአብሔርን እውነት ባለማወቃቸውና ሥነ ምግባር በጐደለው አኗኗራቸው የተነሣ አሕዛብን ለሚንቁ አይሁድ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው::

2፥2 ***እናውቃለን፤*** የሚናገረውን መልእክት የሚሰሙ ሰዎች በሰሙት ነገር የተስማሙ አድርጎ በመቍጠር፣ ጳውሎስ በመልእክቱ ውስጥ አዘውትሮ የሚጠቀምበት አገላለጽ ነው (3፥19፤ 7፥14፤ 8፥22:28፤ 1ቆሮ 8፥1-4፤ 2ቆሮ 5፥1፤ 1ጢሞ 1፥8 ይመ)::

*2፥3፤* ጌታ ኢየሱስም እንደዚህ ዐይነቱን ባሕርይ ይነቅፋል

እየፈረድህ፣ ያንኑ የምታደርግ ከሆነ ከእግዚ
ብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃል? 4ወይስ
የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሓ የሚመራህ መሆ
ኑን ሳትገነዘብ፣ የቸርነቱን፣ የቻይነቱን የትዕ
ግሥቱን ባለ ጠግነት ትንቃለህ?
5ነገር ግን በድንዳኔህና ንስሓ በማይገባ
ልብህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርዱ ሲገለጥ
በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን በራስህ ላይ ቍጣን
ታከማቻለህ:: 6እግዚአብሔር "ለእያንዳንዱ እንደ
ሥራው ይሰጠዋል"፤ 7በጎ የሆነውን ጸንቶ በማድረግ
ክብርን፣ ሞገስንና ዘላለማዊነትን ለሚሹ የዘ
ላለም ሕይወት ይሰጣቸዋል:: 8ነገር ግን በራስ
ወዳዶች፣ እውነትን ትተው ክፋትን በሚከተሉ
ፍርድና ቍጣ ይደርስባቸዋል:: 9ክፉ በሚያደርግ
በማንኛውም ሰው፣ አስቀድሞ በአይሁድ
ከዚያም በአሕዛብ ላይ መከራና ጭንቀት
ይሆናል፤ 10ነገር ግን በጎ ለሚሠራ ለማንኛውም፣
አስቀድሞ ለአይሁድ ከዚያም ለአሕዛብ ክብር፣
ሞገስና ሰላም ይሆንለታል፤ 11እግዚአብሔር ለማ
ንም አያደላምና::
12ሕግ ሳይኖራቸው ኀጢአት የሠሩ ሁሉ
ያለ ሕግ ይጠፋሉ፤ ሕግ እያላቸው ኀጢአት
የሠሩ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤ 13ምክንያቱም
በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን የሚባሉት ለሕጉ
የሚታዘዙ እንጂ፣ ሕጉን የሚሰሙ አይደሉም::
14ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ሕግ የሚያዝዘውን
ነገር በተፈጥሮ ሲያደርጉ፣ ሕግ ባይኖራቸውም
እነርሱ ለራሳቸው ሕግ ናቸው:: 15ኅሊናቸው
ስለሚመሰክር፣ ሐሳባቸው ስለሚከሳቸው፣
ደግሞም ስለሚከላከልላቸው የሕግ ትእዛዝ
በልባቸው የተጻፈ መሆኑን ያሳያሉ:: 16ይህም
በወንጌል እንደማስተምረው እግዚአብሔር በሰው
ልብ የተሰወረውን በክርስቶስ በኩል በሚፈ
ርድበት ዕለት ግልጽ ይሆናል::

## ሕግና አይሁድ

17አንተ ይሁዲ ነኝ ካልህ፣ በሕግ የምት
ተማመንና ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት
የምትኵራራ፣ 18በሕግ በመመራትህም ፈቃዱን
ዐውቀህ ፍጹም የሆነውን ለይተህ ከያዝህ፣
19ለዕውሮች መሪ፣ በጨለማ ላሉትም ብርሃን
መሆንህን እርግጠኛ ከሆንህ፣ 20በሕጉም ካገ
ኘኸው ዕውቀትና እውነት የተነሣ አላዋቂ
ለሆኑት መካሪ፣ ለሕፃናት አስተማሪ ከሆንህ፣
21እንግዲህ አንተ ሌሎችን የምታስተምር፣
ራስህን አታስተምርምን? አትስረቅ ብለህ
የምትሰብክ፣ ትሰርቃለህን? 22አንተ ሰዎች
ማመንዘር የለባቸውም የምትል፣ ታመነዝራ
ለህን? አንተ ጣዖትን የምትጸየፍ፣ ቤተ
መቅደስን ትመዘብራለህን? 23አንተ በሕግ
የምትመካ፣ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን
ታዋርዳለህን? 24ይህም "በእናንተ ምክንያት
የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ ዘንድ ይሰደባል"
ተብሎ እንደ ተጻፈው መሆኑ ነው::
25ሕግን የምትፈጽም ከሆነ ግዝረት ዋጋ
አለው፤ ሕግን የምትተላለፍ ከሆነ ግን እን
ዳልተገረዝህ ትሆናለህ:: 26ያልተገረዙት ሕጉ
የሚያዝዘውን የሚፈጽሙ ከሆነ፣ እንደ ተገረዙ
አይቈጠሩምን? 27አንተ የተጻፈ ሕግ፣ ግዝረ
ትም ቢኖርህ፣ ሕግ ተላላፊ በመሆንህ፣ በሥጋ

2፥4 ዘፀ34፥6፤ ሮሜ9፥22፤9፥23፤11፥22፤ 11፥33፤ኤፌ1፥7:18፤ 2፥7፤3፥8:16፤ፊል2፥21 3፥25፤1ጢሞ1፥16፤ 1ጴጥ3፥20፤2ጴጥ3፥9፤ 2ጴጥ3፥15
2፥5 መዝ110፥5፤ ይሁዳ1፥6፤ራእ6፥17፤
2፥6 መዝ62፥12፤ ማቴ16፥27፤ምሳ24፥12
2፥7 ቍ10፤ ማቴ25፥46፤ 1ቆሮ15፥53:54፤ 2ጢሞ1፥10፤
2፥8 ሕዝ22፥31፤ 2ተሰ2፥12፤
2፥9 ቍ10፤ መዝ32፥10፤ሮሜ1፥16
2፥10 ቍ9፤ ሮሜ1፥16
2፥11 ሐሥ10፥34
2፥12 ሮሜ3፥19፤ 6፥14፤ 7፥4፤ 1ቆሮ 9፥20:21፤ ገላ 4፥21፤5፥18፤
2፥13 ያዕ1፥22: 23:25
2፥14 ሐሥ10፥35
2፥16 መክ12፥14፤ ሐሥ10፥42፤ሮሜ16፥ 25፤1ቆሮ 4፥5፤ 2ጢሞ 2፥8
2፥17 ቍ23፤ ኤር 8፥8፤ሚክ3፥11፤ ዮሐ 5፥45፤ሮሜ 9፥4
2፥21 ማቴ23፥3:4
2፥22 ሐሥ19፥37
2፥23 ቍ17
2፥24 ኢሳ52፥5፤ ሕዝ36፥22፤2ጴጥ2፥2
2፥25 ቍ13:27፤ ኤር 4፥4፤ 9፥25:26፤ ገላ 5፥3፤ 2፥26 ሮሜ8፥4፤ 1ቆሮ 7፥19
2፥27 ማቴ12፥41: 42

(ማቴ 7፥3 ይመ፤ ከሉቃ 18፥9 ጋር ያነጻጽሩ)::

*2፥4፤* የእግዚአብሔር ቸርነት ዐላማ፣ ሰዎች ንስሓ ይገቡ ዘንድ ዕድል መስጠት ነው (2ጴጥ 3፥9) ነገር ግን አይሁድ የእርሱን ትዕግሥት በተሳሳተ መንገድ በመረዳት፣ ፍርድ ለመስጠት ፍላጎት እንደ ሌለው አድርገው ቈጠሩት::

2፥5 *በእግዚአብሔር የቍጣ ቀን*፤ በ1፥18-32 ላይ ከተጠቀሰው ፍርድ የተለየ፣ በመጨረሻው ዘመን የሚሆነውን የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚያመለክት ነው::

*2፥6-7፤* ጳውሎስ ሰው የሚድነው በሥራው ሳይሆን፣ ክርስቶስ ስለ እርሱ በሠራው ሥራ በማመን እንደ ሆነ አስረግጦ ሲጽፍ፣ ሮሜንም ጨምሮ በሌሎች ጽሑፎቹ ሁሉ በተከታታይ የተገለጸውን ሐሳብ በመቃረን ማብራራቱ አይደለም፤ ይልቁንስ እንደየሥራው ፍርድ የመስጠትን መርሕ መግለጹ ነው (የቍ 1-16 ማብ ይመ):: ማንም መልካም ሥራ በማድረግ ቢጸና፣ ነቀፋም ሳይኖረው ፍጹም ሰው ሆኖ ቢኖር፣ የዘለዓለምን ሕይወት ያገኛል:: ማንም ሰው ፍጹም መሆን አይችልም፤ ሆኖ ቢገኝ ግን እግዚአብሔር በሰው ላይ እንደ ሥራው ስለሚፈርድ፣ ለዚያ ሰው ሕይወትን ይሰጠዋል::

2፥9 *አስቀድሞ በአይሁድ*፤ መንፈሳዊ በረከትን ማግኘት መንፈሳዊ ኀላፊነትን ያስከትላል (አሞ 3፥2፤ ሉቃ 12፥48 ይመ)::

*2፥11፤* ይህ የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መሠረታዊ ትምህርት ነው::

2፥12 *ሕግ*፤ የሙሴን ሕግ ያመለክታል፤ "ያለ ሕግ ኀጢአት የሠሩ ሁሉ" ሲል አሕዛብን ለማሳየት ነው:: እግዚአብሔር ሰዎች እንዲከተሉት በሰጣቸውና በተረዱት መመሪያው መሠረት ይፈርዳል:: አሕዛብ ሳልተሰጣቸው ሕግ ባለመታዘዛቸው አይፈ ርድባቸውም፤ የእነርሱ ፍርድ በተለየ መንገድ ይሆናል (1፥18-20፤ 2፥15 ይመ:: ከአሞ 1፥3-2፥3 ጋር ያነጻጽሩ)::

2፥13 *ጻድቃን የሚባሉት ለሕጉ የሚታዘዙ*፤ ጳውሎስ ሕግ የሚለውን ቃል ሲጠቅስ፣ ደረጃን የመመዘኛ መንገድ አድርጎ በመቍጠር፣ ከጸጋ ውጭ ድነት እንድናገኝበት መጠቈሙ አይደለም፤ እዚህ ላይ "ሕግ" እግዚአብሔር ለሰው ዘር የገለጸውን ፈቃድ ያመለክታል:: ከእምነት፣ ራስን አሳልፎ ከመስጠትና ከመታዘዝ ተለይቶ ሕግን መስማት ብቻ የሚያስገኘው ጥቅም የለም::

2፥14 *በተፈጥሮ*፤ ለሙሴ ሕግ ሳይሆን፣ ለተፈጥሮ ስሜት መገዛትን ያመለክታል:: *ሕግ የሚያዝዘውን ነገር*፤ አረማውያን የሙሴን ሕግ ፈጽመዋል ማለት ሳይሆን፣ በኅብረተሰባቸው ውስጥ የሚከናወኑትን ማለትም ከሙሴ ሕግ ጋር የሚስማሙትን፣ ይኸውም ለታመሙና በዕድሜ ለገፉ ሰዎች እንክብካቤ ማድረግን፣ ወላጆችን ማክበርን፣ ዝሙትን መቃወምንና የመሳሰሉትን መልካም ተግባሮች ማድረጋቸውን ያመለክታል:: *ለራሳቸው ሕግ ናቸው*፤ የሙሴ ሕግ ለአይሁድ መመሪያ እንደ ሆነ ሁሉ፣ በኅሊና የሚደገፈው ግብረገባዊ ተፈጥሮም ለአረማውያን መመሪያ ነው (ቍ 15)::

*2፥16፤* ይህ ጥቅስ ከ ቍ 13 ጋር ተያይዞ መታየት አለበት::

*2፥17-24፤* በዚህ ክፍል የተጻፈው ሐሳብ የቀረበው በክርክር መልክ ነው:: ከአይሁድ ወገን ስለ ነበር፣ በራሱ ጽድቅ የሚመካው ይሁዲ እንዴት እንደሚያስብ ያውቃል:: የተሰጧቸውን በጎ ነገሮች በመጥቀስ አይሁድ ለእነዚህ በጎ ነገሮች ብቁ አለመሆናቸውን ጳውሎስ ያመለክታል፤ አይሁድ የተቀበሏቸውን በጎ ነገሮች በሥራ ላይ ባለማዋላቸው እነዚህ በጎ ነገሮች ዕዳ ሆኑባቸው:: ጳውሎስ ከቍ 1-16 የሚገኘውን የፍርድ መመሪያ ለአይሁድ እንዲውል አድርጓል (የቍ 1-16 ማብ ይመ)::

2፥19-20 *ለዕውሮች ... ለሕፃናት*፤ አይሁድ በሙሴ ሕግ በመመካትና ራሳቸውን የበላይ አድርገው በመቍጠር የሚንቋቸውን አሕዛብ ያመለክታል::

2፥22 *ቤተ መቅደስን ትመዘብራለህ?*፤ ሐሥ 19፥37 ይመ:: በአረማውያን ቤተ መቅደስ ውስጥ ከፍተኛ መጠን ያለው ንብረት ይከማች ነበር::

2፥25 *ግዝረት*፤ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያደረገው ኪዳን ምልክት (ዘሌ 12፥3) ሲሆን፣ ለኪዳኑ በረከት መተማመኛ ነበር (ዘፍ 17 እና የዘፍ 17፥10-11 ማብ ይመ):: አይሁድ ግዝረትን፣ ከእግዚአብሔር ለሚቀበሉት በጎ ነገር ዋስትና አድርገው ይቈጥሩት ነበር::

*2፥27፤* ለጽድቅ ሲባል በሚከናወነው ተግባር የአሕዛብ ድርጊት ከአይሁድ የላቀ ከሆነ፣ ይህ ሁኔታ በሙሴ ሕግ ዕውቀት

ያልተገረዘው ለሕግ በመታዘዙ ይፈርድብሃል።
28አንድ ሰው ለይምሰል በውጫዊው ብቻ
ይሁዲ ልሁን ቢል ይሁዲ አይሆንም፤ እውነ
ትኛ ግዝረትም ውጫዊና ሥጋዊ ሥርዐት
አይደለም። 29ዳሩ ግን አንድ ሰው ይሁዲ የሚ
ሆነው በውስጣዊ ማንነቱ ይሁዲ ሆኖ ሲገኝ
ነው። ግዝረትም ግዝረት የሚሆነው በተጻ
ፈው ሕግ ሳይሆን፣ በመንፈስ የልብ ግዝረት
ሲኖር ነው። እንዲህ ያለው ሰው ምስጋናው
ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።

## የእግዚአብሔር ታማኝነት

3 ታዲያ አይሁዳዊ መሆን ጥቅሙ ምንድን
ነው? መገረዝስ ምን ፋይዳ አለው? 2በየት
ኛውም መንገድ ጥቅሙ ብዙ ነው፤ ከሁሉ
አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃል በዐደራ የተሰጠው
ለእነርሱ ነው።
3አንዳንዶች እምነት ባይኖራቸውስ? የእ
ነርሱ አለማመን የእግዚአብሔርን ታማኝነት ዋጋ
ያሳጣዋልን? 4ፈጽሞ አይሆንም! ሰው ሁሉ ሐሰ
ተኛ፣ እግዚአብሔር ግን እውነተኛ ይሁን፤ እንዲህ
ተብሎ ተጽፎአልና፤

"ከቃልህ የተነሣ እውነተኛ፣
በፍርድም ፊት ረቺ ትሆናለህ።"

5የእኛ ዐመፃ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አጒልቶ
የሚያሳይ ከሆነ፣ ምን ማለት እንችላለን?
እንደ ሰው ለመከራከር ያህል እግዚአብሔር በእኛ
ላይ ቍጣውን ማምጣቱ ትክክል አይደለም
ሊባል ነውን? እንደ ሰው ሲታሰብ ማለቴ
ነው። 6በእርግጥ እንዲህ ሊሆን አይችልም፤
እንዲህ ቢሆንማ ኖሮ እግዚአብሔር በዓለም ላይ
እንዴት ሊፈርድ ይችላል? 7"የእኔ ውሸተኛ
መሆን የእግዚአብሔርን እውነተኛነት የሚያጐላ፣
ክብሩንም የሚጨምርለት ከሆነ፣ ኀጢአተኛ
ተብዬ እስካሁን እንዴት ይፈርድብኛል?"
በማለት ሊከራከር የሚችል ሰው ይኖር ይሆ
ናል። 8ይህማ "በጎ እንዲመጣ ክፉ እንሥራ"
ይላሉ በማለት አንዳንዶች እንደሚያስወሩ
ብን ነው፤ በእነዚህ ሰዎች ላይ የሚደርሰው
ፍርድ ትክክለኛ ነው።

## ማንም ጻድቅ አይደለም

9እንግዲህ ምን እንላለን? እኛ ከእነርሱ
እንበልጣለንን?[ም] ከቶ አይደለም፤ አይሁድም
ሆኑ አሕዛብ፣ ሁሉም ከኀጢአት በታች እን
ደሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋል፤
10እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤

"ጻድቅ ማንም የለም፤ አንድም እንኳ፤
11አስተዋይ የለም፤
እግዚአብሔርንም የሚሻ አንድም የለም።
12ሁሉም ተሳስተዋል፤
በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል፤
በጎ የሚያደርግ ማንም የለም፤
አንድም እንኳ።"
13"ጕሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው፤
አንደበታቸው ሽንገላን ያዘወትራል።"
"በከንፈሮቻቸው የእባብ መርዝ አለ።"
14"አፋቸው ርግማንና ምሬት ሞልቶበታል።"
15"እግራቸው ደም ለማፍሰስ ፈጣን ነው፤
16በመንገዳቸው ጥፋትና ጕስቍልና ይኖሩል፤
17የሰላምንም መንገድ አያውቁም።"
18"በዐይናቸው ፊት የእግዚአብሔር
ፍርሀት የለም።"

19እንግዲህ አፍ ሁሉ እንዲዘጋና ዓለም በሙሉ
ለእግዚአብሔር መልስ እንዲሰጥ ሕግ የሚናገረው
ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንደ ሆነ፣ እናው

2፥28 ማቴ3፥9፤ ዮሐ8፥39፤ሮሜ9፥6፡7፤ገላ6፥15
2፥29 ዘዳ30፥6፤ ዮሐ5፥44፤12፥43፤ ሮሜ7፥6፤ 1ቆሮ4፥5፤ 2ቆሮ3፥6፤10፥18፤ ገላ1፥10፤ፊል3፥3፤ ቈላ2፥11፤1ተሰ2፥4፤ 1ጴጥ3፥4
3፥2 ዘዳ4፥8፤ መዝ147፥19፤ ሐሥ7፥38፤ሮሜ9፥4፡5፤
3፥3 ሮሜ10፥16፤ 2ጢሞ2፥13፤ዕብ4፥2፤
3፥4 መዝ116፥11፤ 51፥4፤ዮሐ3፥33፤
3፥5 ሮሜ 5፥8፤ 6፥19፤ ገላ3፥15
3፥6 ዘፍ18፥25፤ ሮሜ2፥16
3፥7 ቍ4፤ ሮሜ9፥19
3፥8 ሮሜ6፥1
3፥9 ቍ1፡19፡23፤ 1ነገ8፥46፤ 2ዜና 6፥36፤መዝ106፥6፤ መክ7፥20፤ሮሜ5፥12፤ 11፥32፤ገላ3፥22
3፥12 መዝ14፥1-3፤ 53፥1-3፤
3፥13 መዝ5፥9፤ 140፥3
3፥14 መዝ10፥7
3፥17 ኢሳ59፥7፡8
3፥18 መዝ36፥1
3፥19 ቍ9፤ መዝ63፥11፤107፥42፤ ሕዝ16፥63፤ ዮሐ10፥34፤ ሮሜ2፥12፤

ም9 ወይም *እንብሳለን?*

በላቀ ደረጃ ላይ የሚገኙትን አይሁድ ይኰንናል።

2፥29 *በመንፈስ*፤ የእግዚአብሔር ሰው የመሆን እውነተኛ ማስረጃ፣ መንፈስ ቅዱስ በልቡ ውስጥ የሚያከናውነው መታደስ እንጂ በውጫዊ ሰውነት ላይ የሚታየው ምልክት አይደለም፤ ይህን ማስረጃ ጳውሎስ "የልብ ግዝረት" ይለዋል (ዘዳ 30፥6 ይመ)።

3፥2 *አስቀድሞ*፤ ጳውሎስ 9፥4-5 እስከሚደርስ ድረስ፣ ይሁዲ መሆን የሚያስገኘው የተለየ ጥቅም ምን እንደ ሆነ አይገል ጽም። *በዐደራ የተሰጠው*፤ ከእግዚአብሔር ቃል የሚገኘውን በረከት ተካፋይ መሆን፣ ጌዴታ መወጣትንና በኀላፊነት መጠየቅን ያስከትላል።

3፥3 *የእግዚአብሔርን ታማኝነት*፤ እግዚአብሔር ለገባው ቃል ታማኝ በመሆኑ እስራኤል አላመነምና ይቀጣዋል (ቍ5፤ 2ጢሞ 2፥13 ይመ)

*3፥4፤* እግዚአብሔር ኀጢአትን መቅጣቱ ጻድቅ ለሆነው ባሕርዩ ታማኝ መሆኑን ያሳያል።

3፥5 *የእግዚአብሔርን ጽድቅ አጒልቶ የሚያሳይ*፤ በኀጢአት የተበከለውንና አሳዛኝ የሆነውን የሰው ዘር ታሪክ በማመልከት ያነጻጽራል። *እንደ ሰው ለመከራከር ያህል፤* ከሰው ደካማ ጐን አንጻር የተነገረ ነው።

3፥6 *ሊፈርድ ይችላል*፤ በመጨረሻው የፍርድ ቀን እግዚ አብሔር የሚሰጠውን ፍርድ የሚያመለክት ነው። *በዓለም*፤ በሕገ ተፈጥሮና በሙሴ ሕግ ሥር ያሉትን ሰዎች የሚያመለክት ሲሆን (ቍ 19)፣ በ1፥20 ከተገለጸው ይኸኛው እጅግ ውሱን ነው።

3፥9 *እኛ ከእነርሱ እንበልጣለን?* በእግዚአብሔር ፊት አይሁድ ከአሕዛብ አይበልጡም ማለት ነው። *ሁሉም*፤ የዚህ ቃል ሐሳብ ከቍ 9-12 ባለው ክፍል "ከቶ አይደለም"፤ "ማንም የለም"፤ "አንድም እንኳ" በሚሉ ሐረጎች በተለያየ አገላለጽ ተደጋግሞ ተጠ ቅሶአል። *ከኀጢአት በታች*፤ በኀጢአት ኀይል ቍጥጥር ሥርና ከኀጢአት ፍርድ በታች መሆንን ያሳያል።

*3፥10-18፤* በብሉይ ኪዳን የሚገኙ ጥቅሶችን የያዘ ሲሆን፣ አይሁድና አሕዛብ ሁለቱም በኀጢአት ኀይል ሥር መሆናቸውን ጳውሎስ በአጽንዖት የገለጸበት ክፍል ነው። ጥቅሶች ሁልጊዜ ቃል በቃል ለምን እንደማይጠቀሱ የተለያዩ ምክንያቶች ይቀርባሉ። 1) አንዳንድ ጊዜ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች አጠቃላይ ሐሳብን ለማስጠት እንጂ ጥቅስን ቃል በቃል የማያስቀምጡ በመሆናቸው 2) በግሪክ ቋንቋ የጥቅስ ምልክቶች ሥራ ላይ አለመዋላቸው፣ 3) ግሪኮች በዕብራይስጥ ከተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ትውውቅ ስለ ሌላቸውና ጥቅሶቹ ሁልጊዜ ከዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ወደ ግሪክኛ ከተተረጐመው የተወሰዱ በመሆናቸው፣ 4) አንዳንድ ጊዜ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊ ሐሳቡን ግልጽ ለማድረግ ሆን ብሎ፣ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ በመመራት ከብሉይ ኪዳን የሚወሰደውን ጥቅስ ያሰፋዋል፤ ያሳጥረዋል፤ አባባሉን ያሻሽለዋል፤ ወይም ደግሞ ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑትን የጽሑፍ ክፍሎች አጣምሮ ይጽፋል።

3፥11 *አስተዋይ የለም*፤ ስለ እግዚአብሔርና ትክክለኛ ስለ ሆነው ነገር መረዳት የሚፈልግ የለም።

3፥13 *የተከፈተ መቃብር*፤ በኀጢአት የተበከለውን ልብ ያመለክታል።

3፥18 *የእግዚአብሔር ፍርሀት*፤ እግዚአብሔርን በታላቅ ፍርሀት ማክበር ሲሆን፣ ይህም እግዚአብሔርን ለመምሰል ዋነኛ መንገድ ነው (የዘፍ 20፥11 ማብ ይመ)። "እግዚአብሔርን በመፍ ራት ሰው ከክፋት ይመለሳል" (ምሳ 16፥6 ይመ፤ ከምሳ 3፥7፤ ከ8፥13፤ ከ9፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

3፥19 *እናውቃለን*፤ የ2፥2 ማብ ይመ፣ *ሕግ*፤ በዮሐ 10፥34፣ 15፥25፤ በ1ቆሮ 14፥21 እንደ ተጠቀሰው፣ ብሉይ ኪዳን ማለት ነው። *ከሕግ በታች ላሉት*፤ አይሁዶችን ያመለክታል። *አፍ ሁሉ ... ዓለም በሙሉ*፤ አይሁድም ሆኑ አሕዛብ ኀጢአተኞችና

ቃለን፤ 20ስለዚህ ሕግን በመጠበቅ ማንም
በእርሱ ፊት ጻድቅ ነው ሊባል አይችልም፤
ይልቁንም በሕግ አማካይነት ኀጢአትን
እንገነዘባለን።

## በእምነት የሚገኝ ጽድቅ

21አሁን ግን ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት፣
ከሕግ ውጭ የሆነ፣ የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገ
ልጦአል። 22ይህ የእግዚአብሔር ጽድቅ ኢየሱስ
ክርስቶስን በማመን የሚገኝ ጽድቅ ነው።
ልዩነት የለም፤ 23ምክንያቱም ሁሉም ኀጢ
አትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድ
ሎአቸዋል፤ 24በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ቤዛነት
እንዲያው በጸጋው ጸድቀዋል፤ 25በደሙም
በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር የማስተስረያ
መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል፤ʷ ይህንም
ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን ኀጢአት ሳይ
ቀጣ በትዕግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት
ነው፤ 26በአሁኑ ዘመን ይህን ያደረገው፣ ጽድቁን
ይኸውም እርሱ ራሱ ጻድቅ ሆኖ፣ በኢየሱስ
የሚያምነውን የሚያጸድቅ መሆኑን፣ ለማሳየት
ነው።

27ታዲያ ትምክሕት ወዴት ነው? እርሱማ
ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ? በሥራ ሕግ
ነውን? አይደለም፤ በእምነት ሕግ ነው እንጂ።
28ማንም ሰው ሕግን በመፈጸም ሳይሆን፣
በእምነት እንደሚጸድቅ እናረጋግጣለን። 29እግዚ
አብሔር የአይሁድ አምላክ ብቻ ነውን? የአሕዛብስ
አምላክ አይደለምን? አዎን፤ የአሕዛብም አምላክ
ነው፤ 30የተገረዘውን በእምነት፣ ያልተገረዘውንም
በዚያው እምነት የሚያጸድቅ አንድ እግዚ
አብሔር ብቻ ነውና። 31ታዲያ እንዲህ ከሆነ
ከእምነት የተነሣ ሕግን ዋጋ የሌለው እናደርግ
ይሆን? ፈጽሞ አይደረግም፤ ሕጉን እናጸናለን
እንጂ።

## አብርሃም በእምነት ጸደቀ

4 እንግዲህ በሥጋ የቀድሞ አባታችን የሆነ
አብርሃም በዚህ ረገድ ምን አገኘ እንላለን?

3፥20 ሐሥ13፥39፤ ሮሜ4፥15፤ገላ2፥16፤
3፥21 ኢሳ46፥13፤ ኤር23፥6፤ ሐሥ10፥43፤ ሮሜ1፥2፤17፤9፥30፤
3፥22 ዮሐ3፥15፤ ሮሜ1፥17፤4፥11፤ 9፥30፤10፥4፡12፤ ገላ2፥16፤3፥22፤28፤ ቆላ3፥11
3፥23 ቍ9
3፥24 መዝ130፥7፤ ዮሐ1፥14፡16፡17፤ ሮሜ 4፥16፤ 5፥21፤ 4፥25፤ 6፥14፤ 11፥5፤ 2ቆሮ12፥9፤ ኤፌ1፥7፡14፤ 2፥8፤ 4፥7፤1ቆሮ1፥30፤ ገላ4፥5፤ቆላ1፥14፤ ቲቶ2፥11፤ዕብ 4፥16፤ዕብ9፥12
3፥25 ዘፀ25፥17፤ ዘሌ16፥10፤መዝ65፥3፤ ሐሥ14፥16፤17፥30፤ 20፥28፤ሮሜ5፥9፤ ኤፌ1፥7፤ዕብ2፥17፤ 9፥28፤13፥12፤ 9፥12፡14፤1ጴጥ1፥19፤ 1ዮሐ4፥10፤ራእ1፥5፤
3፥27 ሮሜ2፥17፡ 23፤4፥2፤1ቆሮ1፥29-31፤ኤፌ2፥9
3፥28 ሐሥ13፥39፤ሮሜ3፥20፡21፤ ኤፌ2፥9፤ገላ2፥16፤3፥11፤ ያዕ2፥20፡24፡26፤ 3፥29 ሐሥ10፥34፡ 35፤ሮሜ9፥24፤10፥12፤ 15፥9፤ገላ3፥28 3፥30 ሮሜ4፥11፡ 12፤ ገላ3፥8
4፥1 ሮሜ8፥31፤ሉቃ3፥8

ʷ25 *ወይም እግዚአብሔር ቍጣውን በመተው ኀጢአትን ለማስወገድ*

ተጠያቂዎች መሆናቸውን ያሳያል።

3፥20 *ማንም ... ጻድቅ ነው ሊባል አይችልም*፤ የቍ 24 እና የ2፥13 ማብ ይመ።

*3፥21-5፥21*፤ አሕዛብም ሆኑ አይሁድ ሁሉም በራሳቸው ጻድቃን እንዳይደሉ በማሳየት (1፥18-3፥20)፣ እዚህ ላይ ጳውሎስ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ጽድቅን መስጠቱን ያመለክታል።

3፥21 *አሁን ግን*፤ ሁለት ትርጉም ሊኖረው ይችላል፤ 1) ጊዜን ያመለክታል፤ ጊዜ ሁሉ በሁለት የሚከፈል ሲሆን፣ "አሁን" በሚለው ጊዜ ውስጥ ከእግዚአብሔር የሆነው ጽድቅ መገለጡ ተመልክቶአል፤ 2) ሕግን በመጠበቅ በሚገኘው ጽድቅ (የማይቻል ነጽጽር ነው ቍ 20) እና ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጽድቅ መካከል ያለውን ያመለክታል። *ሕግና ነቢያት የመሰከሩለት*፤ ዘፍ 15፥6፤ መዝ 32፥1-2፤ ዕን 2፥4 ይመ።

3፥22-23 *ልዩነት የለም ... የእግዚአብሔርም ክብር*፤ ተዛ ማጅነት ያለው ሐሳብ ሲሆን፣ ይኸውም የሚያምኑ ሁሉ "እን ዲሁ ይጸድቃሉ" (ቍ 24) ይላል እንጂ "ኀጢአት የሠሩ ሁሉ ... እንዲሁ ይጸድቃሉ" አይልም።

3፥22 *ልዩነት የለም*፤ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ማለት ነው (10፥12 ይመ)።

3፥23 *የእግዚአብሔርም ክብር*፤ እግዚአብሔር ከመጀመ ሪያው ለሰው ልጆች የነበረውን በጎ ፈቃድ ያመለክታል፤ ሰው በኀጢአት ከመውደቁ በፊት የነበረውን ክብር (ዘፍ 1፥26 -28፤ መዝ 8፥5-6 ይመ፤ ከኤፌ 4፥24፤ ከቈላ 3፥10 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በክርስቶስ በማመን እንደ ገና ያገኘዋል (ዕብ 2፥5-9 ይመ)።

3፥24 *ጸድቀዋል*፤ ጳውሎስ ይህን ቃል በ2፥13፤-5፥1፤ በገላ 2-3 በተደጋጋሚ ጠቅሶታል። ቃሉ አንድ ሰው ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ በመቀበል ሲድን የሚሆነውን ነገር ይገልጻል፤ ይኸ ውም በአንድ በኩል እግዚአብሔር ሰውን በደለኛ እንዳልሆነ ያውጃል፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጻድቅ አድርጎ ያየዋል፤ እግዚአብሔር የሰውን በደል በመደምሰስ በምትኩ ጽድቁን አጐናጽፎታል። ይህን በሚመለከት ጳውሎስ ሁለት ሐሳቦችን በአጽንዖት ይገልጻል፤ 1) ማንም መልካም፣ ቅዱስና ጻድቅ በሆነ ሕይወት አይኖርም፤ "ጻድቅ ማንም የለም" (ቍ 10)፤ ምክንያቱም "ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎአቸዋል" (ቍ 23) ብሎአልና። ስለዚህ "ሕግን በመጠበቅ በእርሱ ፊት ማንም ጻድቅ አይባልም" (ቍ 20)። 2) ነገር ግን ሁሉ እንደ ኀጢአተኞች እንጂ እንደ ልጆች እንኳ ባይሆኑም፣ በኢየሱስ የሚያምኑት ሁሉ ጻድቃን እንጂ በደለኞች እንዳልሆኑ እግዚአብሔር ይናገራል። ይህ የሕግ ዕወጃ ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቶስ የእኛን የኀጢአት ዕዳ ለመክፈል ሞቶአልና፤ ለእኛም የሚቈጠር ፍጹም የሆነ የጽድቅ ሕይወት ኖሮአልና። የሮሜ መልእክት መሪ ሐሳብ ነው፤ በ1፥17 ላይም፣ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" ተብሎ ተገልጦአል። የክርስቶስ ጽድቅ፣ ይኸውም ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዙና ራሱን ለሞት አሳልፎ መስጠቱ በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ የእነርሱ እንደ ሆነ ይቈጠርላቸዋል። ጳውሎስ፣ "ተቈጠረለት" የሚለውን ቃል፣ በምዕራፍ 4 ላይ ደጋግሞ ይጠቅሳል። *እንዲያው በጸጋው*፤ የጽድቅ ዐቢይ ሐሳብ ይህ ነው፤ ሰው በኀጢአቱ በደለኛ ሆኖ ሊፈረድበት የሚገባ ቢሆንም (ቍ 9-19)፣ በክርስቶስ በማመኑ በእግዚአብሔር ጻድቅ ይባላል። ይህም ቀጥሎ በተለያየ መንገድ ተገልጾአል፤ 1) "እን ዲሁ በነጻ" ማለትም ያለ ምንም ክፍያ ስጦታ ሆኖ፣ 2) "በጸጋው"፣ 3) "በክርስቶስ ኢየሱስ በሆነው ቤዛነት" እንዲሁም 4) በእምነት (ቍ 25)። *ቤዛነት*፤ ባሪያ ከሚሸጥበት ገበያ የተገኘ ቃል ሲሆን፣ መሠረተ ሐሳቡም፣ የተጠየቀውን ገንዘብ በመክፈል በባርነት የሚገኝ ሰው ነጻ እንዲወጣ ማድረግ ነው። ክርስቶስ በሞቱ ዕዳ ችንን በመክፈሉ፣ በፍርድ ፊት ተጠያቂ ከሚያደርገን ጥፋትና ለኀጢአት ባሪያ ሆኖ ከመገዛትም ነጻ መሆናችንን ለማሳየት ሲል ጳውሎስ ይህን ቃል ይጠቀማል።

3፥25 *የማስተስረያ መሥዋዕት*፤ የግሪኩ አገላለጽ ይህን ሐረግ በማስመልከት፣ ከእግዚአብሔር ቅዱስ ባሕርይ የሚወጣው ጽድቅ ቍጣውን ለማብረድ ብቁ የሆነ መሥዋዕት እንደ ሆነ ይገልጻል። ስለዚህ ማስተስረያ በሕጉ መሠረት ሰዎች ሁሉ ለዘለዓ ለም ቅጣት የተመደቡ ናቸው፤ የ1ዮሐ 2፥2 ማብ ይመ። *በደሙም በሆነው እምነት*፤ ለድነት የሚበቃ እምነት ለእኛ ኀጢ አት ማስተስረያ መሥዋዕት ሆኖ የሞተውን ክርስቶስ ኢየሱስን ትምክህት ያደረገ እምነት ነው።

*3፥25-26*፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን እንስሳትን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ በምሳሌነት ሲቀጣ የነበረው የእግዚአብሔር ሰዎች ኀጢአት፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መሥዋዕት ሆኖ በመቅረቡ ፈጽሞ እንዲቀጣ ተደርጎአል።

3፥28 *በእምነት*፤ ሉተር ይህን ክፍል ሲተረጉም፣ "ብቻ" የሚል ቃል አስገብቶአል፤ ምንም እንኳ ቃሉ በግሪኩ ቅጅ ባይኖርም፣ የዚህን ክፍል ሐሳብ በትክክል ይገልጻል (የያዕ 2፥14-26 ማብ ይመ)።

3፥30 *አንድ እግዚአብሔር ብቻ*፤ ጳውሎስ በዘዳ 6፥4 የተጠቀሰው "አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው" የሚለውን የመጀመሪያውን የአይሁድ የእምነት አንቀጽ በማመልከት ለአይሁድና ለአሕዛብ፣ ለሁለቱም ወገኖች በክርስቶስ በማመን አንድ ብቻ የድነት መንገድ መኖሩን እርግጠኛ በመሆን ሐሳቡን ያቀርባል።

*3፥31*፤ ታዲያ እንዲህ ከሆነ፣ ሕግን ዋጋ የሌለው እናደርግ ይሆንን? የሚል ጥያቄ እንደሚቀርብበት በመገመት ጳውሎስ በም 6-7 ላይ ገላጭ የሆነ መልስ በመስጠት ሕግ አስፈላጊ መሆኑን በ13፥8-10 ላይ በአጽንዖት ይገልጻል። ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቁና በመንፈስ ቅዱስ አዲስ ሰው በመሆኑ፣ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕግ ለማክበርና ለመታዘዝ ይችላል (8፥2-4)።

4፥1 *አባታችን የሆነ አብርሃም*፤ የጸደቀ ሰው እውነተኛ ምሳሌ ሲሆን፣ ታላቁ የአይሁድ ነገድ አባት (ያዕ 2፥21-23 ይመ) ነው። በኢየሱስ

2 አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን ኖሮ፣ የሚመካበት
ነበረው፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት መመካት
አይችልም። 3 መጽሐፍስ ምን ይላል? "አብርሃም
እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።"
4 አንድ ሰው ሥራ ከሠራ ደመወዙ እንደ
ስጦታ ሳይሆን እንደ ተገቢ ዋጋው ይቈጠ
ርለታል። 5 ነገር ግን ለማይሠራው፣ ኃጥኡን
ሰው ጻድቅ በሚያደርግ በእግዚአብሔር ለሚያምን
ሰው፣ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቈጠርለታል።
6 ዳዊትም ጽድቅ ያለ ሥራ ስለሚቈጠርለት ሰው
ብፅዕና እንዲህ ብሎአል፤

7 "መተላለፋቸው ይቅር የተባለላቸው፣
ኀጢአታቸው የተሰረየላቸው፣
ብፁዓን ናቸው።
8 ኀጢአቱን፣ ጌታ ከቶ የማይቈጥርበት ሰው
ብፁዕ ነው።"

9 ይህ ብፅዕና ለተገረዙት ብቻ ነው ወይስ
ላልተገረዙትም? የአብርሃም እምነቱ ጽድቅ
ሆኖ ተቈጠረለት ብለናል። 10 ታዲያ እንዴት
ተቈጠረለት? ከተገረዘ በኋላ ነው ወይስ
ከመገረዙ በፊት? የተቈጠረለት ከተገረዘ በኋላ
ሳይሆን ከመገረዙ በፊት ነው። 11 ሳይገረዝ
በነበረው እምነት ላገኘው ጽድቅ፣ የመገረዝን
ምልክት ይኸውም የጽድቅን ማኅተም ተቀበለ፤
ስለዚህ ለሚያምኑ ነገር ግን ላልተገረዙት
ጽድቅ ይቈጠርላቸው ዘንድ የሁሉ አባት ነው።
12 እርሱ ለተገረዙትም አባት ነው፤ መገረዝ
ብቻ ሳይሆን፣ አባታችን አብርሃም ከመገረዙ
በፊት የነበረውን የእምነቱን ፈለግ ለሚከተሉ
ሁሉ ነው። 13 እርሱ የዓለም ወራሽ እንዲሆን
አብርሃምና ዘሩ ተስፋን የተቀበሉት በሕግ
በኩል አልነበረም፤ ነገር ግን በእምነት ከሆነው
ጽድቅ ነው።
14 በሕግ የሚኖሩት ወራሾች ከሆኑ፣ እምነት
የማይጠቅም፣ ተስፋም ከንቱ በሆነ ነበር፤
15 ሕግ ቍጣን ያስከትላል፤ ሕግ በሌለበት ግን
መተላለፍ አይኖርም።
16 ስለዚህ ተስፋው በእምነት መጥቶአል፤
ይኸውም ተስፋው በጸጋ እንዲሆንና ለአብ
ርሃም ዘር ሁሉ ዋስትና ይሆን ዘንድ ነው፤
ይህም በሕግ የእርሱ ለሆኑት ብቻ ሳይሆን፣
በእምነት የአብርሃም ለሆኑትም ነው፤ እር
ሱም የሁላችን አባት ነው፤ 17 ይህም "የብዙ
ሕዝብ አባት አድርጌሃለሁ" ተብሎ እንደ ተጻ
ፈው ነው፤ እርሱም ለሙታን ሕይወትን በሚ
ሰጥ፣ ያልነበረውንም እንደ ነበረ በሚያደርግ፣
ባመነበት በእግዚአብሔር ፊት አባታችን ነው።
18 "ዘርህም እንዲሁ ይሆናል" ተብሎ ለእ
ርሱ በተነገረው መሠረት፣ ምንም ተስፋ
በሌለበት፣ አብርሃም በተስፋ አምኖ የብዙ
ሕዝብ አባት ሆነ። 19 እርሱ የመቶ ዓመት
ሰው ሆኖ ሳለ፣ የራሱም ሰውነት ሆነ የሣራ
ማሕፀን ምዉት እንደ ነበረ እያወቀ በእምነቱ
አልደከመም። 20 ይልቁንም በእምነቱ በመጽናት
ለእግዚአብሔር ክብርን ሰጠ እንጂ፣ የእግዚአብሔርን

4፥2 1ቆሮ1፥31
4፥3 ቍ5:9:22፤ ዘፍ15፥6፤ገላ3፥6፤ ያዕ2፥23
4፥4 ሮሜ11፥6
4፥5 ቍ3:9:22፤ ሮሜ9፥30
4፥8 መዝ32፥1:2፤ 103፥12፤2ቆሮ5፥19
4፥9 ቍ3፤ ሮሜ3፥30፤
4፥11 ቍ16:17፤ ዘፍ17፥10:11፤ ሉቃ 3፥8፤ሮሜ3፥22
4፥13 ዘፍ17፥4-6፤ ሐሥ13፥32፤ ሮሜ9፥30፤ ገላ 3፥16:29፤
4፥14 ገላ3፥18
4፥15 ሮሜ7፥7-25፤ 7፥12፤ 3፥20፤5፥13፤ 7፥7፤1ቆሮ15፥56፤ 2ቆሮ3፥7፤ገላ3፥10፤
4፥16 ቍ11፤ ሉቃ3፥8፤ሮሜ3፥24፤ 15፥8፤ገላ3፥16
4፥17 ዘፍ17፥5፤ ኢሳ48፥13፤ዮሐ5፥21፤ 1ቆሮ1፥28
4፥18 ቍ17፤ ዘፍ15፥5
4፥19 ዘፍ17፥17፤ 18፥11፤ዕብ 11፥11:12፤
4፥20 1ሳሙ30፥6፤ ማቴ9፥8

ጊዜ የነበሩ አይሁድ አብርሃምን በሥራ የጸደቀ ሰው ምሳሌ አድርገው ሲቈጥሩት፣ ጳውሎስ ግን በእምነት ለሚገኘው ጽድቅ ጕልሕ ምሳሌ አድርጎ ያቀርበዋል (ገላ 3፥6-9 ይመ)።

*4፥3፤* ይህ ጥቅስ ስለ ሥራ ምንም የማይገልጸውን በዘፍ 15፥6 ላይ ያለውን ያመለክታል። *ተቈጠረለት፤* አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ ሊያስገኝለት የሚችል ሕግ አልጠበቀም፤ አገልግሎትም ሆነ ሃይማኖታዊ ሥርዐት አልፈጸመም፤ ነገር ግን ለእርሱ ተስፋ በሰጠው በእግዚአብሔር በማመኑ፣ ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት።

*4፥6-8፤* በኀጢአቱ ተጸጽቶ ንስሓ በመግባት ይቅርታ የሚጠይቀውን ኀጢአተኛ እግዚአብሔር ይቅር ይለዋል እንጂ በደሉን አይቈጥርበትም (መዝ 32፥3-5፤ ሕዝ 18፥23፡ 27-28፡ 32፤ 33፥14-16 ይመ)።

4፥9 *ለተገረዙት፤* አይሁድን ያመለክታል። *ላልተገረዙትም፤* አሕዛብን የሚያመለክት ነው።

4፥10 *ከተገረዘ በኋላ ሳይሆን ከመገረዙ በፊት ነው፤* አብርሃም ጻድቅ የተባለው (ዘፍ 15) ከመገረዙ ዐሥራ አራት ዓመት አስቀድሞ ነበር (ዘፍ 17)፤ እንዲሁም ተመሳሳይ ሐሳብ ለማግኘት ገላ 3፥17 ይመ።

4፥11 *ምልክት፤* ግዝረት፣ አብርሃም በእግዚአብሔር በማመኑ ለተቈጠረች ጽድቅ ውጫዊ ነው። *ስለዚህ፤* አብርሃም ለሚያምኑ፣ ነገር ግን ላልተገረዙ አሕዛብ "አባት" ነው፤ ምክንያቱም የአይሁድ ምልክት የሆነው የግዝረት ሥርዐት ከመመሥረቱ በፊት አምኖ ጸድቆአልና።

4፥12 *ለተገረዙትም አባት፤* አብርሃም ለሚያምኑ አይሁድም አባት ነው። ስለዚህ በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነት ሳይኖር፣ አንድ የጽድቅ መንገድ ብቻ እንዳለ የአብርሃም ታሪክ ያሳያል፤ ይህም የእምነት መንገድ ነው።

4፥13 *በሕግ በኩል አልነበረም፤* ተስፋው የሚፈጸመውና ዋጋ የሚኖረው ሕግ የሚጠይቀውን ነገር በማሟላት እንዳልሆነ ያሳያል። *ዘሩ፤* አብርሃም "አባታቸው ነው" ተብለው የሚጠቀሱትን ሁሉ ያመለክታል። በኦሪት ዘፍጥረት ስለ አብርሃም በተጻፈው ታሪክ ውስጥ ስለዚህ ወራሽነት በግልጽ የተነገረ ነገር የለም። ዘሩ እንደ ምድር አሸዋ እንደሚበዛ (ዘፍ 13፥16)፣ የከነዓንን ምድር እንደሚወርስና (ዘፍ 12፥7፤ 13፥14-15፤ 15፥7፤ 18-21፤ 17፥8) የምድር ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ (ዘፍ 12፥3፤ 18፥18) ወይም በዘሩ (ዘፍ 22፥18) እንደሚባረኩ ተስፋ ተሰጥቶታል። በኦሪት ዘፍጥረት ላይ በግልጽ እንደተጻፈው በአብርሃምና በዘሩ በኩል እግዚአብሔር የዓለምን ሁሉ የወደፊት ዕድል ለመወሰን አቅዶአል፤ ይህም እርሱና ዘሩ ምድርን እንደሚወርሱ (መዝ 37፥9፡11፡22፡29፡34፤ ማቴ5፥5 ይመ)፣ ለአብርሃም በተሰጠው ተስፋ ተመልክቶአል። ይህን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት በክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚመሠረተውንና ፍጹም የሆነውን መሲሓዊ መንግሥት መጠበቅ ያስፈልጋል።

4፥14 *በሕግ የሚኖሩት፤* ሕግ መፈጸምን መሠረት በማድረግ ወራሽነት ይገኛል የሚሉ ናቸው። *ተስፋም፤* የቍ 13 ማብ ይመ።

4፥15 *ሕግ ቍጣን ያስከትላል፤* ሕግ ኀጢአትን ስለሚገልጥና ስለሚያነሣሣ (7፥7-11 ይመ)፣ ተስፋን ሳይሆን ቍጣን ያመጣል። *መተላለፍ፤* ሥርዐትንና ሕግን መጣስ ማለት ነው። ሕግ በሌለበት ኀጢአት አለ፤ የመተላለፍ ባሕርይ ግን አይኖረውም።

*4፥16፤* በቍ 11-12 ላለው ክፍል ማጠቃለያ ሐሳብ ነው። በእምነትና በጸጋ መካከል ተዛምዶ ለመኖሩ 3፥24-25 እና ኤፌ 2፥8 ይመ። *በሕግ ... ለሆኑት፤* ከአይሁድ ወገን የሆኑትን ክርስቲያኖች ያመለክታል። *በእምነት የአብርሃም ለሆኑትም፤* የአብርሃም እምነት ተከፋዮች የሆኑ ነገር ግን እንደ አብርሃም ሕግ የሌላቸው ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው።

4፥17 ... *ባመነበት ... ፊት፤* ሌሎች በተለይም አይሁድ የፈለጉትን ቢሉትም፣ እግዚአብሔር አብርሃምን፣ የአይሁድና ያመኑት አሕዛብ አባት አድርጎ ይቈጥረዋል። *ለሙታን ሕይወትን በሚሰጥ ... ባመነበት* አብርሃምና ሣራ ሁለቱም ዕድሜአቸው ገፍቶ ልጅ መውለድ በማይችሉበት ጊዜ የይስሐቅን መወለድ ያመለክታል (ዘፍ 18፥11 ይመ)። ሁለተኛ ጳውሎስ የክርስቶስን ትንሣኤ በተዘዋዋሪ ይጠቀማል (ቍ 24-25 ይመ)። ያልነበረውንም እንደ ነበረ በሚያደርግ፤ በይስሐቅ መወለድ እንደሚታየው፣ እግዚአብሔር ከምንም አንድን የመፍጠር ችሎታ አለው።

4፥18 *ምንም ተስፋ በሌለበት ... በተስፋ አምኖ፤* ከሰው ችሎታ አኳያ ተስፋ ሁሉ በተሟጠጠ ጊዜ አብርሃም ተስፋውን በእግዚአብሔር አደረገ።

4፥19 *በእምነቱ አልደከመም፤* አብርሃም ልጅ ለመውለድ የተሰጠውን ተስፋ ከስሜቱ የተነሣ ቢጠራጠርም፣ እግዚአብሔር ይህን ሁኔታ በክፉ አላየበትም (ዘፍ 17፥17-18 ይመ)። *እንደ ነበረ እያወቀ፤* እምነት ያለው ሰው ነባራዊውን እውነታ እንደ ሌላ አድርጎ አይቈጥርም፤ ነገር ግን ከደረሰበት ችግር ሁሉ ባሻገር እግዚአብሔርንና የተሰጠውን ተስፋ ይመለከታል። *የሣራ ማሕፀን ምዉት እንደ ነበረ፤* ሣራ ከአብርሃም በዐሥር ዓመት ብታንስም (ዘፍ 17፥17 ይመ)፣ ልጅ የመውለድ ዕድሜዋ ግን ዐልፎ ነበር።

4፥20 *ለእግዚአብሔር ክብርን ሰጠ፤* እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ እንደሚፈጽም አብርሃም እምነት ስለ ነበረው ነው። ሥራ፣ ሰው

ተስፋ አልተጠራጠረም፤ 21እግዚአብሔር የሰጠ
ውን ተስፋ እንደሚፈጽም በሙሉ ልብ እር
ግጠኛ ነበር:: 22ስለዚህ፣ "ጽድቅ ሆኖ ተቈጠ
ረለት::" 23"ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት" የሚለው
ቃል የተጻፈው ለእርሱ ብቻ አይደለም፤
24ነገር ግን እግዚአብሔር ጽድቅ አድርጎ ለሚቈጥ
ርልን፣ ጌታችን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው
በእርሱ ለምናምን ለእኛም ጭምር ነው::
25እርሱ ስለ ኀጢአታችን እንዲሞት ዐልፎ
ተሰጠ፤ እኛን ጻድቅ አድርጎ ለማቅረብም
ከሞት ተነሣ::

## ሰላምና ደስታ

5 እንግዲህ በእምነት ስለ ጸደቅን፣ በጌታ
ችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር
ጋር ሰላም አለን[ʻ]:: 2በእርሱም በኩል አሁን
ወደ ቆምንበት ጸጋ በእምነት መግባት ችለናል፤
የእግዚአብሔርንም ክብር ተስፋ በማድረግ ሐሤት
እናደርጋለን::[ʻ] 3በዚህ ብቻ ሳይሆን በመከራ
ችንም ሐሤት እናደርጋለን[ʻ]፤ ምክንያቱም
መከራ ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ እናውቃለን::
4ትዕግሥት ጽናትን፣ ጽናት የተፈተነ ባሕርይን፣
የተፈተነ ባሕርይ ተስፋን፤ 5ይህም ተስፋ ለዕ
ፍረት አይዳርገንም፤ እግዚአብሔር በሰጠን በመ
ንፈስ ቅዱስ ፍቅሩን በልባችን አፍስሶአልና::
6ገና ደካሞች ሳለን፣ ልክ ጊዜው ሲደርስ፣
ክርስቶስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቶአልና:: 7ለጻድቅ
የሚሞት ሰው ማግኘት እጅጉን ያዳግታል፤
ለደግ ሰው ሲል ሊሞት የሚደፍር ምናልባት
ይገኝ ይሆናል:: 8ነገር ግን ገና ኀጢአተኞች
ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞተ፤ ይህም እግዚ
አብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል::
9አሁን በደሙ ከጸደቅን፣ ይልቁንማ በእ
ርሱ በኩል ከእግዚአብሔር ቍጣ እንዴት አን
ድንም! 10የእግዚአብሔር ጠላቶች ሳለን በልጁ
ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ ዕርቅን ካገኘን
በኋላ፣ በሕይወቱማ መዳናችን እንዴት የላቀ
አይሆንም! 11ይህ ብቻ አይደለም:: ነገር ግን
አሁን ዕርቅን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ ሐሤት
እናደርጋለን::

## ሞት በአዳም፣ ሕይወት በክርስቶስ

12ስለዚህ ኀጢአት በአንድ ሰው በኩል ወደ
ዓለም እንደ ገባ ሁሉ፣ ሞትም በኀጢአት
በኩል ገብቶአል፤ በዚሁ መንገድ ሞት ወደ

4፥21 ዘፍ18፥14፤ ማቴ19፥26
4፥22 ቍ3
4፥24 መዝ 102፥18፤ ዕን 2፥2፤ ሐሥ 2፥24፤ ሮሜ10፥9፤15፥4፤ 1ቆሮ 9፥10፤10፥11፤ 2ጢሞ3፥16:17፤ 1ጴጥ1፥21
4፥25 ኢሳ53፥5:6፤ ኢሳ 53፥11፤ሮሜ 5፥6:8፤8፥32፤1ቆሮ 6፥11፤2ቆሮ5፥21፤ ሮሜ 3፥24፤ 5፥1:9: 16:18፤8፥30፤ 2ቆሮ5፥15
5፥1 ቍ10፤ ሉቃ2፥14፤ ሮሜ4፥25፤3፥28፤
5፥2 1ቆሮ15፥1፤ ኤፌ2፥18፤3፥12፤ ዕብ3፥6
5፥3 ማቴ5፥12፤ ዕብ10፥36
5፥5 ቍ8፤ ዮሐ3፥16፤ሐሥ2፥33፤ ሮሜ310፥45፤ ፊል1፥20፤ቲቶ3፥5:6፤ ዕብ3፥6፤1ዮሐ3፥2:3፤
5፥6 ቍ8:10፤ ማር 1፥15፤ሮሜ4፥25፤ ኤፌ1፥10፤ገላ4፥4፤
5፥8 ዮሐ3፥16፤ 15፥13፤1ጴጥ3፥18፤ 1ዮሐ3፥16፤4፥10
5፥9 ሮሜ4፥25፤ 3፥25፤1፥18
5፥10 ቍ11፤ሮሜ8፥34፤11፥15፤11፥28፤2ቆሮ5፥18:19፤ ቈላ1፥20:21:22፤ዕብ7፥25
5፥11 ቍ10
5፥12 ቍ 14:15: 16:17፤18፤ ዘፍ2፥17፤3፥1-7፤1ቆሮ15፥21:22፤3፥19፤ሮሜ3፥9፤6፥23፤

[ʻ]5 1:2:3 *ወይም ሰላም ይኑረን፣ እናድርግ፣ እናድርግ*

ሳደረገው ነገር ይገኛል በማለት እግዚአብሔርን እንዲጠይቅ የሚያደርግ ሲሆን፣ እምነት ግን ለእግዚአብሔር ክብርን ይሰጣል::

4፥22 *ስለዚሁ* የአብርሃም እምነት በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ ሙሉ በሙሉ ያረፈ በመሆኑ፣ "ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት" ይላል::

4፥23 *ለእርሱ ብቻ አይደለም፤* አብርሃም በእምነቱ የተለ ማመደው ነገር በግል ሕይወቱ ላይ ተወስኖ የሚቀር ብቻ ሳይሆን፣ ሌላውንም የሚጠቅም ነው:: አብርሃም በእምነት መጽደቁ እውነት እንደ ሆነ ሁሉ፣ ሌላውም እንደዚሁ ነው:: በእምነት መጽደቅ ለእርሱ እውነት ከሆነ፣ ለሚያምን ሁሉ እውነት ነው::

4፥24 *ለእኛም ጭምር ነው፤* አብርሃም ለሙታን ሕይወትን በሚሰጥ በእግዚአብሔር በማመኑ እንደ ጸደቀ ሁሉ እኛም፣ "ጌታችን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው" በማመናችን እንጸድቃለን::

4፥25 *እኛን ጻድቅ አድርጎ ለማቅረብም ከሞት ተነሣ፤* የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት በእኛ ውስጥ ከሌለ በስተቀር ጽድቅ ሊኖረን አይችልም:: እነዚህ ቃላት ከግሪኩ ቅጅ የተወሰደውን የኢሳ 53፥12 ሐሳብ የሚያንጸባርቁ ናቸው::

5፥1 *ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም፤* የአእምሮ ሰላም ማግኘትን ብቻ ሳይሆን፣ በቅድሚያ ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ግንኙነት በመፍጠር ተጨባጭ በሆነ ደረጃ ላይ መገኘትን ያመለክታል፤ ይኸውም በፊት ጠላቶቹ ነበርን፤ አሁን ግን ወዳጆቹ ነን (5፥10፤ ኤፌ 2፥16፤ ቈላ 1፥21-22 ይመ)::

5፥2 *መግባት፤* ኢየሱስ፣ እግዚአብሔር ወዳለበት ይመራናል:: ሰውን ከእግዚአብሔር፣ እግዚአብሔርንም ከሰው ለይቶ የነበረው ወፍ ራሙ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ተወግዶአል፤ (የማቴ 27፥51 ማብ ይመ):: *የእግዚአብሔርንም ክብር ተስፋ፤* የክርስቲያን ትምክሕት የሆነው እግዚ አብሔር እርሱን የፈጠረበት ዐላማ በመጨረሻ ግልጽ ይሆናል::

5፥3 *በመከራችንም ሐሤት እናደርጋለን፤* ጳውሎስ፣ በመ ከራ ውስጥ ዐልፈን በምናገኘው ደስታ የሞላበት የአሸናፊነት ሕይወት ሐሤት እንድናደርግ እንጂ፣ መከራና ችግር የሞላበትን ሕይወት እንድንኖር መደገፉ አይደለም::

*5፥4፤* ክርስቲያን መከራ በሚደርስበት ጊዜ ሊደሰት ይችላል፤ ምክንያቱም በመከራ ውስጥ ማለፉ በከንቱ እንዳልሆነ ያውቃልና:: በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር ካሉት ዐላማዎች አንዱ፣ በልጆቹ ውስጥ የራሱ የሆነውን ባሕርይ መቅረጽ ነው::

5፥5 *ተስፋ ለዕፍረት አይዳርገንም፤* የክርስቲያን ተስፋ፣ ሁሉም ነገር ይሳካልኛል ከሚለው መሠረተ ቢስ አስተሳሰብ ጋር አንድ አይደለም:: ነገር ግን ወደ ፊት የሚጠብቀንን በረከት በትክክል የሚያረጋግጥ ሲሆን፣ ይህም በግልጽ በክርስቶስ ሞት በታየውና በመንፈስ ቅዱስ በተገለጸልን በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው:: ጳውሎስ፣ ከእምነት (ቍ1) ወደ ተስፋ (ቍ2፥4-5) ከዚያም ወደ ፍቅር (ቍ5፤ 1ቆሮ13፥13 እንዲሁም የ1ተሰ 1፥3 ማብ ይመ) ሲሸጋገር እናያለን:: *አፍስሶአልና፤* ግሱ ቀደም ሲል ከተፈጸመው ድርጊት የተገኘውን ውጤት ያመለክታል:: በመጀመሪያ በክርስቶስ ባመን ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍቅር በልባችን አፈሰሰ፤ ይህም ፍቅር በእኛ ውስጥ ዘወትር ይኖራል::

5፥6 *ጊዜው ሲደርስ፤* በእግዚአብሔር የመቤዠት ዕቅድ መሠረት ትክክለኛ የሆነውን ጊዜ ያመለክታል (ማር 1፥15፤ ገላ 4፥4):: *ክርስቶስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቶአልና::* የክርስቶስ ፍቅር በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የተመሠረተ ነው እንጂ፣ ሰው ከብቃቱ የተነሣ የተሰጠው አይደለም፤ በእርግጥ ክፉ ባሕርይ ቢኖረንም፣ አብዝቶ አፈሰሰው::

5፥7 *ለጻድቅ ... ለደግ ሰው፤* ክርስቶስ ስለ እኛ በሞተ ጊዜ፣ ጻድቅም ሆነ ደግ ሰው አልነበርንም፤ ነገር ግን ኀጢአተኞች ነበርን (ቍ 8፤ 3፥10-12 ይመ)::

5፥9 *በደሙ፤* ክርስቶስ ሕይወቱን መሥዋዕት አድርጎ በማ ቅረብ ስለ እኛ ኀጢአት መሞቱን የሚያመለክት ነው (3፥25 ይመ):: *ከእግዚአብሔር ቍጣ፤* "እንድናለን" በሚለው ግስ እንደ ተገለጸው የመጨረሻውን ፍርድ ያሳያል (ከ1ተሰ 1፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)::

5፥10 *የእግዚአብሔር ጠላቶች፤* ከኀጢአቱ የተነሣ ሰው የእግዚአብሔር ጠላት ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ግን የሰው ጠላት አይደለም:: ስለዚህ ዕርቅ ይፈጸም ዘንድ፣ ጠላትነት ከሰው መወገድ አለበት፤ እግዚአብሔር ቀድሞ እርምጃ በመውሰድ፣ በልጁ ሞት ይህ ሁኔታ እንዲለወጥ አድርጎአል (ቍ 11፤ ቈላ 1፥21-22 ይመ):: *ከታረቅን፤* መታረቅ፣ "ጠላትነትን ማስወገድ" ማለት ሲሆን፣ በቍ 9-10 እንደ ተጠቀሰው "መጽደቅ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ይኸውም፣ በቍ 9 "አሁን በደሙ ከጸደቅን ... እንዴት አንድንም!" ሲል በቍ 10 ደግሞ፣ "በልጁ ሞት ከእርሱ ጋር ከታረቅን ... መዳናችን እንዴት የላቀ አይሆንም!" ይላል:: *በሕይወቱማ መዳናችን፤* ከሞት የተነሣው ክርስቶስ ለሕዝቡ የሚሰጠውን ዘላለማዊ አገልግሎትና ሕይወት የሚያመለክት ነው (ዕብ 7፥25 ይመ):: ክርስቲያን ሕያው እምነት ይዞ ከሕያው ክርስቶስ ጋር አንድነቱን በማጠናከር መዳኑን ያጸናል:: የእግዚ አብሔር ጠላቶች ሳለን ከእርሱ ጋር ከታረቅን፣ ክርስቶስ ስለ እኛ በሕይወት ስለሚኖር መዳናችን የጸና ይሆናል::

5፥11 *አሁን ዕርቅን ባገኘንበት፤* ዕርቅም እንደ ጽድቅ (ቍ1) ክርስቶስን አምነው ለተቀበሉት ሁሉ ወዲያው የሚሰጥና ሐሤትም የሚያደርጉበት ነው::

*5፥12-21፤* ይህ ክፍል አዳምንና ክርስቶስን ያነጻጽራል::

ሰዎች ሁሉ መጣ፤ ምክንያቱም ሁሉም ኀጢ
አትን ሠርተዋል፤ 13ሕግ ከመሰጠቱ በፊት
ኀጢአት በዓለም ላይ ነበር፤ ነገር ግን ሕግ
በሌለበት ኀጢአት አይቈጠርም። 14ይሁን
እንጂ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ
ባሉት፣ እንደ አዳም ሕግን በመጣስ ኀጢ
አት ባልሠሩት ላይ እንኳ ሞት ነገሠ፤ አዳም
ይመጣ ዘንድ ላለው አምሳሉ ነበረ።
15ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን
አይደለም፤ በአንድ ሰው መተላለፍ ብዙዎቹ
ከሞቱ፣ የእግዚአብሔር ጸጋና በአንዱ ሰው፣ ይኸ
ውም በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የመጣው ስጦታ
ለብዙዎች እንዴት አብልጦ ይትረፈረፍ! 16ደግ
ሞም የእግዚአብሔር ስጦታ እንደ አንዱ ሰው
የኀጢአት ውጤት አይደለም፤ ምክንያቱም
ፍርዱ የአንድን ሰው ኀጢአት ተከትሎ ኵነኔን
አመጣ፤ ስጦታው ግን አያሌ መተላለፍን ተከ
ትሎ ጽድቅን አመጣ። 17በአንድ ሰው መተላለፍ
ምክንያት ሞት በዚህ ሰው በኩል የነገሠ
ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን የተትረፈረፈ ጸጋና
የጽድቅ ስጦታ የተቀበሉት፣ በአንዱ ሰው በኢ
የሱስ ክርስቶስ በኩል እንዴት አብልጠው በሕ
ይወት አይነግሡ!

5፥13 ሮሜ4፥15
5፥14 ዘፍ3፥11:12፤ 1ቆሮ15፥22:45
5፥15 ቊ12:18: 19፤ ሐሥ15፥11
5፥17 ቊ12፤ ዮሐ10፥10
5፥18 ቊ12፤ ኢሳ53፥11፤ ሮሜ4፥25፤
5፥19 ቊ12፤ ሮሜ3፥9፤ፊል2፥8
5፥20 ሮሜ3፥20፤ 6፥1፤7፥7:8፤ገላ3፥19፤ 1ጢሞ1፥13:14
5፥21 ቊ12:14 ማቴ25፥46፤ ሮሜ6:16፤3፥24፤
6፥1 ቊ15፤ ሮሜ3፥5:8፤8፥31፤
6፥2 ቊ 6:10:11: 18፤ሮሜ8፥13፤ ቈላ3፥5፤1ጴጥ 2፥24
6፥3 ማቴ28፥19
6፥4 ቊ6፤ ሐሥ 2፥24፤ ሮሜ 7፥6፤2ቆሮ 5፥17፤ኤፌ4፥22-24፤ ቈላ3፥10

18ከእንግዲህ በአንድ ሰው መተላለፍ የተ
ነሣ ኵነኔ በሁሉ ሰው ላይ እንደ መጣ፣ እንዲ
ሁም በአንዱ የጽድቅ ሥራ ለሰው ሁሉ ሕይ
ወትን የሚሰጥ ጽድቅ ተገኘ። 19በአንዱ ሰው
አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ፣
በአንዱ ሰው መታዘዝ ደግሞ ብዙዎች ጻድቃን
ይሆናሉ።
20ሕግ በመምጣቱ መተላለፍ በዛ፤ ነገር
ግን ኀጢአት በበዛበት ጸጋ አብልጦ የተት
ረፈረፈ ሆነ፤ 21ይህም የሆነው ኀጢአት በሞት
እንደ ነገሠ ሁሉ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
ደግሞ የዘላለም ሕይወት ይገኝ ዘንድ ጸጋ
በጽድቅ እንዲነግሥ ነው።

## ለኀጢአት መሞት፣ በክርስቶስ ሕያው መሆን

6 እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ
ኀጢአት እየሠራን እንኑር? 2ከቶ አይ
ሆንም፤ ለኀጢአት ሞተናል፤ ታዲያ እንዴት
አድርገን ከእንግዲህ በእርሱ እንኖራለን?
3ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንድንሆን
የተጠመቅን፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን
ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? 4ስለዚህ
ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደ ተነሣ፣

አዳም፣ ለኀጢአትና ለሞት ወደ ዓለም መምጣት ምክንያት ሆነ፤ ክርስቶስ ግን ጽድቅንና ሕይወትን አመጣ። በቍ 12 ላይ የተጀመረው ንጽጽር በቍ 18 ላይ የሚያበቃ ሲሆን፣ እነዚህ ሁለቱ ቍጥሮች የክፍሉን ማጠቃለያ ሐሳብ ይዘዋል። እስከ አሁን ድረስ ያለው የመጽሐፉ መልእክት እነዚህን ሁለት ሰዎች ምሳሌ በማድረግ ተጠቃሎ ቀርቦአል። አዳም፣ በኀጢአት ምክንያት በሰው ላይ ሊደርስ ያለውን ኵነኔ የሚያመለክት ሲሆን (1፥18-3፥20)፣ ክርስቶስ ግን ለክርስቲያኖች የተሰጠውን ጽድቅ ያመለክታል (3፥21-5፥11)።

5፥12 *ሞት*፤ ለኀጢአት የሚሰጥ ቅጣት ሲሆን፣ በመጨረሻ የሰውን ከእግዚአብሔር መለየት የሚያሳየውን መንፈሳዊ ሞት ያመለክታል። *ሁሉም ኀጢአትን ሠርተዋል*፤ የ3፥23ን ሐሳብ ለመድገም አይደለም፤ ነገር ግን የአዳም ኀጢአት በሰው ሁሉ ላይ ፍርድና (ቍ18-19) ሞት (ቍ15) እንዲደርስ ማድረጉን የሚያሳይ ክፍል ነው። ከኀጢአት ነጻ ሆነን መኖር የምንችል እንኳ ቢሆን፣ ሕይወትን አናገኝም፤ ነገር ግን ሕይወትን የምናገኘው በተፈጥሮአችን ኀጢአተኞች ሆነን ሳለን ነው (ዘፍ 8፥21፤ መዝ 51፥5፤ 58፥3፤ ኤፌ 2፥3 ይመ)።

5፥13 *ኀጢአት አይቈጠርም*፤ የሙሴ ሕግ በሌለበት ዘመን፣ ሰው ኀጢአት በመሥራት ማለትም ሕግን በመጣስ (ቍ 14) አይጠየቅም ነበር (4፥15 ይመ)፤ ይሁን እንጂ ሞት በዚያ ዘመን እንኳ እንደ ነገሠ ቈየ (ቍ 14)፤ ይህም ሞት ለኀጢአት የሚሰጥ ቅጣት ስለ ሆነ፣ በአዳምና በሙሴ መካከል ያሉ ሰዎችም የሌላ ሰው፣ ይኸውም የአዳምን ኀጢአት ተካፋዮች ሆኑ (የቍ 12 ማብ ይመ)።

5፥14 *አምሳሉ*፤ አዳም በኀጢአቱ፣ በሰው ዘር ሁሉ ላይ ጥፋትን አምጥቶአል፤ በዚህ ድርጊቱም፣ በጽድቅ ሥራው (ቍ 18) ለሰው ሁሉ በረከት ካመጣው ከሁለተኛው አዳም ከክርስቶስ ጋር ሲነጻጸር፣ የመጀመሪያው አዳም ሊባል ይችላል። ይህም በልዩነት ላይ ያተኰረ ንጽጽር ነው።

5፥15 *ብዙዎቹ*፤ "ሰዎች ሁሉ" (ቍ 12) ማለት ነው (ኢሳ 53፥11፤ ማር 10፥45 ይመ)። *አብልጦ*፤ በዚህ ክፍል ተደጋግሞ የተጠቀሰ መሪ ሐሳብ ነው። የአዳም ኀጢአት ካስከተለው ጥፋት ይልቅ፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ያስገኘው በረከት እጅግ አብዝቶ በልጦአል።

5፥16 *የእግዚአብሔር ስጦታ፤* ድነት ነው። *አያሌ መተላለፍን*፤ ከአዳም በኋላ ያለውን ትውልድ ሁሉ ኀጢአት የሚያመለክት ነው።

5፥17 *በሕይወት አይነግሡ፤* ወደፊት ክርስቲያኖች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብረው እንደሚነግሡ ያመለክታል (2ጢሞ 2፥12፤ ራእ 22፥5)።

5፥18 *ለሰው ሁሉ ሕይወትን*፤ ድነት ለሰው ሁሉ የተሰጠ ቢሆንም፣ ሰው ሁሉ በመጨረሻ ይድናል ማለት አይደለም። እያንዳንዱ ሰው ይድን ዘንድ፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ መቀበል አለበት (ቍ17 ይመ)።

5፥19 *ጻድቃን ይሆናሉ*፤ በእግዚአብሔር ፊት የሚኖራቸውን ቦታ ወይም ደረጃ (2ቆሮ 5፥21 ይመ) እንጂ፣ በባሕርይ ላይ የሚሆነውን ለውጥ የሚያሳይ አይደለም። የባሕርይን ለውጥ (የመቀደስን መሠረታዊ ትምህርት) በሚመለከት ከ6-8 ባሉት ምዕራፎች ተገልጾአል።

5፥20 *ሕግ በመምጣቱ*፤ የሰውን ልጅ ከኀጢአቱ ለመዋጀት ሳይሆን መዋጀት አስፈላጊ መሆኑን ለማመልከት ሕግ መጣ። ሕግ፣ ከእግዚአብሔር ቅድስና ጋር ሲነጻጸር ኀጢአት ምን እንደ ሆነ በግልጽ በማሳየት አብዝቶ ኀጢአት እንዲሆን አድርጓታል።

*6፥1-8፥39፤* እግዚአብሔር ለመዳናችንና ለጽድቃችን አስፈላጊ የሆነውን ነገር እንዴት እንዳዘጋጀ፤ ጳውሎስ በ3፥21-5፥21 ይገልጻል፤ ቀጥሎም የመቀደስን መሠረታዊ ትምህርት፣ ይኸውም ክርስቲያኖች በክርስቶስ ለማደግ የሚከተሉትን ሂደት በሦስት በመክፈል ያስረዳል፤ 1) ከኀጢአት ቀንበር ነጻ መሆን (ም 6)፣ 2) ከሕግ ፍርድ ነጻ መሆን (ም 7) እና 3) በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ሕይወትን ማግኘት (ም 8)።

6፥1 *ጸጋ እንዲበዛ ኀጢአት እየሠራን እንኑር?* ለዚህ ጥያቄ መነሻ የሆነው ጳውሎስ በ 5፥20 ላይ "ኀጢአት በበዛበት ጸጋ አብልጦ የተትረፈረፈ ሆነ" በማለት የተናገረው ነው። ይህ ጥያቄ የሥነ ምግባርን ሕግ በመቃወም ክርስቲያን በክርስቶስ ባገኘው የእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት ኀጢአት መሥራት ቢቀጥልም፣ አይፈረድበትም በማለት የሚያስተምረውንና ስለ ጸጋ የተዛባ አመለካከት ያለውን የእምነት ክፍል ይገልጻል። አንዳንዶች "ጽድቅ በእምነት ብቻ" የሚለውን የጳውሎስ ትምህርት ለሥነ ምግባር ግድ የለሽ ወደ መሆን ይመራል በማለት በግልጽ ተቃውመዋል።

6፥2 *ለኀጢአት ሞተናል*፤ በቍ3 ላይ እንደ ተገለጸው ያለፈውን ድርጊት የሚያመለክት ነው።

*6፥3-4፤* ክርስቲያን ለኀጢአት የሞተው መቼና እንዴት እንደ ሆነ ያሳያል። በአዲስ ኪዳን ዘመን አንድ ሰው በክርስቶስ እንዳመነ ወዲያው ይጠመቅ ስለ ነበር፣ ጥምቀትና በክርስቶስ ማመን የአንድ ድርጊት ጥምር ክፍሎች ተደርገው ይቈጠሩ ነበር (ሐሥ 2፥38 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር ዋና የእምነት ግንኙነት የምናደርግበት መንገድ ባይሆንም፣ ከእምነት ጋር የተሳሰረ ነው። ጥምቀት ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር በእምነት አንድ በሚሆንበት ጊዜ፣ የሚታየውን ውጤት በግልጽ ያሳያል፤ ይኸውም ከሥጋ በመወለድ ከአዳም ጋር አንድ እንደ ሆነ ሁሉ፣ በእምነትም በኩል ከክርስቶስ ጋር አንድ መሆናችንን ነው። በአባታችን በአዳም በኩል በኀጢአት እንደ ወደቅንና ሞትም የተገባን እንደ ሆን፣ አሁን ከክርስቶስ ጋር ሞተን፣ ከእርሱም ጋር እንድንነሣ ተደርገናል፤ ጥምቀትም ምሳሌ በመሆን ይህን ይገልጻል።

እኛም እንዲሁ በአዲስ ሕይወት እንድንኖር
በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር ተቀብረናል።
[5]በሞቱ ከእርሱ ጋር እንደዚህ ከተባበ
ርን፣ በትንሣኤው ደግሞ በእርግጥ ከእርሱ
ጋር እንተባበራለን። [6]ከእንግዲህ የኀጢአት
ባሮች እንዳንሆን፣ የኀጢአት ሰውነት እንዲ
ሻር[ሀ] አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ
ተሰቀለ እናውቃለን፤ [7]ምክንያቱም የሞተ
ከኀጢአት ነጻ ወጥቶአል።
[8]ከክርስቶስ ጋር ከሞትን፣ ከእርሱ ጋር
እንደምንኖር እናምናለን። [9]ክርስቶስ ከሙታን
ተነሥቶአልና፣ ዳግመኛ እንደማይሞት እናው
ቃለንና፤ ሞት ከእንግዲህ በእርሱ ላይ ጕልበት
አይኖረውም። [10]በሞተ ጊዜ፣ ለአንዴና ለመጨ
ረሻ ጊዜ ለኀጢአት ሞቶአል፤ ነገር ግን በሕ
ይወት መኖርን ለእግዚአብሔር ይኖራል።
[11]እንደዚሁም ለኀጢአት እንደ ሞታችሁ፣
ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ ለእግዚአብሔር ሕያ
ዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቍጠሩ። [12]ስለ
ዚህ ክፉ መሻቱን ትፈጽሙ ዘንድ በሚች
ሥጋችሁ ላይ ኀጢአት እንዲነግሥበት አታድ
ርጉ። [13]ብልቶቻችሁን የክፋት መሣሪያ
አድርጋችሁ ለኀጢአት አታቅርቡ፤ ይልቁንስ
ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገሩ ሰዎች
አድርጋችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤
ብልቶቻችሁንም የጽድቅ መሣሪያ አድርጋችሁ
ለእግዚአብሔር አቅርቡ። [14]ከጸጋ በታች እንጂ
ከሕግ በታች ስላልሆናችሁ፣ ኀጢአት አይገዛች
ሁምና።

### የጽድቅ ባሮች

[15]እንግዲህ ምን ይሁን? ከሕግ በታች ሳይ
ሆን፣ ከጸጋ በታች በመሆናችን ኀጢአት እንሥ
ራን? በጭራሽ አይገባም! [16]ራሳችሁን እንደ ባሪያ
አድርጋችሁ ስታቀርቡ፣ ለምትታዘዙት ለእርሱ፣
ይኸውም ወደ ሞት ለሚወስደው ለኀጢአት
ወይም ወደ ጽድቅ ለሚያደርሰው ለመታዘዝ
ባሮች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? [17]ነገር ግን
የኀጢአት ባሮች የነበራችሁ ቢሆንም፣ ለተሰጣ
ችሁለት ትምህርት በሙሉ ልብ የታዘዛችሁ
በመሆናችሁ፣ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፤
[18]ከኀጢአት ነጻ ወጥታችሁ፣ የጽድቅ ባሪያዎች
ሆናችኋል።
[19]በተፈጥሮ ደካሞች ስለ ሆናችሁ፣ በሰው
ቋንቋ ይህን እላለሁ፤ ብልቶቻችሁን በባርነት

6፥5 ቍ 4:8፤ ሮሜ 8፥11፤ 2ቆሮ 4፥10፤ ኤፌ 2፥6፤ ፊል 3፥10፡ 11፤ ቈላ 2፥12፤ 3፥1 2ጢሞ 2፥11
9፤ 5፥24፤ 6፥14፤
6፥7 ቍ 18
6፥8 ቍ 5
6፥9 ቍ 4፤ ሐሥ 2፥24፤ ራእ 1፥18
6፥10 ቍ 2፤ ዕብ 7፥27
6፥6 ቍ 2:3-8፤16፤ ሮሜ 7፥24፤ 2ቆሮ 4፥ 10፤ ገላ 2፥20፤ 5፥24፤ ኤፌ 4፥22፤ ፊል 3፥10፤ ቈላ 2፥12:20፤ 3፥3፤ 3፥
6፥11 ቍ 2
6፥12 ቍ 16
6፥13 ቍ 16:19፤ ሮሜ 7፥5፤ 12፥1፤ 2ቆሮ 5፥14:15፤ 1ጴጥ 2፥24
6፥14 ቍ 16፤ ሮሜ 2፥12፤ 3፥24
6፥15 ቍ 1:14
6፥16 ቍ 6:12: 14: 17:20:23፤ ዘፍ 4፥7፤ መዝ 51፥5፤ 119፥133፤ ዮሐ 8፥34፤ ሮሜ 5፥21፤ 7፥14: 23:25፤ 8፥2፤ 2ጴጥ 2፥19፤
6፥17 ቍ 16፤ ሮሜ 1፥8፤ 2ቆሮ 2፥14፤ 2ጢሞ 1፥13
6፥18 ቍ 2:7:22 16:22፤ ሮሜ 8፥2፤ 1ጴጥ 4፥1፤
6፥19 ቍ 13:22፤ ሮሜ 3፥5፤ ገላ 3፥15፤

[ሀ]6 *ወይም ኀይል እንዳይኖረው*

6፥4 *በጥምቀት ሞተን ከእርሱ ጋር ተቀብረናል፤* ከ5 እስከ 7 ባሉት ቍጥሮች ተብራርቶአል። *በአብ ክብር፤* በእግዚአብሔር ኀይል ማለት ነው። መለኮታዊ የሆነ እጅግ የላቀ የእግዚአብሔር መልካምነት፣ የእርሱም ፍጹምነት ማለት ነው። እያንዳንዱ ባሕርዩ የእርሱን ታላቅነት የሚገልጽ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ጽድቅ የክብሩ መግለጫ እንደ ሆነ ሁሉ (3፥23 ይመ)፣ ኀይሉም የእርሱ ክብር የሚገለጥበት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክብርና ኀይል ሳይነጣጠሉ በብዙ ቦታዎች ተጠቅሰዋል (መዝ 145፥11፤ ቈላ 1፥11፤ 1ጴጥ 4፥11፤ ራእ 1፥6፤ 4፥11፤ 5፥12-13፤ 7፥12፤ 19፥1 ይመ)። *በአዲስ ሕይወት እንድንኖር፤* ከ 8 እስከ 10 ባሉት ቍጥሮች ተብራርቶአል።

6፥6 *አሮጌው ሰዋችን፤* ድሮ የነበረን፣ ያልተለወጠው እኛነታችን ማለት ነው። *የኀጢአት ሰውነት፤* ክርስቲያን ከመሆናችን በፊት በኀጢአት ቍጥጥር ሥር የነበረውን እኔነት ያመለክታል። ይህም አሮጌው እኔነት እንደ ሰው ሆኖ የቀረበበት ምሳሌያዊ አገላለጽ ነው። ይህ "ሰውነት" ሊሞት የሚችል ነው። አሮጌው ሰው በክርስቲያን ላይ ኀይል እንዳይኖረው በመደረጉ፣ ለኀጢአት ባሪያዎች ሆነን እንድንገዛ ሊያደርገን አይችልም፤ ለማንሰራራት የሚያደርገው ሙከራም የሞቱን ሥቃይ ያበዛበታል።

6፥7 *የሞተ፤* ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ለኀጢአት በመሞቱ የኀጢአት ኀይል በእርሱ ላይ ሊሠለጥን አይችልም። *ከኀጢአት ነጻ ወጥቶአል፤* ከኀጢአት እስራትና ኀይል መላቀቁን ያመለክታል።

*6፥8፤* በክርስቶስ ሕይወት፣ ትንሣኤ ሞትን ተከትሎ እንደ መጣ ሁሉ፣ ከክርስቶስ ጋር የሞተ ክርስቲያንም አሁኑኑ ለተሻለና ለአዲስ ሕይወት አብሮት እንዲነሣ ተደርጎአል፣ ትንሣኤ ዳግመኛ ከመወለድና አዲስ ሕይወት ከማግኘት አንጻር ሲታይ፣ እውነተኛና የተረጋገጠ ነው፤ ይህም ዘወትር በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል።

6፥10 *ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለኀጢአት ሞቶአል፤* ክርስቶስ በኀጢአተኞች ፈንታ ለመሞት ራሱን አሳልፎ ሰጠ (5፥21)፤ በዚህም በኀጢአትና በሞት መካከል የነበረውን የፍርድ ግንኙነት አስወገደ፤ ከሞትም በመነሣት፣ አሁን እግዚአብሔርን ለማክበር ለዘላለም ይኖራል። *ለእግዚአብሔር፤* ለእግዚአብሔር ክብር ማለት ነው።

6፥11 *ራሳችሁን ቍጠሩ፤* ክርስቲያን በሕይወቱ ውስጥ በኀጢአት ላይ ድልን ለመቀዳጀት የሚያስችለው የመጀመሪያ እርምጃ ነው፤ ቀጣዮቹን እርምጃዎች በቍጥር 12 እና 13 ላይ ከተጻፈው ማንበብ ይመ። ለኀጢአት ሞቶ ለእግዚአብሔር ይኖራል፤ በዚህም እውነት እየተመራ በእምነት መኖር ይጠበቅበታል። *በክርስቶስ፤* ይህ ቃል በእያንዳንዱ የጳውሎስ መልእክት በተደጋጋሚ የገባ ሲሆን፣ በሮሜ መልእክት ግን ሲጠቀስ የመጀመሪያው ነው። እውነተኛ ክርስቲያኖች "በክርስቶስ" ናቸው፤ ምክንያቱም ከእርሱ ጋር ሞተው፣ ከእርሱ ጋር ለአዲስ ሕይወት ተነሥተዋልና።

*6፥12-13፤* ክርስቲያን አሁን ያለበት ሁኔታና ደረጃ ይኸውም ለኀጢአት መሞቱ (ቍ 5-7 ይመ) እና ለእግዚአብሔር መኖሩ (ቍ 8-10 ይመ) በተግባር እንዲገለጥ ጥሪ የሚያደርግ ክፍል ነው። ኀጢአትን ድል ለማድረግ ክርስቲያን መውሰድ ያለበት ሁለተኛው እርምጃ፣ ኀጢአት በሕይወቱ እንዳይነግሥ መከልከል ነው (ቍ 12)። ሦስተኛው እርምጃ ደግሞ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት ነው (ቍ 13)።

6፥13 *አቅርቡ፤* ራስን መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ የሚለውን ሐሳብ በመድገም፣ እግዚአብሔርን ለማገልገል ራሳችሁን ስጡ ማለቱ ነው። *ብልቶቻችሁንም፤* የተለያዩ የአካል ክፍሎችን በሙሉ ያመለክታል (ቍ 19)።

6፥14 *ኀጢአት አይገዛችሁምና፤* ጳውሎስ ኀጢአትን እንደ ሰው በመቈጣጠር ባሪያ አድርጎ ሊገዛ የሚችል ኀይል እንደ ሆነ ያስባል። *ከሕግ በታች ስላልሆናችሁ፤* ክርስቲያን ከሥነ ምግባር ሕግና ሥልጣን ሁሉ ነጻ ሆኖአል ማለት አይደለም፤ ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝብ ከነበሩበት የሕግ ባርነት ነጻ መውጣታቸውን ያመለክታል። ሕግ በኀጢአተኛው ላይ መፍረድ እንጂ፣ የኀጢአትን ኀይል ለመቋቋም የሚያስችል አይደለም፤ ጸጋ ግን ይህን ለማድረግ ያስችላል። *ከጸጋ በታች፤* በጸጋ እንዴት መመላለስ እንዳለብን ለመረዳት፣ ቲቶ 2፥11-12 ይመ።

*6፥15-23፤* እዚህ ላይ የተነሣው ጥያቄ፣ በእምነት ብቻ መጽደቅ የሚለውን ትምህርት መከተል፣ ጨርሶ የሥነ ምግባር ቍጥጥር እንዳይኖር ያደርጋል የሚል ፍርሀት ካላቸው ሰዎች የመጣ ይመስላል። ጳውሎስ እንደዚህ ዐይነቱን አመለካከት በመቃወም፣ ክርስቲያን ሥነ ምግባርን ከንቱ አድርጎ እንደማይቈጥር ያሳያል። በአንጻሩ ለኀጢአት ከመገዛት ይልቅ ለጽድቅ ተገዥ ሆኖአል።

*6፥16፤* በኀጢአትና በመታዘዝ መካከል ያለው ንጽጽር እንደሚጠቁመው፣ የኀጢአት ባሕርይ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ነው።

6፥17 *በሙሉ ልብ የታዘዛችሁ በመሆናችሁ፤* የክርስቲያን መታዘዝ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ እንጂ በማስገደድ ወይም በሕግ ተጽእኖ የሚደረግ አይደለም። *ለተሰጣችሁለት ትምህርት፤* በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለአዲስ አማኞች የተሰጡትን የክርስቶስ ግብረ ገባዊና ሥነ ምግባራዊ ትምህርቶች ሊያመለክት ይችላል።

6፥18 *የጽድቅ ባሪያዎች፤* ክርስቲያን የጌቶች ለውጥ አድርጎአል፤ ቀድሞ የኀጢአት ባሪያ የነበረ ሲሆን፣ አሁን ግን ፈቃደኛ አገልጋይ በመሆን ራሱን የጽድቅ ባሪያ አድርጎአል።

6፥19 *በሰው ቋንቋ ይህን እላለሁ፤* ሐሳቡን ለመግለጽ የተጠቀመበት የማነጻጸሪያ መንገድ በቂ ባለመሆኑ፣ ይቅርታ ለመጠየቅ

ለርኵሰትና እየባሰ ለሚሄድ ክፋት ታቀርቡ
እንደ ነበር፣ አሁን ደግሞ ወደ ቅድስና
ለሚወስደው ጽድቅ ባሪያ አድርጋችሁ አቅ
ርቡ፡፡ 20የኀጢአት ባሮች ሳላችሁ ከጽድቅ
ነጻ ነበራችሁ፡፡ 21አሁን ከምታፍሩበት ነገር
ያን ጊዜ ምን ጥቅም አገኛችሁ? የዚያ ነገር
ውጤት ሞት ነው፡፡ 22አሁን ግን ከኀጢአት
ነጻ ወጥታችሁ የእግዚአብሔር ባሮች ሆናችኋል፤
የምትሰበስቡትም ፍሬ ወደ ቅድስና ያመራል፤
መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው፡፡ 23የኀጢ
አት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር
ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ[ሸ]
የዘላለም ሕይወት ነው፡፡

## የጋብቻ ምሳሌ

7 ወንድሞች ሆይ፤ ሕግን ለሚያውቁ ሰዎች
እናገራለሁ፤ ሕግ በአንድ ሰው ላይ ሥልጣን
የሚኖረው፣ ሰውዬው በሕይወት እስካለ ድረስ
ብቻ መሆኑን አታውቁምን? 2አንዲት ያገባች
ሴት ከባሏ ጋር በሕግ የታሰረች የምትሆነው
እርሱ በሕይወት እስካለ ድረስ ነው፤ ባሏ
ቢሞት ግን ከጋብቻ ሕግ ነጻ ትሆናለች፡፡
3ነገር ግን ባሏ በሕይወት እያለ ሌላ ሰው ብታ
ገባ አመንዝራ ትባላለች፤ ባሏ ቢሞት ግን ሌላ
ሰው ብታገባም እንኳ፣ ከዚያ ሕግ ነጻ ትሆና
ለች፤ አመንዝራ አትባልም፡፡
4ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፤ እናንተም በክር
ስቶስ ኢየሱስ ሥጋ ለሕግ ሞታችኋል፤ ይህም
ከሙታን ለተነሣው ለእርሱ፣ ለሌላው ሆና
ችሁ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ ነው፡፡
5ኀጢአተኛ በሆነ ተፈጥሮ[*] ቊጥጥር ሥር
ሳለን፣ ለሞት ፍሬ እንድናፈራ በሕግ የተቀ
ሰቀሰው የኀጢአት መሻት በሥጋችን ላይ ይሠራ
ነበር፡፡ 6አሁን ግን ቀድሞ ጠፍሮ አስሮን ለነበ
ረው ሞተን፣ ከሕግ ነጻ ወጥተናል፤ ይህም
አሮጌ በሆነው በተጻፈው ሕግ ሳይሆን፣ አዲስ
በሆነው በመንፈስ መንገድ እንድናገለግል ነው፡፡

## ከኀጢአት ጋር መታገል

7እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ በራሱ ኀጢአት
ነውን? በፍጹም አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ
በኩል ባይሆን ኖሮ፣ ኀጢአት ምን እንደ
ሆነ ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ "አትመኝ" ባይል
ኖሮ፣ ምኞት ምን እንደ ሆነ በእርግጥ አላ
ውቅም ነበር፡፡ 8ኀጢአት ግን ትእዛዙ ባስገኘው
ዕድል ተጠቅሞ በእኔ ውስጥ ማንኛውንም
ዐይነት አጕል ምኞት አስነሣ፤ ኀጢአት
ያለ ሕግ ምዉት ነውና፡፡ 9ሕጉ ሳይኖር ሕያው
ነበርሁ፤ ትእዛዝ ከመጣ በኋላ ግን፣ ኀጢአት
ሕያው ሆነ፤ እኔም ሞትሁ፡፡ 10ለሕይወት
እንዲሆን የታሰበው ያ ትእዛዝም ሞትን
እንዳመጣ ተገነዘብሁ፤ 11ኀጢአት በትእዛዝ
በኩል የተገኘውን ዕድል በመጠቀም አታለለኝ፤
በትእዛዝም ገደለኝ፡፡ 12ስለዚህ ሕጉ በራሱ ቅዱስ
ነው፤ ትእዛዙም ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም
ነው፡፡

[ሸ]23 ወይም *በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል*
[*]5 ወይም *በሥጋ፤* እንዲሁም ቍ 25 ይመ

6፥20 ቍ16
6፥21 ቍ23
6፥22 ቍ18:19፤ ማቴ25፥46፤ ሮሜ7፥25፤1ቆሮ7፥22፤ ኤፌ6፥6፤1ጴጥ2፥16፤
6፥23 ቍ16:21፤ ዘፍ2፥17፤ምሳ10፥16፤ ሕዝ18፥4፤ማቴ25፥46፤ ሮሜ1፥32፤5፥12፤ 7፥5:13፤8፥6:13፤ ገላ6፥7:8፤ያዕ1፥15፤
7፥1 ሐሥ1፥16፤ 22፥5፤ሮሜ1፥13፤ 1ቆሮ1፥10፤5፥11፤ 6፥6፤14፥20:26፤ ገላ3፥15፤6፥18
7፥2 1ቆሮ7፥39
7፥3 ሉቃ16፥18
7፥4 ቍ6፤ሮሜ6፥6፤ 8፥2፤ገላ2፥19:20፤ 3፥23-25፤4፥31፤5፥1፤ ቈላ1፥22፤
7፥5 ሮሜ7፥7-11፤ 6፥13-23፤ገላ5፥24፤
7፥6 ቍ4፤ ሮሜ 2፥29፤2ቆሮ3፥6
7፥7 ቍ12፤ ዘፀ20፥17፤ዘዳ5፥21፤ ሮሜ4፥15፤8፥31፤
7፥8 ቍ11፤ ሮሜ4፥15
7፥10 ዘሌ18፥5፤ ሉቃ10፥26-28፤ ሮሜ10፥5፤ገላ3፥12
7፥11 ቍ8፤ዘፍ3፥13
7፥12 ቍ7:13: 14:16፤ሮሜ4፥15፤

የቀረበ አባባል ነው፡፡ "ባሪያ" የሚለውን ቃል በክርስቶስ ነጻ ለወጡት ክርስቲያኖች መጠቀም በተለምዶ አባባል ሲወሰድ ተስማሚ ላይሆን ይችላል፡፡

6፥22 *ከኀጢአት ነጻ ወጥታችሁ፤* የቍ 6 ማብ ይመ፡፡ *ቅድስና፤* ለእግዚአብሔር ባሪያ መሆን ቅድስናን ያስገኛል፤ የሂደቱም መጨረሻ የዘላለም ሕይወት ነው (ይህም አሁን እንደምንረዳው ሳይሆን ወደፊት ሊሆን ባለው በመጨረሻ ገጽታው ሲታይ ነው)፤ ያለ ቅድስና የዘላለም ሕይወት አይገኝም (ዕብ 12፥14 ይመ)፡፡ ማንኛውም የጸደቀ ሰው ለመጽደቁ፣ በሕይወቱ ውስጥ በሚታየው ቅድስና ያረጋግጣል፡፡ "ቅድስና"ን በተመለከተ የተጻፉትን ሌሎች ሐሳቦች ለመረዳት፣ ቍ19፤ 1ቆሮ 1፥30፤ 1ተሰ 4፥3-4:7፤ 2ተሰ 2፥13፤ 1ጢሞ 2፥15፤ ዕብ 12፥14፤ 1ጴጥ 1፥2 ይመ፡፡

*6፥23፤* በዚህ ክፍል ሁለት ዐይነት ባርነቶች ተነጻጽረው ልዩነታቸው ተመልክቷል፤ የአንደኛው ደመ ወዝ ሞት ሲሆን፣ የሌላው ግን የዘላለም ሕይወት ነው፤ የዘላለም ሕይወት እንደ ደመ ወዝ ወይም አንድ ሰው በይገባኛል የሚያገኘው ሳይሆን የእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ነው፡፡

7፥1 *ሕግ፤* ምናልባት ጳውሎስ ይህን የጠቀሰው የሙሴን ሕግ በማሰብ ሊሆን ይችላል፤ እዚህ ላይ ግን ትኵረቱ፣ መሠረታዊውን የሕግ ባሕርይ የሚመለከት ነው፡፡

*7፥2-3፤* እነዚህ ጥቅሶች በቍ 1 ላይ የተጻፈውን ሕግ ያብራራሉ፡፡ ሞት አንድ ሰው ከሕግ ጋር ያለውን ግንኙነት ፈጽሞ ይለውጣል፡፡

7፥4 *ስለዚሁ* እዚህ ላይ ጳውሎስ፣ በቍ 1፣ በቍ 2 እና 3 ላይ ከተብራራው ሕግ በመነሣት መደምደሚያ ሐሳብ ያቀርባል፡፡ *ለሕግ ሞታችኋል፤* በ6፥2-7 በተጠቀሰው መሠረት መሞቱ በተረጋገጠው ክርስቲያን ላይ ሕግ የመፍረድ ኀይል የለውም፡፡ እዚህ ላይ ለሕግ መሞቱን የሚያሳይ ሲሆን፣ በ 6፥2-7 ግን ለኀጢአት መሞቱን ይገልጻል፡፡ ይህም ከእንግዲህ በሕግ ቍጥጥር ሥር እንዳልሆነ ይስረዳል፡፡ *በክርስቶስ ኢየሱስ ሥጋ፤* የተሰቀለውን የክርስቶስን አካል ያመለክታል፡፡ *ለሌላው ሆናችሁ፤* ከሙታን የተነሣውን ክርስቶስ ማለት ነው (6፥5 ይመ)፡፡ የዚህ አንድነት ዐላማ፣ የቅድስናን ፍሬ ለማፍራት ነው፡፡

7፥5 *ኀጢአተኛ በሆነ ተፈጥሮ ቍጥጥር ሥር፤* ክርስቲያኖችን በሚመለከት፣ ያለፈውን ይኸውም ከዳግም መወለድ (ከሕይወት መለወጥ) በፊት የነበረውን ሁኔታ ያሳያል፡፡ *በሕግ የተቀሰቀሰው፤* ሕግ፣ ኀጢአትን መግለጽ ብቻ ሳይሆን፣ እንዲነሣሣም ያደርገዋል፤ ይህም በሰው ውስጥ ያለው ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ የተከለከለውን ነገር ለማግኘት የሚመኝ በመሆኑ ነው፡፡ *ለሞት፤* ሥጋዊ ሞት፣ ከዚያም ዐልፎ ከእግዚአብሔር ለዘላለም መለየት የሆነው መንፈሳዊ ሞት፣ ከሕግ ጋር "የመተባበራችን" ውጤቶች ነበሩ፡፡

7፥6 *ቀድሞ ጠፍሮ አስሮን ለነበረው፤* በቍ4 እና 6 ላይ እንደ ተጠቀሰው፣ ሕግን ያመለክታል፡፡ *ከሕግ ነጻ ወጥተናል፤* ሕግ ከሚያመጣው ፍርድ ማለት ነው፡፡ (የቍ 4 ማብ ይመ)፡፡ *አዲስ በሆነው በመንፈስ መንገድ፤* የ8፥4 ማብ ይመ፡፡ *አሮጌ በሆነው በተጻፈው ሕግ፤* በብሉይ ኪዳን ሕግ ሥር የነበረውን ሕይወት ያመለክታል፡፡

7፥7 *ሕግ በራሱ ኀጢአት ነውን?* ሕግን በሚመለከት በቍ 4-6 የተሰጠውን አስተያየት መነሻ በማድረግ የተጠየቀ ነው፡፡ *አላውቅም (እኔ)፤* ጳውሎስ የራሱን ስም ምትክ የሆነውን ተውላጠ ስም የተጠቀመ ይመስላል፤ እንዲሁም የሰውን ዘር በአጠቃላይ (ቍ 7-12) በተለይም ክርስቲያኖችን (ቍ 13-25) ወክሎ መናገሩ ነው፡፡ ኀጢአት ምን እንደ ሆነ ባላውቅሁም ነበር፤ ሕግ ኀጢአት መኖሩንና እርግጠኛ መሆኑን በመግለጥ ጠቃሚ የሆነ ተግባር አከናውኖአል፡፡

7፥8 *ትእዛዙ ባስገኘው ዕድል፤* የቍ 5 ማብ ይመ፡፡ *ኀጢአት ... ምዉት ነውና፤* ጨርሶ የለም ማለት ሳይሆን፣ መኖሩ ሙሉ በሙሉ ጕልቶ የማይታይ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡

7፥9 *ሕያው ነበርሁ፤* ጳውሎስ አሁን ካገኘው ጠቃሚ መረዳት አንጻር፣ የራሱን ልምምድ ይገመግማል፡፡ ሕጉ ሞት እንደ ፈረደበት ከማስተዋሉ በፊት ሕያው ነበረ፤ ይህም የሚመለከተው ስለ ሕጉ ሙሉ ኀላፊነት ከመውሰዱ በፊት ወይም የሕጉን እውነተኛ ጥንካሬ መረዳት የተቻለበትን የሕይወት ለውጥ ከማግኘቱ በፊት ያለውን ጊዜ ነው (ሉቃ 18፥20-21፤ ፊል 3፥6 ይመ)፡፡ *ትእዛዝ ከመጣ በኋላ፤* ጳውሎስ በሕጉ ፊት ኀጢአተኛ መሆኑን የተረዳበት፣ ማለትም በ13 ዓመት ዕድሜው ስለ ሕጉ ሙሉ ኀላፊነት የወሰደበት ጊዜ፣ ወይም የሕጉን ሙሉ ኀይል ለማስተዋል የቻለበት (የተለወጠበት) ጊዜ ነው፡፡ *ሞትሁ፤* ጳውሎስ ሞት እንደ ተፈረደበት ተረዳ፤ ምክንያቱም ሕግ ኀጢአትን ይገልጣል፤ የኀጢአትም ደመ ወዝ ሞት ነው (6፥23)፡፡

7፥10 *ለሕይወት እንዲሆን የታሰበው፤* ሕግ የተደነገገው ለሕይወት እንዲሆን ታስቦ ነበር፤ ከጳውሎስ የግል ልምድና ከሰው ልጅ ሕይወት እንደታየው ሕግ ለኀጢአት መግቢያ መንገድ ሆኖ ተገኘ፡፡ ሕጉ፣ ሕይወትን በመስጠት ፈንታ ፍርድን አመጣ፤ ቅድስናን በማስገኘት ፈንታ፣ ለኀጢአት መነሣሣት ምክንያት ሆነ፡፡

7፥12 *ሕጉ በራሱ ቅዱስ ነው፤* ኀጢአት ሕጉን ከተደነገገበት ዐላማ

[13]ታዲያ በጎ የሆነው ነገር ሞት ሆነብኝን?
ከቶ አይደለም፤ ነገር ግን ኀጢአት በኀጢአት
ነቱ ይታወቅ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር በኩል
ሞትን አመጣብኝ፤ ይኸውም ኀጢአት በትእ
ዛዝ በኩል ይብሱን ኀጢአት ይሆን ዘንድ
ነው::
[14]ሕጉ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለን፤
እኔ ግን ለኀጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥሁ ሥጋዊ
ነኝ:: [15]የማደርገውን አላውቅም፤ ለማድረግ
የምፈልገውን አላደርግም፤ ነገር ግን የምጠ
ላውን ያን አደርጋለሁና:: [16]ማድረግ የማል
ፈልገውን የማደርግ ከሆነ፣ ሕጉ በጎ እንደ
ሆነ እመሰክራለሁ፤ [17]እንዲህ ከሆነ፣ ይህን
የማደርገው እኔ ራሴ ሳልሆን፣ በእኔ ውስጥ
የሚኖረው ኀጢአት ነው:: [18]በእኔ፣ ማለትም
ኀጢአተኛ በሆነው ተፈጥሮዬ[ሀ] ውስጥ ምንም
በጎ ነገር እንደማይኖር ዐውቃለሁ፤ በጎ
የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ፤ ነገር
ግን ልፈጽመው አልችልም:: [19]የማደርገው
ሳደርገው የምፈልገውን በጎ ነገር አይደለም፤
ዳሩ ግን ለማድረግ የማልፈልገውን ክፉ ነገር
ነው:: [20]ላደርገው የማልፈልገውን ነገር የማ
ደርገው ከሆነ፣ ያን የማደርገው እኔ ራሴ ሳል
ሆን፣ የሚያደርገው በእኔ ውስጥ የሚኖረው
ኀጢአት ነው::

8፥4፤ገላ3፥21፤
1ጢሞ1፥8፤
7፥13 ቍ12፤
ሮሜ 6፥23፤
7፥14 1ነገ21፥20:
25፤2ነገ17፥17፤
ሮሜ6፥16፤1ቆሮ3፥1
7፥15 ቍ19፤
ገላ5፥17
7፥16 ቍ12
7፥17 ቍ20
7፥18 ቍ25፤
ገላ5፥ 24
7፥19 ቍ15
7፥20 ቍ17
7፥21 ቍ23:25
7፥22 መዝ1፥2፤
40፥8፤ኤፌ3፥16፤
7፥23 ሮሜ6፥16፤
ገላ5፥17፤1ጴጥ2፥11፤
ያዕ4፥1፤
7፥24 ሮሜ6፥6፤
8፥2
7፥25ሮሜ6፥16:22፤
2ቆሮ 2፥14፤
8፥1 ቍ34:39፤
ሮሜ16፥3
8፥2 ዮሐ8፥32:36፤
ሮሜ6፥16:18፤
7፥25፤1ቆሮ15፥45፤
7፥4
8፥3 ሮሜ7፥18:19፤
ፊል2፥7፤ገላ5፥24፤

[21]ስለዚህ ይህ ሕግ እየሠራ እንደ ሆነ ተረድ
ቻለሁ፤ ይኸውም በጎ ነገር ለመሥራት ስፈልግ፣
ክፉት ከእኔ ጋር አለ:: [22]በውስጤ በእግዚአብሔር
ሕግ ሐሤት አደርጋለሁ፤ [23]ነገር ግን በብልቶቼ
ውስጥ ለሚሠራው የኀጢአት ሕግ እኔን እስ
ረኛ በማድረግ፣ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋ
ሌላ ሕግ በብልቶቼ ውስጥ ሲሠራ አያለሁ::
[24]እኔ ምን ዐይነት ጐስቋላ ሰው ነኝ! ከዚህ
ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ሊያድነኝ ይችላል?
[25]በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ምስጋና
ለእግዚአብሔር ይሁን::
እንግዲያስ እኔ ራሴ በአእምሮዬ ለእግዚ
አብሔር ሕግ ባሪያ ስሆን፣ በኀጢአተኛ ተፈ
ጥሮዬ ግን ለኀጢአት ሕግ ባሪያ ነኝ::

## ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ

8 ስለዚህ በክርስቶስ ኢየሱስ[+] ያሉት አሁን
ኵነኔ የለባቸውም፤ [2]ምክንያቱም የሕ
ይወት መንፈስ ሕግ በክርስቶስ ኢየሱስ ከኀጢ
አትና ከሞት ሕግ ነጻ አውጥቶአችኋል::
[3]ሕግ ከሥጋ ባሕርይ[ǂ] የተነሣ ደክሞ ሊፈ
ጽም ያልቻለውን፣ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን

[ሀ]18 ወይም *ሥጋዬ*
[+]1 አንዳንድ የቅርብ ጊዜ ቅጆች *ስለዚህ እንደ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሳይሆን እንደ መንፈስ ፈቃድ በኖረው በክርስቶስ ኢየሱስ ይላሉ::*
[ǂ]3 ወይም *ኀጢአተኛ ተፈጥሮ*፤ እንዲሁም ቍ4:5:8:9:12:13 *ይመ*

ውጭ ለማይረባ ነገር ምክንያት አድርጎ ቢጠቀም በትም፣ ሕጉ ሊነቀፍ አይገባውም:: ሕጉ የእግዚአብሔር ስለ ሆነ በእርሱም ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካም ነው::

*7፥13-25፤* በዚህ ክፍል ጳውሎስ የሚገልጸው፣ ክርስቲያን ስለ ሆነ ወይም ስላልሆነ ሰው መሆኑን ለይቶ ለማወቅ ለብዙ መቶ አመታት ያህል ቤተ ክርስቲያንን አከራክሮአል፤ ክርስቲያን ስላልሆነ ሰው እንደሚናገር በመደገፍ የቀረቡ ምክንያቶችም፤ 1) ‘ለኀጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥሁ’ (ቍ14)፣ ‘በእኔ ውስጥ በጎ ነገር እንደማይኖር ዐውቃለሁ’ (ቍ18) እንዲሁም ‘ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ’ (ቍ24) የሚሉትን መጠቀሙ፣ ክርስቲያን የሆነውን ሰው ሕይወት ለመግለጽ አይመስልም፤ 2) በሌላ መልኩ ደግሞ ምዕራፍ 7 እና 8 ሲነጻጸሩ፣ በክፍሉ ውስጥ የተጠቀሰው ሐሳብ ከክርስትና ውጪ ያለ ሰውን የሚመለከት ነው ብሎ ለማመን አስቸጋሪ ይሆናል:: 3) ክርስትና መንፈሳዊ ጕስቍልናን የሚያስከትል ከሆነ አንድ ሰው ክርስቲያን ለመሆን ያለው ፍላጎት ይቀንሳል፤ በአንጻሩም፣ ጳውሎስ በዚህ ክፍል ክርስቲያን ስለ ሆነ ሰው ሕይወት ይገልጻል የሚለውን ሐሳብ የሚደግፉ ሰዎች ቀጥሎ ያሉትን ምክንያቶች ያቀርባሉ፤ 1) በክፍሉ የተጠቀሱት ዐረፍተ ነገሮች ሁሉ የአሁን ጊዜ ድርጊት አፈጻጸም ስዋስው በመጠቀም በመጻፋቸው፣ 2) ጳውሎስ ስለ ራሱ ያለው ዝቅ ያለ አመለካከት (ቍ18)፣ 3) ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ሕግ ከፍተኛ ግምት መስጠቱ (ቍ14-16)፣ 4) ይህ ጽሑፍ በሮሜ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጠው ሥፍራ ጳውሎስ ስለ መቀደስ፣ ማለትም የአንድ ክርስቲያን በቅድስና ማደግ ምን መምሰል እንዳለበት በሚናገርበት ክፍል መሆኑ ናቸው::

*7፥13፤* ኀጢአት ቅዱስ የሆነውን የእግዚአሔር ሕግ ለዘለ ቄታው ቅዱስ ሳልሆን፣ ማለትም ለሞት ተጠቀመበት፤ በዚህም ሁኔታ፣ አስነዋሪ የሆነው የኀጢአት ባሕርይ ተገልጦአል::

7፥14 ***መንፈሳዊ***፤ ሕጉ የመነጨው ከእግዚአብሔር ነው:: ***እኔ ... ነኝ!*** አንደኛ መደብ ተውላጠ ስምና ግሡ አንድ ላይ ሲታዩ ጳውሎስ፣ አሁን ስላለው የክርስትና ሕይወቱ ሁኔታ የሚገልጽ መሆኑን ይጠቁማሉ:: ***ሥጋዊ ነኝ!*** ክርስቲያን የሆነ ሰው እንኳ፣ በልቡ ውስጥ የዐመፅ ቅሪት ሊኖርበት ይችላል:: ***ለኀጢአት እንደ ባሪያ የተሸጥሁ***፤ አገላለጹ ጠንከር ያለ በመሆኑ፣ ብዙዎች የክርስቲያንን ሕይወት እንደሚገልጽ አድርገው አይቀበሉትም:: ይሁን እንጂ በወንጌል ላይ የተገለጸውን ፍጹም የሆነውን ሥነምግባር ክርስቲያን እንኳ ሊመላለስበት እንዳልቻለ በግልጽ ያመለክታል፤ ኀጢአትም ሳይቋረጥ ክርስቲያንን የመፈታተን ባሕርይ እንዳለው ያሳያል::

7፥15 ***የማደርገውን አላውቅም***፤ በውስጡ የተፈጠረው ትግል በአንጻሩ፣ የሐሳብ መዘባረቅና ውጥረት አስከትሎበታል::

7፥16 ***ሕጉ በጎ እንደ ሆነ እመሰክራለሁ!*** በመሠረቱ ሕግ በጎ እንደ ሆነ ለጳውሎስም ሆነ ለሌሎች ክርስቲያኖች የሚገልጸው መንፈስ ቅዱስ ነው::

7፥17 ***ይህን የማደርገው እኔ ራሴ ሳልሆን***፤ ኀጢአት በክርስቲያን ሕይወት ላይ ያለውን የመቈጣጠር ኀይል ለማሳየት እንጂ ከሥነምግባራዊ ኀላፊነት ለማምለጥ የተነገረ አይደለም::

7፥18 ***በእኔ ... ውስጥ ምንም በጎ ነገር እንደማይኖር***፤ የዐረፍተ ነገሩ የመጨረሻ ሐረግ እንደሚያመለክተው፣ ይህ ሐሳብ በኀጢአት ስለ ወደቀ ሰው ባሕርይ ይናገራል:: ጳውሎስ በጎ የሆነ ነገር በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ፈጽሞ የለም ማለቱ አይደለም::

7፥20 ***ያን ... የሚያደርገው ... ኀጢአት ነው***፤ የቍ 17 ማብ ይመ::

7፥21 ***ሕግ***፤ እዚህ ላይ ሕግ ሲባል *መመሪያ* ማለት ነው::

7፥22 ***በእግዚአብሔር ሕግ ሐሤት አደርጋለሁ!*** በሙሴ ሕግ ወይም በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ሕግ ማለት ነው:: ክርስቲያን ካልሆነ ሰው እንዲህ ዐይነት ሐሳብ መጠበቅ አስቸጋሪ ነው::

7፥23 ***ሌላ ሕግ***፤ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር ሕግ እንዳይታዘዝ የሚያደርገውን የውስጥ ኀይል ያመለክታል:: ከአእምሮዬ ሕግ ጋር፤ ለእግዚአብሔር ሕግ ለመታዘዝ ያለውን ፍላጎት ያመለክታል:: ***የኀጢአት ሕግ!*** ቀደም ሲል ሌላ ሕግ ተብሎ ከተጠቀሰው ጋር ይመሳሰላል::

7፥24 ***ለሞት ከተሰጠ ሰውነት***፤ እንደ ሬሳ በመጋደም በውስጥ ሆኖ ነጻነትን የሚከለክለውን ኀጢአተኛ ሥጋ ያመለክታል (6፥6)::

*7፥25፤* በዚህ ጥቅስ የተገለጸው ሐሳብ ከኀጢአት ነጻ መሆን የሚቻለው ሕግን ለመጠበቅ በሚደረገው ጥረት ሳይሆን፣ በክርስቶስ መሆኑን በማሳየት በቍ24 ላይ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ይሰጣል:: ***እኔ ራሴ!*** በእግዚአብሔር ሕግ የሚደሰተውን (ቍ22) የውስጥ ማንነት ያመለክታል::

8፥1 ***ኵነኔ!*** ሕጉ ኵነኔን ያመጣል፤ ምክንያቱም ኀጢአትን ለይቶ ያመለክታል፤ ይቀሰቅሳል፤ በኀጢአትም ላይ ይፈርዳል:: ይሁን እንጂ ክርስቲያን “ከሕግ በታች” አይደለም (6፥14):: ***በክርስቶስ ኢየሱስ***፤ በ 6፥1-10 እንደ ተገለጸው ከእርሱ ጋር አንድ መሆንና መተባበር ማለት ነው፤ (በተጨማሪም የ6፥11 ማብ ይመ)::

8፥2 ***የሕይወት መንፈስ ሕግ***፤ ሕይወት ሰጪ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን የመቈጣጠር ኀይል ያመለክታል:: ጳውሎስ በሮሜ መልእክት ላይ “ሕግ” የሚለውን ቃል በተለያየ መንገድ አውሎት ይገኛል፤ ይኸውም እዚህ ላይ እንደ ተጠቀሰው የሚቈጣጠር ኀይል፣ የእግዚአብሔር ሕግ (2፥17-20፤ 9፥31፤ 10፥3-5)፣ አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት (3፥21) ብሉይ ኪዳን በሙሉ (3፥19)፣ *መመሪያ* ሕግ (3፥27) ለማለት ነው:: ***ከኀጢአትና ከሞት ሕግ!*** በመጨረሻ ሞትን የሚያስከትለውን፣ ሕይወትን የሚቈጣጠረውን ኀጢአት ያመለክታል::

8፥3 ***ደክሞ ሊፈጽም ያልቻለውን***፤ ሕጉ ኀጢአትን ለማሸነፍ አልቻለም፤ ኀጢአትን ለይቶ ሊያመለክት፣ በእርሱም ላይ

በኀጢአተኛ ሰው አምሳል፣ የኀጢአት መሥዋ
ዕት[ገ] እንዲሆን በመላክ ፈጸመው፤ በዚህም
ኀጢአትን በሥጋ[ነ] ኰነነ፤ [4]ይኸውም በሥጋ
ሳይሆን በመንፈስ በምን መላለስ በእኛ፣ ሕጉ
የሚጠይቀው ጽድቅ ሙሉ በሙሉ እንዲፈ
ጸም ነው።
[5]እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ልባቸውን
በሥጋ ፍላጎት ላይ ያሳርፋሉ፤ እንደ መንፈስ
ፈቃድ የሚኖሩ ግን ልባቸውን በመንፈስ
ፍላጎት ላይ ያደርጋሉ። [6]የሥጋን ነገር ማሰብ[ፐ]
ሞት ነው፤ የመንፈስን ነገር ማሰብ ግን ሕይ
ወትና ሰላም ነው። [7]ለኀጢአት የተገዛ አእምሮ[ኣ]
ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤ ለእግዚአብሔር ሕግ
አይገዛም፤ መገዛትም አይችልም። [8]በሥጋ ፈቃድ
የሚመሩትም እግዚአብሔርን ማስደሰት አይች
ሉም።
[9]እናንተ ግን፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስ
ጣችሁ የሚኖር ከሆነ፣ በሥጋ ሳይሆን በመ
ንፈስ ናችሁ። ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌ
ለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም። [10]ነገር
ግን ክርስቶስ በውስጣችሁ ካለ፣ ሰውነታችሁ
ከኀጢአት የተነሣ ሟች ሲሆን፣ መንፈሳችሁ ግን
ከጽድቅ የተነሣ ሕያው ነው። [11]ኢየሱስን ከሙ
ታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ
የሚኖር ከሆነ፣ ክርስቶስን ከሙታን ያስነ
ሣው፣ በውስጣችሁ በሚኖረው በመንፈሱ
ሟች ለሆነው ሰውነታችሁ ሕይወትን ይሰጣል።
[12]ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ግዴታ አለብን፤
ይሁን እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ እንድንኖር
ለሥጋ አይደለም። [13]እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ
ትሞታላችሁና፤ ክፉ የሆነውን የሥጋ ሥራ
በመንፈስ ብትገድሉ ግን፣ በሕይወት ትኖራ
ላችሁ፤ [14]በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ
የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና። [15]እንደ ገና የፍር
ሀት ባሪያ የሚያደርጋችሁን መንፈስ ሳይሆን፣
"አባ[ከ]፣ አባት" ብለን የምንጠራበትን የልጅ
ነት[ኸ] መንፈስ ተቀብላችኋልና፤ [16]የእግዚአብሔር
ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈ
ሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል። [17]ልጆች ከሆን
ወራሾች ደግሞ ነን፤ የክብሩ ተካፋዮች እንሆን
ዘንድ በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፣
የእግዚአብሔር ወራሾች፣ ከክርስቶስ ጋር አብረን
ወራሾች ነን።

## የሚመጣው ክብር

[18]የአሁኑ ዘመን ሥቃያችን ወደ ፊት ሊገ
ለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር
ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ።

ዕብ2፥14:17፤7፥18፤ 10፥1-4
8፥4 ሮሜ2፥26፤ ገላ5፥16
8፥5 ገላ5፥19-21: 22-25
8፥6 ቍ13፤ ሮሜ6፥23፤ገላ6፥8
8፥7 ያዕ4፥4
8፥8 ገላ5፥24
8፥9 ቍ11፤ ዮሐ14፥17፤ ሐሥ16፥7፤ 1ቆሮ6፥19፤ገላ5፥24፤ 2ጢሞ1፥14፤ 1ዮሐ 4፥13
8፥10 ቍ9፤ ዘፀ29፥45፤ዮሐ14፥20: 23፤2ቆሮ13፥5፤ ገላ2፥20፤ኤፌ3፥17፤ ቈላ1፥27፤ራእ3፥20
8፥11 ዮሐ5፥21፤ ሐሥ2፥24፤ሮሜ6፥5
8፥12 ቍ4፤ ገላ5፥24
8፥13 ቍ6፤ ሮሜ6፥23፤6፥21፤ ገላ6፥8
8፥14 ቍ19፤ ሆሴ1፥10፤ሚል3፥17፤ ማቴ5፥9፤ዮሐ1፥12፤ ገላ5፥18፤ገላ3፥26፤ 4፥5፤ኤፌ1፥5፤ ራእ 21፥7
8፥15 ማር14፥36፤ ዮሐ20፥22፤ገላ4፥5:6፤ 2ጢሞ 1፥7፤
8፥16 ቍ14፤ዮሐ1፥12፤ 2ቆሮ 1፥22፤ኤፌ1፥13
8፥17 ሐሥ20፥32፤2ቆሮ1፥5፤ገላ3፥29፤4፥7፤ኤፌ3፥6፤ቲቶ3፥7፤ 2ጢሞ 2፥12፤ 1ጴጥ 4፥13 8፥18 2ቆሮ4፥17፤1ጴጥ4፥13፤5፥1

[ገ]3 *ወይም ስለ ኀጢአት መሥዋዕት*
[ነ]3 *ወይም በኀጢአተኛ ሰው*
[ፐ]6 *ወይም ስለ ሥጋ ማሰብ*
[ኣ]7 *ወይም ስለ ሥጋ የሚያስብ አእምሮ*
[ከ]15 በአራማይክ ቋንቋ አባት የሚጠራበት ስም ነው
[ኸ]15 *ወይም እንደ ልጅ*

ሊፈርድ፣ ሊያነሣሣውም እንኳ ይችላል፤ ነገር ግን ፈጽሞ ሊያስወግደው አልቻለም። *በኀጢአተኛ ሰው አምሳል፤* ክርስቶስ በሰው አምሳል ሲመጣ ፈጽሞ ኀጢአት የሌለው ከመሆኑ በቀር ፍጹም ሰው ሆኖአል። *በኀጢአተኛ ሰው፤* "ሥጋ" የሚለው ቃል የሰውን ሥጋ ወይም የክርስቶስን ሊያመለክት ይችላል፤ የቃሉ ትርጕም የኋለኛው ከሆነም፣ እግዚአብሔር ኀጢአት በሌለበት በክርስቶስ ሰብአዊ ተፈጥሮ ላይ ኀጢአትን የኰነነበትን ሁኔታ ይገልጻል፤ ይህም ትርጕም ከጳውሎስ ትምህርት ጋር በበለጠ ይስማማል።

8፥4 *ሕጉ የሚጠይቀው ጽድቅ፤* ሕጉ አሁንም በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ነው፤ ይኸውም ድነት የማግኛ መንገድ ሳይሆን፣ የሥነ ምግባር መመሪያ በመሆኑ ነው፤ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለውም ከእግዚአብሔር ፍቅርና መንፈስ ቅዱስ ከሚሰጠው ኀይል የተነሣ ነው። ይህም በኤርምያስ 31፥33-34 የተጻፈው የአዲሱ ኪዳን ትንቢት ፍጻሜ ነው። *እንዲፈጸም፤* ቀጥተኛ ትርጕሙ እንዲጠበቅ ማለት ነው። እግዚአብሔር ልጁን የላከበት ዐላማው ክርስቲያኖች የሕጉን ትክክለኛና ሙሉ ሐሳብ በሕይወታቸው እንዲገልጹ ለማስቻል ነው። *በመንፈስ፤* ሕጉ የሚጠይቀው ጽድቅ እንዴት ሊፈጸም ይችላል? ኀጢአተኛ የሆነው ሥጋ እንዲሠለጥን በማድረግ ሳይሆን፣ መሪ ለሆነውና ኀይልን ለሚሰጠው ለመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ራስን አሳልፎ በመስጠት ሊፈጸም ይችላል።

*8፥5-8፤* በዚህ ክፍል ሁለት ዐይነት የልብ ፈቃዶች ተገልጸዋል፤ እነዚህም የኀጢአተኛ ሥጋ ፈቃድና የመንፈስ ፈቃድ ናቸው። የመጀመሪያው ወደ ሞት የሚመራ ሲሆን፣ ሁለተኛው ወደ ሕይወትና ወደ ሰላም ይመራል። ኀጢአተኛ ተፈጥሮ ከሞት ጋር የተቈራኘ (ቍ6)፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚጣላ (ቍ7) ለእግዚአብሔር የማይገዛና (ቍ7) በእርሱም ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ተፈጥሮ ነው (ቍ8)።

8፥10 *ሥጋችሁ ከኀጢአት የተነሣ ሟች ሲሆን፤* የክርስቲያን ሥጋ እንኳ ከኀጢአት የተነሣ ሥጋዊ ሞት የማይቀርለት ሆኖአል። *መንፈሳችሁ ... ሕያው ነው፤* "መንፈስ ሕይወት ነው" ማለት ነው (ቍ 2 ይመ)። በዚህ ክፍል "ሥጋ" የሚለውን ቃል የምንረዳው 7፥24 ላይ በተገለጸው መሠረት ነው። *ከጽድቅ የተነሣ፤* የክርስቲያን መንፈስ ከመጽደቁ የተነሣ በሥጋው ላይ የደረሰው ሞት አይሠለጥንበትም። ክርስቲያን ካገኘው ጽድቅ የተነሣ ሕይወት ሰጪ የሆነው መንፈስ ያድርበታል።

*8፥11፤* በክርስቶስ ትንሣኤና በክርስቲያኖች ትንሣኤ መካከል ስላለው የቀረበ ትስስር 1ቆሮ 6፥14፤ 15፥20:23፤ 2ቆሮ 4፥14፤ ፊል 3፥21፤ 1ተሰ 4፥14 ይመ። *ሟች ለሆነው ሰውነታችሁ ሕይወትን ይሰጣል፤* ትንሣኤያችንን፣ በውስጣችን የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ያረጋግጥልናል፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ መኖር መቻላችን፣ መንፈስ ቅዱስ በውጣችን ለመኖሩ ማረጋገጫ ነው (ቍ 4-9)፤ መንፈስ ቅዱስ ትንሣኤያችን አሁን በሕይወት እያለን እንኳ እውን እንደ ሆነ ለልባችን ያረጋግጣል።

8፥14 *የእግዚአብሔር ልጆች፤* እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ በመሆኑ፣ ሁሉን በመቻሩና ለሁሉ የሚያስፈልገውን ነገር በመስጠቱ "የሁሉ አባት ነው" የተባለው ከዚህ የተነሣ ነው (ማቴ 5፥45 ይመ)። ይሁን እንጂ ሰዎች ሁሉ የእርሱ ልጆች አይደሉም፤ ኢየሱስ በዚህ ምድር ሳለ ለነበሩት ያላመኑ አይሁድ "እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ" ብሎአልና (ዮሐ 8፥44)። ሰዎች በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ በማመን፣ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ (ዮሐ 1፥12-13 ይመ)፤ በእግዚአብሔር መንፈስ መመራታቸውም የዚህ ግንኙነት ማረጋገጫ ነው።

8፥15 *ልጅነት፤* የልጅነት መብት በመስጠት ቤተ ሰብ ማድረግ ማለት ነው። ይህም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተለያዩ አራት ቦታዎች ተጠቅሶአል (ቍ 23፤ 9፥4፤ ገላ 4፥5 የዚህኑ ማብ ይመ፤ ኤፌ 1፥5 )። ከአብራክ ያልተገኘን ልጅ እንደ ራስ ልጅ አድርጎ ማሳደግና ሀብት የመውረስ መብቱ እንዲጠበቅለት ማድረግ፣ በግሪኮችና በሮማውያን ዘንድ የተለመደ ነበር። ክርስቲያኖችም የልጅነትን መብት ያገኙት በጸጋ ነው። ክርስቶስ ግን የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ነው። *አባ፣ አባት፤* ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ልዩ የሆነ ኅብረት ያመለክታል።

8፥16 *ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ... ይመሰክርልናል፤* መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ሆኖ ከክርስቶስ ጋር ያለንን አንድነት ይመሰክርልናል። *የእግዚአብሔር ልጆች፤* እግዚአብሔር እንደ አንድ ልጁ አድርጎ እኛን እንደሚወደን ያሳያል (ዮሐ 17፥23)፤ መንፈስ ቅዱስም በውስጣችን "አባ፣ አባት" ብለን የምንጮኸበት ፍቅርና እምነት ሰጥቶናል (8፥15 ይመ)።

8፥17 *ወራሾች፤* ከእግዚአብሔር የተጠበቀላቸውን በረከት በከፊል መውረስ የጀመሩትን ያመለክታል። *ከክርስቶስ ጋር ... ወራሾች፤* ያለ ጥርጥር ሁሉም ነገር የክርስቶስ ነው፤ ነገር ግን የእርሱ ከሆነው በጸጋ እንካፈላለን። *በእርግጥ የመከራው ተካፋዮች ብንሆን፤* እዚህ ላይ የተጻፈው የግሪኩ አገባብ የሚገልጸው እውነታን እንጂ ክብሩን ለማግኘት ልናሟላ የሚገባንን ቅድመ

19ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ
በናፍቆት ይጠባበቃል:: 20ፍጥረት ሁሉ ለከን
ቱነት ተዳርጎአል፤ ይኸውም በራሱ ምርጫ
ሳይሆን፣ ለተስፋ እንዲገዛ ካደረገው ከፈቃዱ
የተነሣ ነው::* 21ይህም ፍጥረት ራሱ ከመበ
ስበስ ባርነት ነጻ ወጥቶ በእግዚአብሔር ልጆች
ወደ ሆነው ወደ ክበረው ነጻነት እንዲደርስ
ነው::

22እስከ አሁን ድረስ ፍጥረት ሁሉ በምጥ
ጊዜ እንዳለው ሥቃይ በመቃተት ላይ እንደ
ሚገኝ እናውቃለን:: 23እርሱ ብቻ ሳይሆን፣
የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ ያገኘን እኛ
ራሳችን የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነ
ታችንን በናፍቆት እየተጠባበቅን በውስጣችን
እንቃትታለን:: 24በዚህ ተስፋ ድነናል፤ ተስፋው
የሚታይ ከሆነ ግን ተስፋ አይደለም፤ የሚ
ያየውንማ ማን ተስፋ ያደርገዋል? 25ነገር ግን
ገና ያላየነውን ተስፋ ብናደርግ፣ በትዕግሥት
እንጠብቀዋለን::

26እንዲሁም ደግሞ መንፈስ በድካማችን
ያግዘናል፤ እንዴት መጸለይ እንደሚገባን
አናውቅም፤ መንፈስ ግን በቃላት ሊገለጥ
በማይችል መቃተት ለእኛ ይማልድልናል::
27ልባችንንም የሚመረምረው እርሱ የመን
ፈስን ሐሳብ ያውቃል፤ ምክንያቱም መንፈስ
እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለቅዱሳን ይማል
ዳልና::

8፥19 ቆላ1፥14
8፥20 ዘፍ3፥17-19፤
5፥29
8፥21 የሐ1፥12፤
ሐሥ3፥21፤
2ጴጥ3፥13፤ራእ21፥1፤
8፥22 ኤር12፥4
8፥23 ቆላ11፤19፤
2ቆሮ5፥2:4:5፤
ገላ 5፥5፤ፊል3፥21
8፥24 2ቆሮ4፥18፤
1ተሰ5፥8፤ቲቶ3፥7፤
8፥25 መዝ37፥7
8፥26 ቆላ15:16፤
ኤፌ6፥18
8፥27 ቆላ34፤
ራእ2፥23፤
8፥28 ቆላ30፤
ዘፍ50፥20፤
ኢሳ38፥17፤
ኤር29፥11፤
ሮሜ11፥29፤
1ቆሮ1፥9፤ገላ1፥6:
15፤ኤፌ1፥11፤
4፥1:4፤2ተሰ2፥12፤
2ጢሞ1፥9፤
ዕብ6፥17፤9፥15፤
1ጴጥ2፥9፤
2ጴጥ1፥10፤3፥11፤
8፥29 ሮሜ11፥2፤
1ቆሮ15፥49፤
2ቆሮ3፥18፤ኤፌ1፥5:
11፤ፊል3፥21፤
ቈላ1፥18፤1ጴጥ1፥2፤
1ዮሐ3፥2፤

## ከአሸናፊዎች በላይ

28እግዚአብሔር፣ ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ
ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲ
ሠራ እንደሚያደርግላቸው° እናውቃለን::"
29እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን
መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤
ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ
በኵር እንዲሆን ነው:: 30አስቀድሞ የወሰ
ናቸውን ጠራቸው፤ የጠራቸውን አጸደቃቸው፤
ያጸደቃቸውን አከበራቸው::

31ታዲያ ለዚህ ምን እንመልሳለን? እግዚ
አብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፣ ማን ሊቃወመን
ይችላል? 32ለገዛ ልጁ ያልሳሳለት፣ ነገር ግን
ለሁላችንም አሳልፎ የሰጠው እርሱ፣ ሁሉንስ
ነገር ከእርሱ ጋር እንደ ምን በልግስና አይሰጠን?
33እግዚአብሔር የመረጣቸውን የሚከስ ማን ነው?

*20:21 ወይም *በተስፋ አስገዝቶታል::*
°28 ወይም *በጎ የሆነውን ለማድረግ እርሱን ከሚወዱት ጋር ይሠራል::*
"28 *አንዳንድ ቅጆች እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን* ይላሉ::

8፥30 ቆላ28፤ ሮሜ4፥25፤ 9፥23፤ኤፌ1፥5:11፤ 8፥31 ዘፀ3፥12፤
መዝ56፥9፤118፥6፤ኢሳ8፥10፤41፥10፤ኤር20፥11፤ሐጌ1፥13፤
ሮሜ4፥1፤6፥1፤7፥7፤9፥14:30፤ ዕብ13፥6 8፥32 ዘፍ22፥13፤
ሚል3፥17፤ዮሐ3፥16፤ሮሜ5፥8 8፥33 ኢሳ50፥8:9

ሁኔታ አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ የክብር ተካፋዮች ስለ መሆናችን ጥርጣሬ የሚፈጥር አይደለም:: ይልቁንስ ክርስቲያን በምድራዊ ሕይወቱ ሥቃይ ቢደርስበትም፣ ወደፊት ወራሽ እንደሚሆን መተማመኛን አግኝቶአል::

8፥19 ፍጥረት፤ የሰውን ዘር ሳይጨምር፣ ሕይወት ያላቸውንና ሕይወት የሌላቸውን ነገሮች ያመለክታል (ቍ 22-23 ይመ፤ ይህም በሌሎች ፍጥረታትና በእኛ መካከል ንጽጽር የተደረገበት ክፍል ነው):: *የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ፤* ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፤ ነገር ግን እስከ ፍጻሜው የዚህ መብት ሙሉ ክብር ምን ማለት እንደ ሆነ ገና አልተገለጠም (1ዮሐ 3፥1-2 ይመ)::

8፥20 *ለከንቱነት ተዳርጎአል፤* በዘፍ 3፥17-19 የተጻፈውን ያመለክታል:: *ለተስፋ፤* በዘፍ 3፥15 ላይ የተሰጠውን ተስፋ ለማመልከት የተጠቀሰ ቃል ሊሆን ይችላል::

8፥21 *ከመበስበስ ባርነት ነጻ ወጥቶ፤* ሰማይና ምድር ወደፊት ሊታደስ እንጂ ሙሉ በሙሉ ሊጠፋ የተመደበ አይደለም (2ጴጥ 3፥13፤ ራእ 21፥1)፤ እንደ ዛሬው ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሞትና መበስበስ አይሠለጥኑባቸውም::

8፥22 *በመቃተት ላይ እንደሚገኝ፤* ፍጥረት ሁሉ ልጅ ለመውለድ በምጥ ጣር ላይ በምትገኝ ሴት ተመስሎአል::

8፥23 *የመጀመሪያውን የመንፈስ ፍሬ፤* ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆኑ አሁን ላገኘው ድነት ማረጋገጫ ብቻ ሳይሆን (ቍ 14:16፤ ወደ ፊት ለሚያገኘው ውርስ ቃል ኪዳን፣ ማለትም የውርስ ባለመብት ለመሆኑ ተጨባጭ መያዣ ነው (2ቆሮ 1፥22፤ 5፥5፤ ኤፌ 1፥14 ይመ):: *ልጅነታችንን፤* የቍ15 ማብ ይመ:: ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፤ ነገር ግን እዚህ ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ በክርስቶስ ያገኘነውን ውርስ ወደፊት ሙሉ በሙሉ የምንረዳበትን ሁኔታ ለማሳየት ነው:: *የሰውነታችን ቤዛ፤* ከትንሣኤ በኋላ፣ የእግዚአብሔር ልጅነት ውርሳችንን የምንጨብጥበት ድምዳሜ ነው:: ልጅነታችን በእግዚአብሔር ሐሳብ አስቀድሞ መወሰኑ የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን (ኤፌ 1፥5)፣ ሁለተኛው ደግሞ አሁን ያገኘነው የእግዚአብሔር ልጆች ሆነን የተቈጠርንበት ደረጃ ነው (ቍ14 ገላ 3፥26 ይመ)::

8፥24 *በዚህ ተስፋ፤* እኛ የዳነው በተስፋ ሳይሆን በእምነት ነው (ኤፌ 2፥8)፤ ነገር ግን ተስፋ ድነት ጋር አብሮ አለ::

8፥26 *እንዲሁም ደግሞ፤* ተስፋ፣ ክርስቲያንን በመከራ ጊዜ አጽንቶ እንደሚያቆመው ሁሉ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እንዲጸልይ ያግዘዋል:: *በቃላት ሊገለጥ በማይችል መቃተት፤* በቍ 23 ላይ ክርስቲያን እንደሚቃትት ተገልጾአል፤ እዚህ ላይ የተገለጸው ግን የመንፈስ ቅዱስ መቃተት ነው:: እዚህ ላይ ከአንደበት ያልወጣ ሐሳብን ለማሳየት ይሁን ወይም በሰው ቋንቋ ሊገለጥ የማይቻል ቃልን ለማመልከት፣ ሐሳቡ ግልጥ አይደለም፤ የቍ 27 ሐሳብ በሰው ቋንቋ ሊገለጥ የማይቻል ወደሚለው ቢያዘነብልም፣ ትክክለኛው ግን የመጀመሪያው ሊሆን ይችላል::

*8፥27፤* በመንፈስ ቅዱስና በእግዚአብሔር አብ መካከል ቅርብ ግንኙነት ስላለ፣ መንፈስ ቅዱስ ድምፅ በማሰማት መጸለይ አያስፈልገውም፤ እግዚአብሔር አብ እያንዳንዱን የመንፈስ ቅዱስ ሐሳብ ያውቃልና::

8፥28 *ለበጎ፤* ይህም እግዚአብሔር የልጁን መልክ እንድንመስል የሚያደርገው በጎነት ነው:: *ለተጠሩት፤* የሚፈለገውን ውጤት የሚያስገኝ ጥሪ ነው፤ ይኸውም ያለ ጥርጥር አዎንታዊ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባ የእግዚአብሔር ጥሪ ነው::

8፥29 *አስቀድሞ ያወቃቸውን፤* አንዳንዶች እዚህ ላይ የተገለጠው ዕውቀት በሐሳብ ብቻ ሳይሆን በፍቅር የተገለጠና በዓላማ ላይ የተመሠረተ እንደ ሆነ አጥብቀው ይናገራሉ:: ደግሞም፣ እግዚአብሔር እርሱን ከማወቃችን በፊት እኛን ማወቁን ብቻ ሳይሆን፣ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ዐውቆን በጸጋው እንደ መረጠንም ያምናሉ (ኤፌ 1፥4፤ 2ጢሞ 1፥9 እና ማብ ይመ):: ሌሎች ደግሞ የጳውሎስ አባባል፣ እግዚአብሔር ከዘላለም ዘመናት በፊት በእምነት ሕዝቡ የሚሆኑትን እነዚያን፣ አስቀድሞ እንዳወቃቸው የሚያመለክት ነው በማለት ያምናሉ:: *አስቀድሞ የወሰናቸውን፤* እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የመረጣቸው፣ የልጁን መልክ ይመስሉ ዘንድ ቀዳሚ ዕቅድ እንዳለው ያሳያል:: *ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኵር እንዲሆን፤* እግዚአብሔር እነዚህን አስቀድሞ ያወቃውቸውና የልጁን መልክ እንዲመስሉም አስቀድሞ የወሰናቸው፣ በታላቁ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ውስጥ ክርስቶስ ኢየሱስ ከፍተኛውን የክብር ስፍራ እንዲይዝ ለማድረግ ነው::

8፥30 *አስቀድሞ የወሰናቸውን ... አከበራቸው፤* እግዚአብሔር አስቀድሞ በወሰነው መሠረት የሚያደርገውን ነገር ቅደም ተከተል ያሳያል:: *አከበራቸው፤* ይህ የመጨረሻው ደረጃ፣ እግዚአብሔር በቅደም ተከተል በሚፈጽማቸው ዕቅዶች ላይ የተመሠረተ ስለ ሆነ፣ የተፈጸመ ያህል ሆኖ ይቈጠራል::

8፥31 *እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፤* የዚህ ሐረግ ዐይነትና አቀራረብ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑ እንደማያጠራጥር ግልጥ ያደርገዋል::

*8፥32፤* በዚህ ክፍል በተዋረድ የተነሣው የክርክር ሐሳብ፣ በም 5፥9-10 ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ነው:: እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ከሁሉ የሚበልጠውን ስጦታ ልጁን ከሰጠ፣ በመስቀል ላይ የተጀመረውን ሥራ ከፍጻሜ ለማድረስ፣ አስፈላጊ የሆነውን ማንኛውንም ነገር እንደሚሰጥ የሚያጠራጥር አይደለም፤ የዘፍ 22፥16 ማብ ይመ::

*8፥33-34፤* ፍትሕ የሚታይበትን ፍርድ ቤት ያመለክታል:: እግዚአብሔር ከወንጀል ነጻ አድርጎ የፈረደለት ስለ ሆነ፣ ከእንግዲህ

የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፤ 34ታዲያ የሚፈርድ
ማን ነው? የሞተው፣ እንዲሁም ከሞት የተነ
ሣው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው ክርስቶስ
ኢየሱስ፣ ስለ እኛ ይማልዳል። 35ከክርስቶስ
ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ነው ወይስ
ሥቃይ፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ረሀብ፣ ወይስ
ዕራቍትነት፣ ወይስ አደጋ ወይስ ሰይፍ?
36ይህም፣

"ስለ አንተ ቀኑን ሙሉ ከሞት ጋር
 እንጋፈጣለን፤
እንደሚታረዱ በጎች ተቈጠርን"

ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።
37ምንም አይለየንም፤ በዚህ ሁሉ በወደደን
በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። 38ይህን
ተረድቻለሁ፤ ሞትም ይሁን ሕይወት፣ መላእ
ክትም ይሁኑ አጋንንት፣[ቸ] ያለውም ይሁን የሚ
መጣው፣ ወይም ማንኛውም ኀይል፣ 39ከፍ
ታም ይሁን ጥልቀት፣ ወይም የትኛውም
ፍጥረት፣ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካለው
ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም።

### የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ

9 በክርስቶስ ሆኜ እውነት እናገራለሁ፤ አል
ዋሽም፤ ኅሊናዬም በመንፈስ ቅዱስ ይመ
ሰክርልኛል። 2ታላቅ ሐዘንና የማያቋርጥ
ጭንቀት በልቤ አለ። 3ለወገኖቼ ስል ስለ
ወንድሞቼ እኔ ራሴ የተረገምሁና ከክር
ስቶስም ተለይቼ የተጣልሁ እንድሆን እንኳ
እወድ ነበር፤ 4እነርሱም የእስራኤል ሕዝብ
ናቸው፤ ልጅ መሆን፣ መለኮታዊ ክብር፣
ኪዳን፣ ሕግን መቀበል፣ የቤተ መቅደስ ሥርዐ
ትና ተስፋ የእነርሱ ናቸውና። 5አባቶችም
የእነርሱ ናቸው፤ ክርስቶስም በሥጋ የትውልድ
ሐረጉ ሚቈጠረው ከእነርሱ ነው፤ እርሱም፣
ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ
ነው፤[የ] አሜን።
6ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ተሽሮአል
ማለት አይደለም፤ ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ
እስራኤል አይደለምና። 7ከአብርሃም ዘርም
ስለሆኑ፣ ሁሉም ልጆቹ አይደሉም፤ ይልቁንስ፣
"ትውልድህ በይሥሐቅ በኩል ይጠራልሃል"
እንደ ተባለው ነው። 8ይህም ማለት የእግዚአብሔር
ልጆች የተባሉት የሥጋ ልጆች አይደሉም፤
ነገር ግን የአብርሃም ልጆች የተባሉት የተ
ስፋው ልጆች ናቸው። 9"ጊዜው ሲደርስ
እመለሳለሁ፤ ሳራም ወንድ ልጅ ትወልዳለች"
ተብሎ ተስፋው ተሰጥቶአልና።
10ይህም ብቻ ሳይሆን፣ የርብቃ ልጆች
አንድ አባት አላቸው፤ እርሱም አባታችን

8፥34 ቍ1፡27፤ ኢዮ16፥20፤ ኢሳ53፥12፤ ማር16፥19፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ 5፥6-8፤ዕብ7፥25፤ 9፥24፤1ዮሐ2፥1 8፥35 ቍ37-39፤ 1ቆሮ4፤2ቆሮ11፥26፤ 27 8፥36መዝ44፥22 1ቆሮ4፥9፤15፥30፡31፤ 2ቆሮ4፥11፤6፥9፤ 11፥23 8፥37 ሮሜ5፥8፤ 1ቆሮ15፥57፤ ገላ2፥20፤ኤፌ5፥2፤ ራእ1፥5፤3፥98፥38፤ 1ቆሮ3፥22፤ኤፌ1፥21፤ ቈላ1፥16፤1ጴጥ3፥22 8፥38 1ቆሮ3፥22፤ ኤፌ1፥21፤ቈላ1፥16፤ 1ጴጥ3፥22 8፥39 ቍ1፤ ሮሜ5፥8፤16፥3 9፥1 መዝ15፥2፤ ሮሜ1፥9፤ 2ቆሮ11፥10፤ገላ1፥20፤ 1ጢሞ2፥7፤ 9፥3 ዘፀ32፥32፤ ሐሥ22፥5፤ሮሜ1፥14፤ 1ቆሮ12፥3፤16፥22፤ 9፥4 ዘፍ17፥2፤ ዘፀ4፥22፤6፥7፤ ዘዳ7፥6፤14፥13፤ መዝ147፥19፤ ሐሥ13፥32፤3፥25፤ ገላ3፥16፤ኤፌ2፥12፤ ዕብ9፥1፤9፥5 9፥5 ማቴ1፥1-16፤ ዮሐ 1፥1፤ሮሜ1፥3፤1፥25፤ 11፥28፤2ቆሮ11፥31፤ቈላ2፥9፤ 9፥6 ሮሜ2፥28:29፤ ገላ 6፥16፤ ዕብ4፥12፤ 9፥7 ዘፍ21፥12፤ዕብ11፥18 9፥8 ሮሜ 8፥14፤ ገላ3፥16 9፥9 ዘፍ18፥10:14 9፥10 ዘፍ25፥21

[ቸ]38 ወይም *በሰማይ ያሉ አለቆች*
[የ]5 ወይም *ከሁሉ በላይ የሆነ ለዘላለም የተመሰገነ አምላክ ይሁን ወይም ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን*

በክርስቲያን ላይ ክስ ሊቀርብ አይችልም።

*8፥34፤* በእግዚአብሔር ምርጦች ላይ ማንም ሊፈርድ እንደ ማይችል ሦስት ምክንያቶች ቀርበዋል። እነርሱም፣ 1) ክርስቶስ ለእኛ ሞቶልናል 2) ለዘላለም ሕያው ሆኖ ይኖራል፤ ከፍተኛ ሥልጣንን በሚያመለክተው በአብ ቀኝ ተቀምጦአል፤ 3) ስለ እኛም ይማልዳል።

*8፥35-39፤* በዚህ ክፍል ጳውሎስ የገለጸው ሐሳብ፣ መከራ ክርስቲያኖችን ከክርስቶስ የሚለያቸው ሳይሆን፣ ወደ መጨረሻው ግባቸው የሚያደርሳቸው መሆኑን ነው።

*8፥36፤* በዚህ ክፍል የተጠቀሰው፣ መከራ ለእግዚአብሔር ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ፣ የኑሮአቸው አንዱ ገጽታ እንደ ሆነ ለማሳየት ነው።

8፥37 *በወደደን፤* በተለይ የክርስቶስን በመስቀል ላይ መሞት ያመለክታል።

8፥39 *ከፍታም ይሁን ጥልቀት፤* የእግዚአብሔር ፍቅር ቦታ አይወስነውም። *የትኛውም ፍጥረት፤* ይህ አባባል ሁሉን ከፈጠረው ከእርሱ በቀር፣ የተፈጠሩትን ነገሮች ሁሉ ይጨምራል፤ እኛንም ያጸደቀን እርሱ እግዚአብሔር ነው (ቍ 33)።

9፥1 *በመንፈስ ቅዱስ፤* ኅሊናችን በአስተማማኝነት ሊመራን የሚችለው የመንፈስ ቅዱስን ብርሃን ሲያገኝ ብቻ ነው።

9፥3 *የተረገምሁና፤* ለዚህ ቃል የሚተካው የግሪኩ ቃል "የተጠላ" የሚል ትርጕም አለው፤ ይኸውም ለዘላለም ጥፋት ለእግዚአብሔር ቍጣ ዐልፎ የተሰጠ ማለት ነው (1ቆሮ 12፥3፤ 16፥22፤ ገላ 1፥8-9 ይመ)። ጳውሎስ ለአይሁድ ወገኖቹ እንዲህ ያለ ታላቅ ፍቅር ነበረው። ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያለውን የፍቅር አገላለጽ በዘጸ 32፥32 ይመ።

9፥4 *የእስራኤል ሕዝብ፤* እነዚህ እግዚአብሔር ስሙን ለውጦ እስራኤል ብሎ የጠራው ያያዕቆብ ትውልድ ናቸው (ዘፍ 32፥28 ይመ)። በሚሳ 5፥7 እንደ ተጠቀሰው፣ "እስራኤል" የሚለው ስም በመጀመሪያ ለጠቅላላ የእስራኤል ሕዝብ መጠሪያ ነበር፤ አገሩ ለሁለት ከተከፈለ በኋላ ግን (1ነገ 12 ይመ)፣ ስሙ የሰሜኑ ግዛት ብቻ መጠሪያ ሆነ፣ የደቡብ ግዛት ደግሞ "ይሁዳ" ተባለ። በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል በነበረው ዘመንና በኋላም በአዲስ ኪዳን ዘመን፣ በፍልስጥኤም ቆኖሩ የነበሩት አይሁድ ይህን ስም በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች መሆናቸውን ለማመልከት ይጠቀሙበት ነበር። ጳውሎስ ባለማመንና ባለመታዘዝ ለምትገኘው እስራ ኤል፣ እግዚአብሔር ሊፈጽምላት የገባው ቃል ኪዳን አሁንም የጸና መሆኑን ለማሳየት የሚፈልግ ስለ ሆነ፣ እዚህ ላይ የዚህ ስም አገባብ ተገቢነት አለው። *ልጅ መሆን፤* እስራኤል በእግዚአብሔር ዘንድ የልጅነት መብት አግኝታ ነበር (ዘፀ 4፥22-23፤ ኤር 31፥9፤ ሆሴ 11፥1 ይመ)። *ክብር፤* እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል መገኘቱን የሚያረጋግጥ ነው (ዘፀ 16፥7:10፤ ዘሌ 9፥6:23፤ ዘኍ 16፥9 ይመ)። *ኪዳን፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ ልዩ ኪዳኖች ተጠቅሰዋል፤ እነርሱም የአብርሃም ኪዳን (ዘፍ 15፥17-21፤ 17፥1-8) በሞዓብ ምድር (ዘዳ 29፥15)፣ በጌባል፣ በገሪዛን ተራራና (ኢያ 8፥30-35) በሴኬም (ኢያ 24፥25) የታደሰው የሙሴ ኪዳን (ዘጸ 19፥5፤ 24፥1-4)፣ እንዲሁም የዘሌዋውያን ኪዳን (ዘኍ 25፥12-13፤ ኤር 33፥21፤ ሚክ 2፥4-5)፣ የዳዊት ኪዳን (2ሳሙ 7፤ 23፥5፤ መዝ 89፥3-4፡ 28-29፤ 132፥ 11-12) እና (በኤር 31፥31-40 የተጠቀሰው) አዲሱ ኪዳን ናቸው። *ተስፋ፤* በተለይ ለአብርሃም የተሰጡ ተስፋዎችን የሚያመለክት ሲሆን (ዘፍ 12፥7፤ 13፥14-17፤ 17፥4-8፤ 22፥16-18)፣ በብሉይ ኪዳን ውስጥ መሲሑን በሚመለከት የተሰጡ ተስፋዎችንም ይጨምራል (2ሳሙ 7፥12:16፤ ኢሳ 9፥6-7፤ ኤር 23፥5፤ 31፥31-34፤ ሕዝ 34፥23-24፤ 37፥24-28)።

9፥5 *አባቶችም፤* አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብና ልጆቹ ማለት ነው። *አምላክ፤* በአዲስ ኪዳን ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በግልጽ ከሚያሳዩት ሐረጎች አንዱ ነው፤ (1፥4፤ ማቴ 1፥23፤ 28፥19፤ ሉቃ 1፥35፤ 5፥20-21፤ ዮሐ 1፥1:3:10:14:18፤ 5፥18፤ 20፥28፤ ሐዋ 20፥28 2ቆሮ 13፥14፤ ፊል 2፥6፤ ቈላ 1፥15-20፤ 2፥9፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ 1፥3:8፤ 2ጴጥ 1፥1፤ ራእ 1፥13-18፤ 22፥13 ይመ)።

9፥6 *የእግዚአብሔር ቃል፤* በግልጽ የተጻፈው የእግዚአብሔር ዐላማ አልተሻረም፤ ምክንያቱም "ከእስራኤል የተወለደ ሁሉ እስራኤል አይደለምና"፤ ጳውሎስ ባመነውና ባላመነው እስራ ኤል መካከል ያለውን ልዩነት ለመግለጽ እንጂ፣ እንደ አንድ ሕዝብ የእስራኤልን መመረጥ መካዱ አይደለም። በሥጋ የአንድ ዘር ወገን መሆን፣ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባል ለመሆን ዋስትና አይሆንም።

9፥7 *ዘርም፤* ከአብርሃም ትውልድ የሆኑትን ያመለክታል፤ ለምሳሌ እስማኤልና ልጆቹን።

9፥8 *የሥጋ ልጆች፤* በሥጋ ከአብርሃም አብራክ የተገኙና የእርሱ ዘር የሆኑ ማለት ነው። *የእግዚአብሔር ልጆች፤* ቍ 4 ይመ፤ እስራኤላውያን ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ማለት አይደለም፤ ይህ የሚያመለክተው በእምነት የእስራኤል ወገን

ይሥሐቅ ነው። 11መንትዮቹ ገና ሳይወለዱ፣
ወይም በጎም ሆነ ክፉ ሳያደርጉ፣ የእግዚአብሔር
ሐሳብ በምርጫ ይጸና ዘንድ፣ 12በሥራ ሳይ
ሆን ከጠሪው በመሆኑ፣ "ታላቁ ታናሹን
ያገለግላል" ተብሎ ተነገራት። 13ይህም፣ "ያዕ
ቆብን ወደድሁ፤ ዔሳውን ግን ጠላሁ" ተብሎ
እንደ ተጻፈው ነው።

14እንግዲህ ምን እንላለን? እግዚአብሔር አድልዎ
ያደርጋልን? በፍጹም አያደርግም! 15ለሙሴ፣

"የምምረውን እምረዋለሁ፤
ለምራራለትም እራራለታለሁ"
ይላልና።

16እንግዲህ ይህ ከሰው ፍላጎት ወይም
ጥረት ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ
ነው። 17መጽሐፍ ፈርዖንን፣ "ኀይሌ በአንተ
እንዲታይ፣ ስሜም በምድር ሁሉ እንዲነገር
ለዚህ አስነሣሁህ" ይላልና። 18ስለዚህ እግዚ
አብሔር ሊምረው ለሚወደው ምሕረት ያደርግ
ለታል፤ ልቡ እንዲደነድን የፈለገውንም ያደነ
ድነዋል።

19ከእናንተ አንዱ፣ "ታዲያ እንደዚህ ከሆነ
እግዚአብሔር እስከ አሁን ለምን ይወቅሰናል?
ምክንያቱም ፈቃዱን ሊቋቋም የሚችል ማን
አለ?" ይለኝ ይሆናል። 20ነገር ግን በእግዚ
አብሔር መልስ የምትሰጥ አንተ ማን ነህ?
"ሥራ ሠሪውን፣ 'ለምን እንዲህ ሠራኸኝ?'
ይለዋልን?" 21ሸክላ ሠሪ፣ ከሚሠራው ጭቃ፣
አንዳንዱን ሸክላ ለክብር፣ ሌላውን ደግሞ
ለተራ አገልግሎት የማድረግ መብት የለውምን?

22እግዚአብሔር ቍጣውን ለማሳየት፣ ኀይሉንም
ለማሳወቅ ፈልጎ የቍጣው መግለጫ የሆኑ
ትን፣ ለጥፋትም የተዘጋጁትን እጅግ ታግሦ
ቢሆንሳ! 23አስቀድሞ ለክብር ላዘጋጃቸው፣
የምሕረቱም መግለጫዎች ለሆኑት፣ የክብሩ
ባለ ጠግነት እንዲታወቅ ይህን አድርጎ እንደ
ሆነስ? 24የጠራው ከአይሁድ ወገን ብቻ ሳይሆን
ከአሕዛብ ወገን የሆነውን እኛን እንኳ ሳይ
ቀር አይደለምን? 25በሆሴዕ እንዲህ እንደሚል፤

"ሕዝቤ ያልሆኑትን፣ 'ሕዝቤ'
ብዬ እጠራቸዋለሁ፤
ያልተወደደችውንም 'የተወደደችው'
ብዬ እጠራለሁ።
26ደግሞም፣ " 'ሕዝቤ አይደላችሁም'፤
ተብሎ በተነገራቸው በዚያ ቦታ፣
'የሕያው እግዚአብሔር ልጆች' ተብለው
ይጠራሉ።"

27ኢሳይያስም ስለ እስራኤል እንዲህ ሲል

9፥11 ቍ16፤
ሮሜ8፥28
9፥12 ዘፍ25፥23
9፥13 ሚል1፥2:3
9፥14 2ዜና19፥7፤
ሮሜ8፥31፤
9፥15 ዘፀ33፥19
9፥16 ኤፌ2፥8፤
ቲቶ3፥5
9፥17 ዘፀ9፥16፤
14፥4፤መዝ76፥10
9፥18 4፥21፤7፥3፤
14፥4:17፤ዘዳ2፥30፤
ኢሱ11፥20፤
ሮሜ11፥25
9፥19 2ሳሙ16፥10፤
2ዜና20፥6፤ዳን4፥35፤
ሮሜ3፥7፤11፥19፤
1ቆሮ15፥35፤ያዕ2፥18፤
9፥20 ኢሳ64፥8፤
29፥16፤45፥9፤
10፥15፤ኤር18፥6፤
ኢዮ1፥22፤9፥12፤
40፥2፤
9፥21 2ጢሞ2፥20
9፥22 ምሳ16፥4፤
ሮሜ2፥4፤
9፥23 ሮሜ2፥4፤
8፥30
9፥24 ሮሜ8፥28፤
3፥29
9፥25 ሆሴ2፥23፤
1ጴጥ2፥10
9፥26 ሆሴ1፥10፤
ማቴ16፥16፤ሮሜ8፥14 9፥27 ዘፍ22፥17፤ ኤር44፥14፤50፥20፤
ሆሴ1፥10፤ 2ነገ19፥4፤ኢል2፥32፤ሮሜ11፥5

የሆኑትን ነው።

9፥11 *በጎም ሆነ ክፉ ሳያደርጉ፤* እግዚአብሔር ያዕቆብን የመረጠው እንደ በጎ ፈቃዱ እንጂ ያዕቆብ አስቀድሞ ያሟላው ሁኔታ በመኖሩ አይደለም። *የእግዚአብሔር ሐሳብ በምርጫ፤* የእግዚአብሔር ሐሳብ የተገለጠው በገዛ ፈቃዱ ባደረገው ምርጫ በኩል ነው (የኤፌ 1፥4 ማብ ይመ)።

9፥12 *በሥራ ሳይሆን ከጠሪው በመሆኑ፤* የርብቃ ልጆች ከመወለዳቸው በፊት፣ እግዚአብሔር በሰው ተግባር ላይ ያልተመሠረተ ምርጫ አደረገ። *ከጠሪው፤* 8፥28 እና ማብ ይመ።

9፥13 *ያዕቆብን ወደድሁ፤ ዔሳውን ግን ጠላሁ፤* "ያዕቆብን መረጥሁ፤ ዔሳውን ግን ናቅሁ" ከሚለው ጋር አንድ ነው። ጳውሎስ በቍ 6-13 ላይ ግለሰብን ስለሚመለከት ምርጫ እንጂ፣ ጠቅላላውን ሕዝብ ስለሚመለከት ምርጫ መናገሩ አይደለም። ሚል ክያስ በ1፥2-3 የተናገረው ጠቅላላውን ሕዝብ የሚመለከት ምርጫ ቢሆንም፣ ጳውሎስ ይህን የገለጸው የኤዶምያስ ሕዝብ ተንቆ መላው የእስራኤል ሕዝብ መመረጡን ለማሳየት አይደለም። የጳውሎስ ሐሳብ ከእስራኤል ወገን ከሆኑት ብዙዎች የማያምኑና ካለማመናቸውም የተነሣ የሚጠፉ ሆነው ሳለ፣ የእግዚአብሔር ተስፋ እንዴት ሊጸና ይችላል? በሚለው ላይ እንደሚያተኵር በግልጥ ይታያል።

9፥14 *እግዚአብሔር አድልዎ ያደርጋልን?* በያዕቆብና በዔሳው ላይ እንደ ታየው እግዚአብሔር ከበጎ ፈቃዱ የተነሣ የወደደውን ያደርጋል።

*9፥15፤* እግዚአብሔር ምሕረትን እንደ ወደደ ለመስጠት ፍጹም መብት እንዳለው በማመልከት፣ በይስሐቅና በእስማኤል እንዲሁም በያዕቆብና በዔሳው መካከል ባደረገው ምርጫ አድልቶአል የሚለውን ሐሳብ ጳውሎስ አይቀበለውም።

9፥16 *ይህ፤* በማንኛውም መንገድ ሰው ሊቈጣጠረው የማይችለውን የእግዚአብሔርን ምርጫ ያመለክታል፤ ሆኖም ለእስራኤል መናቅ ምክንያቱ አለማመኗ እንደ ሆነ ጳውሎስ ግልጽ ያደርገዋል (ቍ 30-32 ይመ)።

9፥17 *ፈርዖን፤* በዘፀአት የተጠቀሰው ፈርዖን ነው። *አስነሣሁህ፤* የግብፅ ገዢ አደረገው። *ስሜም፤* በተለይም በዘፀአት ላይ እንደ ተገለጸው ያለ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው (ዘፀ 15፥13-18፤ ኢሱ 2፥10-11፤ 9፥9፤ 1ሳሙ 4፥8 ይመ)።

*9፥18፤* የዚህ ጥቅስ የመጀመሪያው ክፍል በዘፀ 33፥19 ላይ የተጻፈውን ሐሳብ በድጋሚ ያመለክታል (ቍ 15 ይመ)፤ የመጨረሻው ክፍል ደግሞ በዘፀ 7፥3፤ 9፥12፤ 14፥4:17 እንደ ተጠቀሰው እግዚአብሔር የፈርዖንና የእስራኤልን ልብ እንዳደነደነ ያሳያል። *ሊምረው ለሚወደው፤* እግዚአብሔር በዘፈቀደ ሁኔታና በቅድመ ሁኔታዎች ላይ ተመርኵዞ እንዲሁ ምሕረቱን ያደርጋል ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር እስራኤልን የናቃት ካለ ማመኗ የተነሣ እንደ ሆነ ጳውሎስ ይገልጻል (ቍ 30-32 ይመ) ነው።

*9፥19፤* አንድ ሰው "እግዚአብሔር ልባቸውን የሚያደነድኑትንና የማያደነድኑትን አስቀድሞ የወሰናቸው ከሆነ፣ ታዲያ ልባቸውን ያደነደኑትን ሰዎች እንዴት ጥፋተኛ አድርጐ ይቈጥራል" በማለት ሊቃወም ይችላል።

9፥20 *ለእግዚአብሔር መልስ የምትሰጥ አንተ ማንህ?* ጳውሎስ፣ እዚህ ላይ ሰው ስለ እግዚአብሔር የሚያቀርበውን ጥያቄ ችላ ማለቱ አይደለም፤ ነገር ግን ጳውሎስ ይህን የተናገረው በኀጢአታቸው ባለመጸጸትና የእግዚአብሔርን ክብር ዝቅ በማድረግ፣ ሰው ላደረገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ተጠያቂ ለሚያደርጉ፣ በጥያቄአቸውም የእግዚአብሔርን ክብር ለሚያጕድፉ ነው።

*9፥21፤* ዋናው ሐሳብ እግዚአብሔር ለሰውና በሰው ላይ በሚያደርገው ነገር ፍጹም ነጻነት እንዳለው ለማመልከት ስለ ሆነ፣ በእግዚአብሔርና በሸክላ ሠሪ፣ እንዲሁም በሰውና በሸክላ መካከል እንደ ምሳሌ ሆኖ ለንጽጽር የቀረበውን ሐሳብ አክርሮ መመልከቱ ተገቢ አይደለም።

*9፥22-23፤* በቍ 21 ላይ የተጠቀሰውን መመሪያ የሚያብራራ ነው፤ የሚያተኵረውም በእግዚአብሔር ቍጣ ላይ ሳይሆን በምሕረቱ ላይ ነው።

9፥22፤ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር "ለምን እንደዚያ ሆነ?" በማለት ማንም ሊከራከረው አይችልም፤ ይሁን እንጂ የወደደውን ለማድረግ ያለውን የምርጫ ነጻነት ያለ አግባብ አይጠቀምበትም፤ ለሚያስቈጡት ሰዎች እንኳ ትዕግሥቱ እጅግ የበዛ ነው። በ2፥4 ላይ በተገለጸው መሠረት የዚህ ዐይነቱ ትዕግሥት ዐላማ ሰዎችን ወደ ንስሓ ለማምጣት ነው።

9፥23 *የክብሩ፤* የ3፥23 ማብ ይመ።

*9፥25-26፤* ይህ ክፍል ከትንቢተ ሆሴዕ የተወሰደ ሲሆን፣ በመሠረታዊ ሐሳቡ የእስራኤልን መንፈሳዊ ተሐድሶ ያመለክታል። እግዚአብሔር እነዚያን "ሕዝቤ ያልሆነውን" "አንተ ሕዝቤ ነህ" ብሎ በመጥራት ደስ የሚሰኝ፣ የሚያድን፣ የሚምርና የሚያድስ አምላክ እንደ ሆነ ጳውሎስ ዐቢይ የሆነ መርሕ ከዚህ ክፍል ለመገንዘብ ችሏል። ጳውሎስም ይህን መርሕ፣ እግዚአብሔር በገዛ ፈቃዱ በኪዳኑ ኅብረት ውስጥ በማስገባት "አንተ ሕዝቤ ነህ" ላላቸው አሕዛብ አውሎታል (ም 11 ይመ)።

*9፥27-29፤* ከኢሳይያስ መጽሐፍ የተወሰዱት እነዚህ ጥቅሶች ቍጥሩ እጅግ ከበዛው የእስራኤል ሕዝብ ጥቂቱ ብቻ እንደሚድን

ይጮኻል፤
"የእስራኤል ልጆች ቊጥር
በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ ቢሆንም፣
ትሩፋ ብቻ ይድናል።
28ጌታ ፍርዱን በምድር ላይ፣
በፍጥነትና ለመጨረሻ ጊዜ ይፈጽማልና።"
29ይኸውም ቀደም ሲል ኢሳይያስ
እንደ ተናገረው ነው፤
"የሰራዊት ጌታ፣ ዘር ባያስቀርልን ኖሮ፣
እንደ ሰዶም በሆን ነበር፤
ገሞራንም በመሰልን ነበር።"

## የእስራኤል አለማመን

30እንግዲህ ምን እንበል? በእምነት የሆነውን
ጽድቅ፣ ለጽድቅ ያልደከሙት አሕዛብ አገኙት፤
31ነገር ግን የጽድቅን ሕግ የተከታተሉት
እስራኤል አላገኙትም። 32ይህ ለምን ሆነ?
በእምነት ሳይሆን በሥራ እንደ ሆነ አድርገው
በመቊጠር ስለ ተከታተሉት ነው፤ እነርሱም፣
"በማሰናከያው ድንጋይ" ተሰናከሉ።

33ይህም፣

"እነሆ፤ ሰዎችን እንዲደናቀፉ
የሚያደርግ ድንጋይ፣
እንዲወድቁ የሚያደርግ ዐለት፣
በጽዮን ላይ አስቀምጣለሁ፤
በእርሱም የሚያምን አያፍርም"
ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

10 ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እስራኤላውያን
የልቤ ምኞት፣ እግዚአብሔርንም የምለ
ምነው እንዲድኑ ነው። 2ለእግዚአብሔር ቀናተኛ
እንደ ሆኑ ስለ እነርሱ መመስከር እችላለሁና፤
ቅናታቸው ግን ከዕውቀት የተነሣ አይደለም።
3ከእግዚአብሔር የሚመጣውን ጽድቅ ስላላወቁና
የራሳቸውን ጽድቅ ለመመሥረት ስለ ፈለጉ፣
ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም። 4ለሚያምን
ሁሉ ጽድቅ ይሆን ዘንድ ክርስቶስ የሕግ
ፍጻሜ ነውና።
5ሙሴ በሕግ በኩል የሆነውን ጽድቅ ሲገ
ልጽ፣ "እነዚህን የሚፈጽም ሰው በእነርሱ
ይኖራል።" ይላል። 6ከእምነት የሆነው ጽድቅ
ግን እንዲህ ይላል፤ " 'በልብህ ማን ወደ
ሰማይ ይወጣል?' አትበል"፤ ይህ ክርስቶስን
ለማውረድ ነው፤ 7"ወይም 'ወደ ጥልቁስ ማን
ይወርዳል?' አትበል"፤ ይህም ክርስቶስን
ከሙታን ለማውጣት ነው። 8ነገር ግን ምን
ይላል? "ቃሉ በአጠገብህ ነው፤ በአፍህና
በልብህም ውስጥ ነው፤" የምንሰብከውም የእ
ምነት ቃል ይህ ነው፤ 9"ኢየሱስ ጌታ ነው"
ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም
ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣

9፥28 ኢሳ10፥22፡23
9፥29 ዘፍ19፥24-29፤ ዘዳ29፥23፤ ኢሳ1፥9፤13፥19፤ ኤር50፥40፤ያዕ5፥4፤
9፥30 ሮሜ8፥31፤ 1፥17፤3፥22፤4፥5፡13፤ 10፥6፤ገላ2፥16፤ ፊል3፥9፤ዕብ11፥7
9፥31 ዘዳ6፥25፤ ኢሳ 51፥1፤ ሮሜ10፥2፡3፤11፥7፤ ገላ 5፥4
9፥32 1ጴጥ2፥8
9፥33 ኢሳ8፥14፤ 28፥16፤ሮሜ10፥11፤ 1ጴጥ 2፥6፡8
10፥1 መዝ20፥4
10፥2 ሐሥ21፥20
10፥3 ሮሜ1፥17፤ 9፥31
10፥4 ሮሜ7፥1-4፤ 3፥22፤ ገላ 3፥24፤
10፥5 ዘሌ18፥5፤ ዘዳ4፥1፤6፥24፤ ነህ9፥29፤ምሳ19፥16፤ ኢሳ55፥3፤ሕዝ20፥11፡13፡21፤ሮሜ7፥10
10፥6 ዘዳ30፥12፤ ሮሜ9፥30፤
10፥7 ዘዳ30፥13፤ ሐሥ2፥24
10፥8 ዘዳ30፥14
10፥9 ማቴ10፥32፤

ያመለክታሉ። የእግዚአብሔር ጥሪም አይሁድንና አሕዛብን ይጨምራል (ቍ 24 ይመ)። ነገር ግን በቍጥር 30 ላይ የሚገኘው ሐሳብ ከተጠሩት ብዙኃኑ አሕዛብ እንደሆኑ ያመለክታል።

*9፥30-32፤* እስራኤል የተናቀችው እግዚአብሔር የሰጣትን ማለትም ወደ ክርስቶስ የሚያመለክተውን ሕግ ካለመታዘዟ የተነሣ ነው፤ ሕጉን የተከተለችበት መንገድ በእምነት ሳይሆን በዘል ማድና በሥራ ላይ ብቻ የተመሠረተ ነበር። ስለዚህ ለእስራኤል መናቅ ዐቢይ ምክንያት የሆነው አለማመኗ ነበር። እንግዲህ፣ በጳውሎስ የክርክር ሂደት ይህኛው አቀራረብ የተለየ ነው።

9፥31 *የጽድቅን ሕግ፤* ጳውሎስ የተቃወመው "ሕግን ስለ ፈጸምሁ በሥራ እጸድቃለሁ" በማለት እግዚአብሔርን ባለ ዕዳ ለማድረግ የሚደረገውን ሙከራ እንጂ ለሕግ መታዘዝን አይደለም።

9፥32 *በእምነት ሳይሆን፤* እስራኤል የወደቀችው የተሳሳተ ነገር በመከተሏ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ምሕረትና ጽድቅ ለማግኘት እምነትን መሠረት ከማድረግ ይልቅ በመልካም ሥራዋ ልታገኘው ከንቱ ጥረት በማድረጓ ነው። *"በማሰናከያው ድንጋይ"፤* መሲሑ ኢየሱስን የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን የናቀው ያለ ምክንያት አልነበረም። ነገር ግን ጽድቅ በእምነት እንዲገኝ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን መንገድ ባለመቀበሏ ነበር።

*9፥33፤* ከትንቢተ ኢሳይያስ በመውሰድ በአንድ ላይ ተቀናጅተው የቀረቡትን እነዚህን ጥቅሶች፣ የጥንት ክርስቲያኖች በኢየሱስ መሲሕነት ላይ የሚነሣውን ክርክር ለመቋቋም ይጠቀሙባቸው ነበር (1ጴጥ 2፥4፡6-8፤ መዝ 118፥22፤ ሉቃ 20፥17-18 ይመ)።

10፥1 *ስለ እስራኤላውያን ... እግዚአብሔርንም የምለምነው፤* ጳውሎስ ስለ አብያተ ክርስቲያናት ብዙውን ጊዜ ይጸልይ ነበር (ኤፌ 1፥15-23፤ ቈላ 1፥3፤ 1ተሰ 1፥2-3፤ 2ተሰ 1፥3 ይመ)፤ እዚህ ላይ ግን በሥጋ ወገኖቹ ለሆኑት እስራኤላውያን መዳን ይጸልይ እንደ ነበር ያመለክታል።

10፥2 *ለእግዚአብሔር ቀናተኛ፤* አይሁድ የነበራቸው ቅናት በእግዚአብሔር ላይ ስለሚያተኵር (ሐሥ 21፥20፤ 22፥3፤ ገላ 1፥14 ይመ)፣ የሚደገፍ ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ለድነት ያዘጋጀውን መንገድ በማወቅ ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ እንዲነቀፍ ያደርገው ነበር። ጳውሎስ ከመለወጡ በፊት የነበረው ሕይወት ለእንደዚህ ዐይነቱ ቅናት ምሳሌ ነው (ገላ 1፥14 ይመ)።

10፥3 *ከእግዚአብሔር የሚመጣውን፤* በሰው ሥራ ሊገኝ የሚችል ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር በነጻ የሚሰጥ በእምነት ላይ የተመሠረተ ጽድቅ ማለት ነው (1፥17 ይመ)። *የራሳቸውን፤* በሰው ሥራ ላይ የተመሠረተ የጽድቅን ሕይወት ያመለክታል።

10፥4 *ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና፤* "ፍጻሜ" የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ የተለያየ ትርጕም ቢሰጠውም እዚህ ላይ ግን "ከግብ ማድረስ" ማለት ነው። ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነው ሲባል (ማቴ 5፥17 ይመ)፣ ለሕጉ ፍጹም በመታዘዝና የትንቢት ቃሎቹንም ተግባራዊ በማድረግ ሕጉን ሙሉ በሙሉ ፈጽሞታል ማለት ነው። ክርስቶስ ከሕግ ኵነኔ ነጻ ስላወጣው ክርስቲያን ከእንግዲህ "ከሕግ በታች አይደለም" (6፥15)፤ ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን ሕጉ በሕይወቱ ውስጥ ቦታ አለው። ክርስቲያን ሕጉ የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር ለማሟላት በመንፈስ ቅዱስ ነጻ ወጥቶአል (8፥4 ይመ)። *ጽድቅ፤* ክርስቶስ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ በሚሰጠው ጸጋ፣ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ መቆም ማለት ነው (የ1፥17፤ 3፥24 ማብ ይመ)።

10፥5 *እነዚህን የሚፈጽም ሰው በእነርሱ ይኖራል፤* በሲና ኪዳን መሠረት ለእስራኤል የተሰጠው ጽድቅ በዘሌ 18፥5 ላይ ተጠቅሶአል (የዚያኑ ማብ፤ ዘዳ 6፥25 ይመ)። አንዳንዶች ጳውሎስ ይህን ሐሳብ እዚህ ላይ የጠቀሰው፣ ሕግን በመፈጸም ጽድቅን ማግኘት እንደሚቻል ለማሳየት ነው ይላሉ (2፥6-10 ይመ)። ሌሎች፣ ደግሞ ይህ ክፍል የሚናገረው ሕግን ሙሉ በሙሉ በመፈጸሙ፣ በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ ድነትን ስለ ሰጠው ስለ ክርስቶስ ነው ይላሉ (ዕብ 5፥9 ይመ)።

*10፥6-7፤* የብሉይ ኪዳን ጥቅስ የተጠቀሰው በእምነት የሚገኘውን ጽድቅ ምንነት ለመግለጽ ነው፤ ጽድቅን በእምነት መቀበል፣ ክርስቶስ ወደ ምድር የወረደውን ያህል ወይም ከሙታን የተነሣውን ያህል ከባድ ሆኖ፣ የተለየ ጥበብና ዕውቀት የሚጠይቅ አይደለም፤ በመሠረቱ ዘዳ 30፥12-13 የሚናገረው ስለ ሕግ ነው፤ እዚህ ላይ ጳውሎስ ይህን መሠረታዊ መርሕ ከክርስቶስ ጋር አገናኝቶ ተጠቅሞበታል።

10፥8 *ቃሉ በአጠገብህ ነው፤* በብሉይ ኪዳን ውስጥ "ቃል" ሲባል፣ በሕጉ ውስጥ ተጠቅሶ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል ነው። ጳውሎስ ይህን ክፍል "የእምነት ቃል" ከሆነው ከወንጌል ጋር ያዛምደዋል፤ የዚህ ክፍል ዋና ሐሳብም፣ የወንጌልን ቃል ማግኘት አስቸጋሪ እንዳልሆነ ለመግለጥ ነው። ጽድቅ የሚገኘው በሥራ ሳይሆን በእምነት ነው፤ ይህም በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር በነጻ ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆነ ሁሉ የተዘጋጀ ነው።

10፥9 *ኢየሱስ ጌታ ነው፤* በጥንት ጊዜ የክርስትና እምነት መግለጫ ሲሆን (ከ1ቆሮ 12፥3 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በጥምቀት ሥርዐት ጊዜ የሚነገር ሳይሆን አይቀርም። የእስራኤል አምላክ (ያህዌ) የሚለውን ስም ለመተርጐም፣ "ጌታ" የሚለው ቃል በግሪኩ

ትድናለህ:: 10የምትጸድቀው በልብህ አምነህ
ነው፤ የምትድነውም በአፍህ መስክረህ ነውና::
11መጽሐፍ እንደሚለው፣ “በእርሱ የሚያምን
ሁሉ አያፍርም::” 12በአይሁድና በአሕዛብ
መካከል ልዩነት የለም፤ አንዱ ጌታ የሁሉ
ጌታ ነውና፤ የሚለምኑትንም አብዝቶ ይባርካል፤
13“የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና::”
14ታዲያ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው
ይጠሩታል? ስለ እርሱስ ሳይሰሙ እንዴት
ያምኑበታል? ሰባኪ ሳይኖር እንዴት መስ
ማት ይችላሉ? 15ካልተላኩስ እንዴት መስበክ
ይችላሉ? ይህም፣ “የምሥራችን የሚያመጡ
እግሮች እንዴት ያማሩ ናቸው!” ተብሎ እንደ
ተጻፈው ነው::
16ነገር ግን የሰሙት ሁሉ የምሥራቹን
ቃል አልተቀበሉም፤ ኢሳይያስም፣ “ጌታ ሆይ፤
መልእክታችንን ማን አምኖአል?” ብሎአልና::
17እንግዲያስ እምነት የሚገኘው መልእክቱን
ከመስማት ነው፤ መልእክቱም በክርስቶስ
ቃል ነው:: 18ነገር ግን አልሰሙ ይሆን?
ብዬ እጠይቃለሁ፤ በእርግጥ ሰምተዋል፤

“ድምፃቸው በምድር ሁሉ፣
ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ተሰማ::”

19ደግሜም እጠይቃለሁ፤ እስራኤል አላስተ
ዋሉ ይሆን? በቅድሚያ ሙሴ እንዲህ ይላል፤
“ሕዝብ ባልሆኑት አስቀናችዋለሁ፤
ማስተዋል በሌለው ሕዝብ አስቈጣችዋለሁ”
20ኢሳያስም በድፍረት፣

“ላልፈለጉኝ ተገኘሁ፤
ላልጠየቁኝ ራሴን ገለጥሁላቸው” ይላል::
21ስለ እስራኤል ግን፣
“ወደማይታዘዝና እሺ ወደማይል ሕዝብ፣
ቀኑን ሙሉ እጄን ዘረጋሁ” ይላል::

## የእስራኤል ትሩፋን

11 እንግዲህ እግዚአብሔር ሕዝቡን ተዋቸ
ውን? ብዬ እጠይቃለሁ፤ በፍጹም!፤
እኔ ራሴ ከብንያም ነገድ፣ የአብርሃም ዘር የሆ
ንሁ እስራኤላዊ ነኝ:: 2እግዚአብሔር አስቀድሞ
ያወቃቸውን ሕዝብ አልጣላቸውም:: ኤልያስ
በእስራኤል ላይ ክስ ወደ እግዚአብሔር እንዴት
እንዳቀረበ፣ መጽሐፍ ስለ እርሱ ምን እንደ
ሚል አታውቁምን? 3“ጌታ ሆይ፤ ነቢያትህን
ገድለዋል፤ መሠዊያዎችህን አፍርሰዋል፤ እኔም
ብቻዬን ቀረሁ፤ ሊገድሉኝም ይፈልጋሉ::”
4እግዚአብሔር የሰጠው መልስ ግን ምን ነበር?
“ለበኣል ያልሰገዱትን ሰባት ሺህ ሰዎች ለራሴ
አስቀርቻለሁ::” 5በአሁኑ ጊዜም እንደዚሁ
በጸጋ የተመረጡ ትሩፋን አሉ:: 6እንግዲህ
በጸጋ ከሆነ በሥራ አይደለም፤ በሥራ ቢሆ
ንማ ኖሮ ጸጋ፣ ጸጋ መሆኑ በቀረ ነበር::[x]
7እንግዲህ ምንድን ነው? እስራኤል አጥ
ብቀው የፈለጉትን አላገኙትም፤ የተመረጡት
ግን አገኙት፤ የቀሩትም ልባቸው ደነደነ፤

[x]6 አንዳንድ ቅጆች *በሥራ ቢሆንማ ኖሮ ጸጋ መሆኑ በቀረ ነበር፤ በጸጋ ከሆነም ሥራ፣ ሥራ መሆኑ ይቀራል::* ይላሉ

ዮሐ13፥13፤3፥15፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ 11፥14
10፥11 ኢሳ28፥16፤ ሮሜ9፥33
10፥12 ማቴ28፥18፤ ሮሜ3፥22: 29፤
10፥13 ኢዩ2፥32፤ ሐሥ2፥21፤
10፥15 ኢሳ52፥7፤ ናሆ1፥15
10፥16 ኢሳ53፥1፤ ዕብ 4፥2፤ዮሐ12፥38
10፥17 ገላ3፥2:5፤ ቈላ 3፥16
10፥18 መዝ19፥4፤ ማቴ24፥14፤ሮሜ1፥8፤ ቈላ1፥6:23፤1ተሰ1፥8
10፥19 ዘዳ32፥21፤ ሮሜ11፥11:14፤
10፥20 ኢሳ65፥1፤ ሮሜ 9፥30
10፥21 ኢሳ65፥2፤ ኤር35፥17
11፥1 ዘሌ26፥44፤ 1ሳሙ12፥22፤ መዝ94፥14፤ ኤር31፥37፤33፥24-26፤ 2ቆሮ11፥22፤ፊል3፥5
11፥2 ቍ1፤ ሮሜ8፥29
11፥3 1ነገ19፥10:14
11፥4 1ነገ19፥18
11፥5 ሮሜ9፥27፤ 3፥24
11፥6 ሮሜ4፥4
11፥7 ቍ25፤ ሮሜ9፥18፤9፥31፤

የብሉይ ኪዳን ቅጅ ውስጥ ከ6000 ጊዜ በላይ ተጠቅሶአል፤ ጳውሎስም ጌታ የሚለውን ቃል እዚህ ላይ ለኢየሱስ ሲጠቀም አምላክነቱን ለማሳየት እንደ ሆነ ግልጽ ነው:: *በልብህ* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “ልብ” የስሜትና የፍቅር ማእከል ብቻ ሳይሆን፣ የማስተዋል ችሎታና የፈቃድ መቀመጫ ነው:: *እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው፤* ይህ የክርስትና እምነት መሠረት (1ቆሮ 15፥4:14:17 *ይመ*) እና የሐዋርያት ትምህርት ዐቢይ ሐሳብ ነው (ሐሥ 2፥31-32፤ 3፥15፤ 4፥10፤ 10፥40 *ይመ*):: ክርስቲያኖች ኢየሱስ በምድር ላይ እንደ ነበር ብቻ ሳይሆን አሁንም በክብሩ እንደሚኖር ያምናሉ:: *ትድናለህ* ይህ ቃል በወደፊት ጊዜ መጻፉ፣ ጳውሎስ ስለ መጨረሻው መዳን፣ ማለትም በመጨረሻው ቀን ሊሆን ስላለው ድነት በማሰብ መሆኑን ያመለክታል::

*10፥10፤* ድነት፣ ውስጣዊውን የልብ እምነትና ውጫዊውን የአፍ ምስክርነት ያካትታል::

10፥12 *በአይሁድና በአሕዛብ መካከል ልዩነት የለም፤* ሁለቱም ለመዳን በጌታ ማመን ስላለባቸው ነው (ቍ 13 *ይመ*)::

*10፥13፤* ጴጥሮስ ይህንኑ ክፍል (ኢሳ 2፥32) በመጥቀስ በጰንጠቆስጤ ቀን (ሐሥ 2፥21) ተናግሮአል::

*10፥14-15፤* አይሁድ ወንጌልን ለመስማትና ለጥሪውም መልስ ለመስጠት ጨርሶ አመቺ ዕድል አላገኙም የሚል አስተያየት ምናልባት ሊኖር ስለሚችል፣ ጳውሎስ ለመዳን አስፈላጊ የሆኑትን ነጥቦች ያቀርባል፡- 1) ከእግዚአብሔር የተላከ ሰባኪ፣ 2) ቃሉን ማወጅ፣ 3) ቃሉን መስማት፣ 4) በቃሉም ማመን ናቸው:

*10፥15፤ የምሥራችን የሚያመጡ እግሮች እንዴት ያማሩ ናቸው::* ይህ በባቢሎን አገር በምርኮ የነበሩት አይሁድ ነጻ የሚወጡ መሆናቸውን በመግለጽ የምሥራች የተናገሩትን ከሚገልጠው ከኢሳ 52፥7 የተወሰደ ነው:: እዚህ ላይ ከኀጢአት እስራት ነጻ መውጣትን ከሚሰብኩ የወንጌል መልእክተኞች ጋር ተዛምዶአል::

10፥17 *በክርስቶስ ቃል፤* ክርስቶስን የሚያመለክት ወንጌል ወይም ክርስቶስ በመልእክተኞቹ የተናገረው መልእክት ነው::

10፥18 *ድምፃቸው፤* ሰማያት ለእግዚአብሔር ክብር የሚሰጡትን ምስክርነት የሚያመለክት ሲሆን፣ ከመዝሙር 19፥4 የተወሰደ ጥቅስ ነው:: እዚህ ላይ ግን “ድምፃቸው” ሲል የወንጌል ሰባኪ ዎችን ያሳያል፤ የወንጌል ሰባኪዎች ቃሉን ይዘው በሁሉም ቦታ ስለ ዞሩ፣ እስራኤል ወንጌልን ላለመስማቷ ማመካኛ እንደ ሌላት ያስገነዝባል:: በመጀመሪያ በፍጥረት ውስጥ የእግዚአብሔርን መገለጥ ለማሳየት የተጻፉ እነዚህ ቃሎች፣ የወንጌል ቃል በሰፋት መሰበኩን የሚገልጹ ናቸው፤ ጳውሎስም እነዚህን ቃሎች አይሁድ የድነት ቃል ለመስማት ብዙ ዕድል እንደ ነበራቸው ለመግለጽ ይጠቀምባቸዋል::

10፥19 *እስራኤል አላስተዋሉ ይሆን?* ከዚህ ጥያቄ ቀጥሎ ያለው ሐሳብ (ዘዳ 32፥21)፣ አይሁድ እንደማያስተውሉ አድርገው የሚቈጥራቸው አሕዛብ እንኳ መረዳታቸውን በመጥቀስ ይህን ጥያቄ ይመልሳል:: አሕዛብ መልእክቱን የተገነዘቡ ከሆነ፣ አይሁድም የተረዱት ለመሆኑ አያጠራጥርም:: *ሕዝብ ባልሆኑት፤* ለእግዚአብሔር ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ ተለይተው ያልነበሩትን አሕዛብ ያመለክታል::

*10፥21፤* እስራኤል ስለ መጣሏ ተጠያቂ የምትሆነው ራሷ እስራኤል ናት፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእርሷ የሚፈልገውን እምነት ሊያገኝባት አልቻለም::

11፥1 *ተዋቸውን?* ከአይሁድ ሕዝብ መካከል ታማኝ የሆኑ ትሩፋን ምን ጊዜም ስለሚኖሩት፣ እግዚአብሔር ጠቅላላ ሕዝቡን አልጣለም::

11፥2 *እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን፤* የ8፥29 ማብ ይመ::

11፥5 *ትሩፋን፤* በኤልያስ ዘመን እንደ ነበሩ ሁሉ በጳውሎስም ዘመን ትሩፋን ነበሩ:: ክሕደት እየተስፋፋ የሄደበት ዘመን ቢሆንም ታማኝ የሆኑ የአይሁድ ትሩፋን ነበሩ:: *በጸጋ የተመረጡ፤* ለእነዚህ ትሩፋን መኖር ምክንያት የሆነው የራሳቸው መልካም ሥራ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ጸጋ ነበር::

11፥7 *እስራኤል አጥብቀው የፈለጉትን፤* ብዙዎች እስራ ኤላውያን ማግኘት ያልቻሉት፣ በእግዚአብሔር ፊት በጸደቀ ሕይ ወት መቆምን ነው:: *የተመረጡት፤* ከአይሁድ መካከል ታማኞች የሆኑትን ትሩፋን ያመለክታል:: *ልባቸው ደነደነ፤* እስራኤላውያን የእምነትን መንገድ ለመቀበል ፈቃደኞች ስላልሆኑ (9፥31-32 ይመ)፣ እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ ነገር ልባቸው ፈጽሞ እንዲ ደነድን አደረገ (የኢሳ 6፥8-10 ማብ ይመ)::

11፥8 *እስከዚህ ቀን ድረስ፤* ከኢሳይያስ ዘመን እስከ

8እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤
"ዐይናቸው እንዳያይ፣
ጆሮአቸውም እንዳይሰማ፣
እግዚአብሔር እስከዚህ ቀን ድረስ፣
የድንዛዜ መንፈስ ሰጣቸው::"
9ዳዊትም አለ፤
"ማእዳቸው አሽክላና ወጥመድ፣
ዕንቅፋትና ቅጣት ይሁንባቸው::
10ዐይኖቻቸው እንዳያዩ ይጋረዱ፤
ወገባቸውም ለዘላለም ይጕበጥ::"

## የተዳቀሉ ቅርንጫፎች

11ተመልሰው እስከማይድኑ ድረስ ተሰናከሉን?
ብዬ እንደ ገና እጠይቃለሁ፤ ከቶ አይደለም፤
ይልቁንም እስራኤልን ለማስቀናት ሲባል
በእነርሱ መተላለፍ ምክንያት ድነት ለአሕ
ዛብ መጥቶአል:: 12ነገር ግን የእነርሱ መተላለፍ
ለዓለም በረከት ከሆነ፣ ውድቀታቸውም ለአሕ
ዛብ በረከት ከሆነ፣ ሙላታቸው ምን ያህል
ታላቅ በረከት ያመጣ ይሆን?
13አሕዛብ ሆይ፤ ለእናንተ እናገራለሁ፤
የአሕዛብ ሐዋርያ እንደ መሆኔ መጠን አገ
ልግሎቴን በትጋት እፈጽማለሁ፤ 14ይኸውም
የገዛ ወገኖቼን እንዲቀኑ አነሣሥቼ ከእነርሱ
ጥቂቱን ለማዳን ተስፋ በማድረግ ነው::
15የእነርሱ መተው ለዓለም ዕርቅን ካስገኘ፣
ተቀባይነት ማግኘታቸውማ ከሞት መነሣት
ነው ከማለት በቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?
16በኵር ሆኖ የቀረበው የቡሖው ክፍል ቅዱስ
ከሆነ፣ ቡሖው ደግሞ ቅዱስ ነው፤ ሥሩ ቅዱስ
ከሆነ፣ ቅርንጫፎቹም ቅዱሳን ናቸው::
17ከቅርንጫፎቹ አንዳንዶቹ ቢሰበሩ፣ አን
ተም የበረሓ ወይራ ሆነህ ሳለ በሌሎቹ
መካከል ገብተህ ከተጣበቅህና ከወይራው ዘይት
ሥር የሚገኘውን በረከት ተካፋይ ከሆንህ፣
18በእነዚያ ቅርንጫፎች ላይ አትኵራራ::
ብትኰራ ግን ይህን አስተውል፤ አንተ ሥሩን
አትሸከምም፤ ሥሩ ግን አንተን ይሸከምሃል
እንጂ:: 19እንግዲህ፣ "ቅርንጫፎች የተሰበሩት
እኔ እንድገባ ነው" ትል ይሆናል:: 20ትክክል
ነው፤ እነርሱ የተሰበሩት ካለማመን የተነሣ
ነው፤ አንተም በእምነት ቆመሃል፤ ፍራ
እንጂ ትዕቢተኛ አትሁን:: 21እግዚአብሔር በተ
ፈጥሮ ቅርንጫፎች ለሆኑት ካልራራላቸው፣
ለአንተም አይራራልህምና::
22እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭካኔ
ተመልከት፤ ጭካኔውም በወደቁት ላይ ነው፤
ቸርነቱ ግን በቸርነቱ ውስጥ እስካለህ ድረስ
ለአንተ ነው፤ ያለዚያ ግን አንተም ትቈረ
ጣለህ:: 23እነርሱም ባለማመናቸው ጸንተው

11፥8 ዘዳ29፥4፤ ኢሳ 29፥10፤ ማቴ13፥13-15፤
11፥10 ቍ8፤ መዝ 69፥22:23
11፥11 ቍ1፤14፤ ሐሥ13፥46፤ ሮሜ10፥19
11፥12 ቍ25
11፥13 ሐሥ9፥15
11፥14 ቍ11፤ ማቴ1፥21፤ሉቃ2፥11፤ ዮሐ3፥17፤ሐሥ4፥12፤ 16፥31፤ሮሜ10፥19፤ 1ቆሮ1፥21፤10፥33፤ 1ተሰ2፥16፤ 1ጢሞ2፥4፤ቲቶ3፥5
11፥15 ሉቃ15፥24፡32፤ሮሜ5፥10፤
11፥16 ዘሌ23፥10፡17፤ዘኍ15፥18-21
11፥17 ኤር11፥16፤ ዮሐ15፥2፤ሐሥ 2፥39፤ኤፌ2፥11-13
11፥18 ዮሐ4፥22
11፥20 1ቆሮ10፥12፤ 2ቆሮ1፥24፤1ጢሞ6፥17፤ 1ጴጥ1፥17
11፥22 ዮሐ15፥21 ሮሜ2፥4፤1ቆሮ15፥2፤ ቈላ1፥23፤ዕብ3፥6፤
11፥23 2ቆሮ3፥16

ጳውሎስ ዘመን ድረስ፣ አይሁድ በድንዛዜ የተያዙ ነበሩ::

*11፥9-10፤* ከመዝ 69፥22-23 የተወሰደው ይህ ጥቅስ ዳዊት ስለ ጠላቶቹ የተናገረው ሊሆን ይችላል፤ እዚህ ላይ ግን ጳውሎስ ከእግዚአብሔር የሆነው የልብ ማደንደን የሚያስከትለውን ውጤት ለመግለጽ ተጠቅሞበታል::

11፥11 *በእነርሱ መተላለፍ፤* አይሁድ ወንጌልን እንዳል ፈለጉ ያመለክታል:: *እስራኤልን ለማስቀናት፤* ቍ 14፥ 10፥19 ይመ::

11፥12 *ለዓለም በረከት፤* "ለአሕዛብ በረከት" ከሚለው ሐሳብ ጋር አንድ ሲሆን፣ ይህም አይሁድ ወንጌልን ባለመቀበላቸው ላመኑት አሕዛብ የተሰጠውን ታላቅ የድነት በረከት ያመለክታል:: የአይሁድ ወንጌልን አለመቀበል፣ ሐዋርያትን ወደ አሕዛብ ዘወር እንዲሉ አደረጋቸው (ሐሥ 13፥46-48፤ 18፥6 ይመ):: *ውድቀታቸውም፤* "የእነርሱ መተላለፍ" ከሚለው ሐሳብ ጋር አንድ ሲሆን (የቍ 11 ማብ ይመ)፣ ይህ መተላለፍ በሚያስከትለው ጕዳት ላይ ያተኵራል:: *ታላቅ በረከት፤* የቍ 15 ማብ ይመ:: *ሙላታቸው፤* የእስራኤልን መዳን የሚያመለክት ቃል ነው (ቍ 26፥27 ይመ፤ እንዲሁም በቍ 25 ላይ "የአሕዛብ ሙላት" የሚለውን ይመ)::

11፥13 *የአሕዛብ ሐዋርያ፤* 1፥5 ሐሥ 9፥15፤ ገላ 1፥16፤ 2፥7:9 ይመ::

11፥15 *የእነርሱ መተው፤* ለጊዜው አይሁድ በእግዚአብሔር ዘንድ በከፊል መገለላቸውን ያመለክታል:: *ለዓለም ዕርቅን፤* "ለዓለም በረከት" ከሚለው ጋር የሚቀራረብ ሐሳብ ነው (የቍ 12 ማብ ይመ):: *ተቀባይነት ማግኘታቸውማ፤* በቍ 12 ከተጠቀሰው "ታላቅ በረከት" ከሚለው ሐሳብ ጋር አንድ ነው:: ከድነት ጋር በመያያዝ በቅደም ተከተል የተፈጸሙ ሁኔታዎች የእስራኤል "መተላለፍ" እና "ውድቀት" (ቍ 12) ለአሕዛብ መዳን ይሆናል፤ የአሕዛብም መዳን እስራኤልን ያስቀናል፤ የእስራኤል የልብ ድንዳኔ ሲወገድም ሙላታቸው እውን ይሆናል (ቍ 12)፤ የእነርሱም ሙላት ለአሕዛብ ታላቅ በረከት ያስገኛል:: ነገር ግን እዚህ ላይ ጳውሎስ ከሙታን ተለይቶ ሕይወትን ማግኘት በማለት የገለጸው፣ ለአሕዛብ ታላቅ በረከት የሆነው ምንድነው (ቍ 12)? ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ሦስት አስተያየቶች ማቅረብ ይቻላል:: እነርሱም 1) ከዚህ በፊት ያልታየ መንፈሳዊ መነቃቃት በዓለም ውስጥ መከሠት፣ 2) በሙታን ትንሣኤ ጊዜ ድነት ሙሉ በሙሉ መፈጸሙ፣ 3) የአይሁድ መለወጥ የሙታን ትንሣኤ ያህል አስደሳችና የከበረ መሆኑን የሚገልጽ ምሳሌያዊ አነጋገር ሲሆን፣ ይኸውም ለዓለም ታላቅ በረከት ያስገኛል:: ከእስራ ኤል መንፈሳዊ ዳግም ልደት በፊት የአሕዛብ ሙላት ስለሚሆን (ቍ 25) ከእነዚህ ከሦስቱ ሐሳቦች የመጀመሪያውን ትክክል ነው ብሎ መቀበል አስቸጋሪ ነው:: የአሕዛብ መዳን በዚያን ጊዜ የሚጠ ቃለል በመሆኑ፣ ከዚህ በፊት ያልታየ መንፈሳዊ መነቃቃት የሚለው ሐሳብ ተቀባይነት የለውም:: ይህ ክፍል፣ በቀጥታ ስለሚሆን የሥጋ ትንሣኤ የሚያወሳ ስላልሆነ፣ ከላይ የተጠቀሰው ሁለተኛው አስተያየት ተቀባይነት የለውም::

*11፥16፤* የዚህ ጥቅስ የመጀመሪያ ክፍል፣ በዘኍ 15፥17-21 ያለውን ሐሳብ ያመለክታል:: ከዕርሻ ከተገኘው የመጀመሪያው ምርት የሚሠራው የቡሖ ክፍል ለእግዚአብሔር ይቀርብ ነበር:: ይህም ቡሖውን ሁሉ ይቀድሳል:: *በኵር፤* የነገድ አባቶችን ያመለክታል:: *ቡሖው፤* የአይሁድ ሕዝብ ምሳሌ ነው:: *ቅዱስ፤* አይሁድ ሁሉ ጻድቃን ናቸው ማለት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ስለ እነርሱ በሰጠው ቃል ኪዳን ታማኝ ነው ማለት ነው (3፥3-4 ይመ):: እስራኤል ለጊዜው የተገለለች ብትሆንም፣ ጳውሎስ ስለ ወደፊት ሁኔታዋ አስቀድሞ አይቶአል:: *ሥሩ፤* የነገድ አባቶችን ያመለክታል:: *ቅርንጫፎቹም፤* አይሁድ ናቸው::

11፥17 *ከቅርንጫፎቹ፤* ከአይሁድ ወገን የሆነ ግለሰብን ያመለክታል:: *የበረሓ ወይራ፤* ከአሕዛብ ወገን ክርስቲያን የሆኑትን ያመለክታል:: *ከተጣበቅህና፤* ይህን ለማድረግ የተለመደው መንገድ፣ ተተክሎ ከበቀለው መልካም ዛፍ የተቈረጠውን ቅርንጫፍ ወይም ቀምበጥ፣ የበረሓ ዛፍ በሆነው ግንድ ላይ ባለው ክፍተት ማስገባት ነው:: ሆኖም በቍ 17-24 ላይ አሕዛብን የሚወክለው የበረሓ ዛፍ ቅርንጫፍ፣ ተተክሎ በበቀለው መልካም ዛፍ ላይ እንደሚጣበቅ የተገለጸበት ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ከተፈጥሮአዊ አሠራር ጋር የሚቃረን ነው (ቍ 24)፤ የዚህ ክፍል ዋና ሐሳብም እንዲህ ዐይነት አሠራር የተለመደ እንዳልሆነ ሁሉ፣ የአሕዛብም በእግዚአብሔር መንግሥት ከአይሁዳውያን ጋር አንድ መሆን እንዴት እንደ ሆነ ለማሳየት ነው:: በመሠረቱ ከእንዲህ ዐይነቱ መጣበቅ ፍሬ አይገኝም:: *ከወይራው፤* የነገድ አባቶችን ያመለክታል፤ ወይራ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይወክላል::

11፥19 *ቅርንጫፎች፤* የማያምኑትን አይሁድ ያመለክታል::

11፥20 *ፍራ፤* "እግዚአብሔርን መፍራት" ስለሚለው፣ የዘፍ 20፥11 ማብ፣ እንዲሁም ምሳ 3፥7፤ ፊል 2፥12-13፤ ዕብ 4፥1 "ተጠንቀቅ" የሚለውን፤ 1ጴጥ 1፥17 ይመ::

11፥22 *የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭካኔ፤* ከእግዚአብሔር የሆነ ትክክለኛ የእምነት ትምህርት እነዚህን ሁለት ሐሳቦች ያካተተ መሆን አለበት:: ቸርነቱን ብንዘነጋ፣ እግዚአብሔር ምሕ ረት የሌለው ጨካኝ ገዥ ይመስላል፤ ጭካኔውን ብንዘነጋ ደግሞ፣ ገደብ የሌለው ፍቅር በማሳየት ቸርነት የሚያደርግ አባት ይመስላል::

11፥23 *እግዚአብሔር መልሶ ሊያስገባቸው ይችላልና፤*

ባይኖሩ፣ ተመልሰው ይገባሉ፤ እግዚአብሔር
መልሶ ሊያስገባቸው ይችላልና:: 24የበረሓ
ከሆነው የወይራ ዛፍ የተቈረጥህና ተፈጥሮህ
ወዳልሆነው ወደ መልካሙ ወይራ የገባህ
ከሆንህ፣ በተፈጥሮአቸው ቅርንጫፎቹ የሆኑት
እነዚህ ወደ ራሳቸው ወይራ ዛፍ መግባታቸ
ውማ ምን ያህል ይሆን?

## እስራኤል ሁሉ ይድናል

25ወንድሞች ሆይ፤ ልባሞች የሆናችሁ እንዳ
ይመስላችሁ፣ ይህን ምስጢር ሳታውቁ
እንድትቀሩ አልፈልግም፤ የአሕዛብ ሙላት
እስኪገባ ድረስ፣ እስራኤል በከፊል በድን
ዳኔ ውስጥ ዐልፋለች:: 26ስለዚህ እስራኤል
ሁሉ ይድናሉ፤ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤

"አዳኝ ከጽዮን ይወጣል፤
ከያዕቆብም ክፋትን ያስወግዳል::
27ኀጢአታቸውንም ሳስወግድ፣
ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳኔ ይህ ነው::"[ጀ]

28እንደ ምሥራቹ ቃል ለእናንተ ሲባል ጠላ
ቶች ናቸው፤ እንደ ምርጫ ከሆነ ግን፣ ለአ
ባቶች ሲባል የተወደዱ ናቸው፤ 29የእግዚአብሔር
ስጦታና ጥሪ ጸጸት የለበትም:: 30እናንተም
ቀድሞ ለእግዚአብሔር የማትታዘዙ እንደ ነበራ
ችሁ፣ ከእነርሱ አለመታዘዝ የተነሣ አሁን
ምሕረት እንዳገኛችሁ ሁሉ፣ 31እግዚአብሔር
ለእናንተ ምሕረት ከማድረጉ የተነሣ፣ እነር
ሱም ምሕረት ያገኙ ዘንድ አሁን[1] የማይታ
ዘዙ ልጆች ሆነዋል፤ 32እግዚአብሔር ለሁሉም ምሕ
ረት ያደርግ ዘንድ ሰውን ሁሉ ባለመታዘዝ
ዘግቶታልና::

## ውዳሴ

33የእግዚአብሔር የጥበቡና የዕውቀቱ ባለ
ጠግነት[ጠ] እንዴት ጥልቅ ነው!
ፍርዱ አይመረመርም፤
ለመንገዱም ፈለግ የለውም!
34"የጌታን ልብ ያወቀ ማነው?
አማካሪውስ የነበረ ማን ነው?"
35 "እግዚአብሔር መልሶ እንደ ሰጠው፣
ለእግዚአብሔር ያበደረ ከቶ ማን ነው?"
36ሁሉም ከእርሱ፣ በእርሱ፣ ለእርሱ ነውና፤
ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን::

11፥24 ኤር11፥16
11፥25 ቍ7፤ ሉቃ21፥24፤ ሮሜ1፥13፤9፥18፤ 12፥16፤16፥25፤ 1ቆሮ10፥1፤12፥1፤ 2ቆሮ1፥8፤1ተሰ4፥13፤
11፥26 ኢሳ45፥17፤ ኤር31፥34
11፥27 ኢሳ59፥20: 21፤27፥9፤ ዕብ 8፥10: 12
11፥28 ዘዳ7፥8፤ 10፥15፤ሮሜ5፥10፤ ሮሜ9፥5
11፥29 ሮሜ 8፥28፤ዕብ7፥21
11፥30 ኤፌ2፥2
11፥32 ሮሜ3፥9
11፥33 መዝ92፥5፤ 139፥6፤ኢዮ5፥9፤ 11፥7፤መክ8፥17፤ ኢሳ40፥28፤ሮሜ2፥4፤ ኤፌ3፥10፤ቈላ2፥3፤
11፥34 ኢዮ15፥8፤ ኢሳ40፥13:14፤ ኤር 23፥18፤36፥22፤ 1ቆሮ2፥16
11፥35 ኢዮ41፥11፤ 35፥7
11፥36 ሮሜ16፥27፤

[ጀ]27 ወይም *ይህ ይሆናል*
[1]31 አንዳንድ ቅጆች *አሁን የሚለው ቃል የላቸውም*
[ጠ]33 ወይም *ባለጠግነቱ፣ ጥበቡና እውቀቱ*

አይሁድ ተስፋ እንዳላቸው ጳውሎስ ይገልጻል፤ ይኸውም "እግዚአብሔር ይችላል" (ማቴ 19፥26፤ ማር 10፥27፤ ሉቃ 18፥27 *ይመ*) በማለት ነው::

11፥24 *ተፈጥሮህ ወዳልሆነው*፤ እንዲህ ዐይነቱ መጣበቅ የተለመደ እንዳልሆነ ጳውሎስ አስተውሎአል (የቍ 17 ማብ *ይመ*):: አሕዛብ በእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ውስጥ መግባታቸው ተፈጥሮአዊ የሆነውን አሠራር የሚቃረን ነው (ከኤፌ 2፥12 ጋር *ያነጻጽሩ*):: በዚህ ጥቅስ ውስጥ የቀረበው ሐሳብ ስለ አትክልት ሁኔታ ከሚናገር ይልቅ፣ ስለ መንፈሳዊ ሁኔታ እንደሚያብራራ ግልጽ ነው:: ከአትክልት አተካከል ሙያ አንጻር ሲታይ፣ የተገነጠለን ቅርንጫፍ መልሶ ወደ ነበረበት ዛፍ መልሶ በማስገባት እንዲጣበቅ ማድረግ አስቸጋሪ ነው:: ነገር ግን አይሁድ ከታሪክና ከመንፈሳዊ አቅጣጫ ሲታዩ የዋናው ዛፍ ክፍል ናቸው፤ ስለዚህ "የራሳቸው ወደ ሆነው የወይራ ዛፍ በቀጥታ እንዲገቡ" ይደረጋል::

11፥25 *ምስጢር፤* ጳውሎስ በነበረበት ዘመን፣ የምስጢር ሃይማኖቶች የተባሉት ለጥቂቶች ብቻ የሚገለጸውን ጕዳይ፣ ለማሳየት፣ በግሪኩ "ምስጢር" የሚለውን ቃል ይጠቀሙ ነበር፤ ጳውሎስ በበኩሉ ቀደም ሲል የተሰወረውን ወይም ያልተገለጠውን፣ አሁን ግን ሁሉም ያውቁትና ይረዱት ዘንድ በእግዚአብሔር የተገለጸውን ለማመልከት ይህን ቃል ተጠቅሞአል (16፥25፤ 1ቆሮ 2፥7፤ 4፥1፤13፥2፤ 14፥2፤ 15፥51፤ ኤፌ 1፥9፤ 3፥3-4:9፤ 5፥32፤ 6፥19፤ ቈላ 1፥26-27፤ 2፥2፤ 4፥3፤ 2ተሰ 2፥7፤ 1ጢሞ 3፥9:16 *ይመ*):: ይህ ቃል (ምስጢር)፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ይገልጣል 1) ስለ ትስብእት (የክርስቶስ ሰው መሆን)፣ (1ጢሞ 3፥16 እና ማብ *ይመ*):: 2) ስለ ክርስቶስ ሞት (1ቆሮ 2፥1፣ አማራጭ ትርጕሙን፤ 2፥7 "ምስጢራዊ ጥበብ" *ይመ*):: 3) እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር በክርስቶስ ለመጠቅለል ስላለው ዐላማ (ኤፌ 1፥9)፣ በተለይም አይሁድንና አሕዛብን በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማስገባት ሳላለው ዕቅድ (ኤፌ 3፥3-6)፣ 4) በሙታን ትንሣኤ ጊዜ ስለሚኖረው ለውጥ (1ቆሮ 15፥15)፣ እንዲሁም 5) አይሁድና አሕዛብ ሁለቱም ለተወሰነ ጊዜ ከሚያሳዩት አለመታዘዝ በኋላ፣ እግዚአብሔር በምሕረቱ ወደ መንግሥቱ እንዲጨመሩ ለማድረግ ስላለው ዐላማ (ቍ25):: *ልባሞች የሆናችሁ እንዳይመስላችሁ፤* እግዚአብሔር አሕዛብን በታላቅ የመዳን ዕቅዱ ውስጥ ለማስገባት ያለው ምሕረትን የተሞላ ዐላማው ትሑት የሚያደርግ እንጂ በትዕቢት እንዲሞሉ የሚያደርግ አይደለም:: *በከፊል፤* የእስራኤል ልበ ደንዳናነት በከፊል እንጂ ሙሉ በሙሉ አይደለም:: *እስኪገባ፤* የእስራኤል ልበ ደንዳናነት ለጊዜው እንጂ ቋሚ ሆኖ የሚቈይ አይደለም:: *የአሕዛብ ሙላት፤* የተመረጡትን አሕዛብ ጠቅላላ ቍጥር የሚያመለክት ነው::

11፥26 *ስለዚህ፤* እስራኤል ሁሉ የሚድኑበት መንገድ ይህ እንደ ሆነ የሚያሳይ የአጽንዖት ቃል ነው:: *እስራኤል ሁሉ፤* የዚህ ሐረግ ሦስት ዋና ትርጓሜዎች 1) ከየትውልዱ የተመረጡት ጠቅላላ አይሁድ ቍጥር፣ ይህም የእስራኤል "ሙላት" (ቍ2) ከሚለው ሐሳብ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ፣ "የአሕዛብ ሙላት" (ቍ25) ከሚለውም ጋር ይመሳሰላል፤ 2) ከየትውልዱ የተመረጡት አይሁድና አሕዛብ ጠቅላላ ቍጥር 3) በመጨረሻው ትውልድ የነበሩት ብዙኃኑ አይሁድ ናቸው:: *ይድናሉ፤* እንደ ማንኛውም ሰው የአይሁድ መዳን የተመሠረተው በተሰቀለውና ከሙታን በተነሣው በኢየሱስ ክርስቶስ በግል በማመን ነው:: *አዳኝ ከጽዮን ይወጣል፤* ጥቅሱ የተወሰደው፣ አዳኝ ወይም "ቤዛ" እግዚአብሔር እንደ ሆነ የሚያመለክት ከሚመስለው ከኢሳይያስ 59፥20 ነው:: ጥንታዊው የአይሁድ የሕግ መጽሐፍ (ታልሙድ)፣ ይህ ክፍል ስለ መሲሕ የሚናገር መሆኑን ይቀበላል፤ ጳውሎስም፣ በዚሁ መንገድ እንደ ተጠቀመበት ይታያል:: *ከጽዮን፤* የገላ 4፥26 ማብ *ይመ*::

11፥27 *ኪዳኔ፤* በኤር 31፥31-34 ላይ የተጠቀሰውን አዲሱን ኪዳን ያመለክታል:: *ኀጢአታቸውንም ሳስወግድ፤* ኤር 31፥34፤ ዘካ 13፥1 *ይመ*:: ለአሕዛብ የሆነ መዳን የኀጢአትን ይቅርታ እንደሚያካትት ሁሉ አይሁድም በሚድኑበት ጊዜ በእግዚአብሔር ምሕረት ይቅርታን ያገኛሉ፤ ይቅርታውም በሚገቡት ንስሓና በሚኖራቸው እምነት ላይ ብቻ የተመሠረተ ነው (ቍ 23፤ ዘካ 12፥10-13፥1 *ይመ*)::

11፥28 *ጠላቶች ናቸው፤* ይህም የሚሆነው ለጊዜው ነው:: *ለእናንተ ሲባል፤* በቍ 11 ላይ ተገልጾአል:: *ለአባቶች ሲባል የተወደዱ፤* ለአይሁድ ሕዝብ ሁሉ ከአባቶች የተላለፈ መልካም ነገር በመኖሩ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በፍቅር እስራኤልን በመምረጡና ይህም ምርጫ የማይለወጥ በመሆኑ ነው::

11፥29 *የእግዚአብሔር ስጦታና ጥሪ ጸጸት የለበትም፤* እግዚአብሔር በሚያደርገው ጥሪ አይጸጸትም:: እስራኤል አሁንም እንኳ ባለማመን ደረጃ ላይ ብትገኝም፣ የእግዚአብሔር ዐላማ በእርሷ ይፈጸማል::

11፥32 *ሰውን ሁሉ፤* እስከ አሁን ድረስ በቀረበው ሐሳብ ላይ ሁለት ወገኖችን፣ ማለትም አይሁድንና አሕዛብን ያመለክታል:: እግዚአብሔር ለሁለቱም ወገኖች ምሕረትን ያደርግ ዘንድ፣ እያንዳንዳቸው ባለመታዘዝ ዘመን ውስጥ ዐልፈዋል:: እዚህ ላይ ጳውሎስ በምንም መንገድ በጅምላ ስለ መዳን ማስተማሩ አይደለም::

*11፥33-36፤* ይህኛውን የሮሜ ክፍል ለማጠቃለል የተጻፈው ውዳሴ፣ አይሁድንም አሕዛብንም ለማዳን ያለው ታላቅ ዕቅድ፣ ጥልቅ በሆነው ጥበቡና ዕውቀቱ እንዲፈጸም ሳደረገው ለእግዚአብሔር ጳውሎስ ያቀረበውን ምስጋና ያካተተ ነው::

## ሕያው መሥዋዕት

12 እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታ
ችሁን ቅዱስና ለእግዚአብሔርን ደስ
የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ
ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምና
ችኋለሁ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀ
ርቡት[ሠ] አምልኮአችሁ ነው። 2 መልካም፣ ደስ
የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ
ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ
በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን
ዓለም አትምሰሉ።
3 እግዚአብሔር በሰጣችሁ እምነት መጠን ራሳ
ችሁን በአግባቡ መዝኑ እንጂ፣ ከሆናችሁት
በላይ ራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንዳታስቡ
በተሰጠኝ ጸጋ እያንዳንዳችሁን እመክራለሁ።
4 እያንዳንዳችን በአንዱ አካላችን ብዙ ብልቶች
እንዳሉን፣ እነዚህም ብልቶች አንድ ዐይነት
ተግባር እንደ ሌላቸው ሁሉ፣ 5 እንዲሁም
እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል
ነን። እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን።
6 እንደ ተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች
አሉን፤ ለአንዱ የተሰጠው ስጦታ ትንቢት
መናገር ከሆነ፣ እንደ እምነቱ መጠን[ለ] ይና
ገር። 7 ማገልገል ቢሆን ያገልግል፤ ማስተ
ማርም ከሆነ ያስተምር፤ 8 መምከር ከሆነ
ይምከር፤ ለሌላቸው መለገስ ከሆነም አብዝቶ
ይለግስ፤ ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተ
ዳድር፤ ምሕረት ማድረግ ከሆነም በደስታ
ይማር።

## ፍቅር

9 ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን፤ ክፉ
የሆነውን ሁሉ ተጸየፉ፤ በጎ ከሆነው ነገር
ጋር ተቈራኙ። 10 እርስ በርሳችሁ በወንድማ
ማች መዋደድ አጥብቃችሁ ተዋደዱ፤ አንዱ
ሌላውን ከራሱ በማስበለጥ እርስ በርሳችሁ
ተከባበሩ። 11 ጌታን ለማገልገል በመንፈስ
የጋላችሁ ሁኑ እንጂ ከዚህ ትጋት ወደ ኋላ
አትበሉ። 12 በተስፋ ደስተኞች ሁኑ፤ በመከራ

1ቆሮ8፥6፤11፥12፤
ኤፌ3፥21፤
ቈላ1፥16፤
1ጢሞ1፥17፤
1ጴጥ5፥11፤ዕብ2፥10፤
ይሁ1፥25፤ራእ5፥13፤
7፥12
12፥1 ሮሜ6፥13፡
16፡19፤ኤፌ4፥1፤
1ቆሮ6፥20፤
1ጴጥ2፥5፡11፤
12፥2 ኤፌ4፥23፤
5፥17፤1ቆሮ1፥20፤
2ቆሮ10፥2፤
1ጢሞ5፥4፤1ጴጥ1፥14፤
1ዮሐ2፥15፤
12፥3 ሮሜ15፥15፤
1ቆሮ15፥10፤ገላ2፥9፤
ኤፌ3፥7፤ 4፥7፤
1ጴጥ4፥10፡11
12፥4 1ቆሮ12፥12-14፤
ኤፌ4፥16
12፥5 1ቆሮ 6፥15፤
10፥17፤12፥12፡20፡27፤
ኤፌ2፥16፤4፥4፡25፤
5፥30፤ቈላ3፥15
12፥6 1ቆሮ7፥7፤
12፥4፡8-10፤ኤፌ4፥11፤
1ጴጥ4፥10፡11
12፥7 ኤፌ4፥11
12፥8 ሐሥ11፥23፤
13፥15፤15፥32፤ 2ቆሮ8፥2፤9፥5-13 12፥9 መዝ97፥10፤አሞ5፥15፤
2ቆሮ6፥6፤ 1ተሰ 5፥21፡22፤1ጢሞ1፥5፤ 12፥10 መዝ133፥1፤
ፊል2፥3፤1ተሰ4፥9፤ዕብ13፥1፤1ጴጥ1፥22፤ 12፥11 ሐሥ18፥25
12፥12 ሉቃ18፥1፤ ሮሜ5፥2፤ዕብ10፥32፡ 36፤

[ሠ]1 *ወይም መንፈሳዊ*
[ለ]6 *ወይም እንደ አገልጋይ ተግባር*

*12፥1-16፥27፤* ጳውሎስ ቀደም ሲል በዚህ መልእክት ውስጥ የጠቀሳቸው ነጥቦች ሁሉ፣ ወደ ተግባር እንዴት እንደሚ ተረጐሙ በዚህ ክፍል ያሳያል። ይህም ማለት ጳውሎስ የክርስቲያን ኑሮ እንዴት መሆን እንደሚገባው እስካሁን ድረስ ምንም አልጠቀሰም ማለት አይደለም፤ በም 6-8 ይህን በሚመለከት ጽፎአል፤ አሁን ደግሞ፣ በኑሮ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ መሆን እንዳለበት በማሳየት ሰፋ ያለ ትንታኔ አቅርቦአል። እነዚህ ምዕራፎች ቀደም ሲል ከም 1-11 በተነሡት ታላላቅ መንፈሳዊ ትምህርቶች ላይ ተጨማሪ ሐሳብ ለማካፈል የተጻፉ አይደሉም። እንደ እውነቱ ከሆነ ጠቅላላ መልእክቱ ተግባራችንን፣ እንዲሁም እምነታችንንና አስተሳሰባችንን እግዚአብሔር እንደሚፈልግ የሚያሳይ መልእክት ነው። እምነት የሚገለጸው በመታዘዝ ነው።

12፥1 *እንግዲህ ... እለምናችኋለሁ፤* ጳውሎስ ከም 1፥11 ካለው ክፍል ጠቃሚ የሆነ የመደምደሚያ ሐሳብ ያቀርባል። *በእግዚ አብሔር ርኅራኄ፤* መልእክቱ በአብዛኛው "የእግዚአ ብሔርን ርኅራኄ" በመግለጽ ላይ ያተኮ ራል። *ሰውነታችሁን፤* 6፥13 እና ማብ ይመ። *ሕያው መሥዋዕት፤* ታርደው ለመሥዋዕት ከሚቀርቡ እንስሳት ጋር የሚነጻጸር ሲሆን፣ "ሕያው" ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን አዲስ ሕይወት ከማግኘት አንጻር ሊሆን ይችላል (6፥4 ይመ)። *እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ፤* ሃይማኖታዊ ሥርዐት ብቻ ሳይሆን፣ የልብና የአእምሮ፣ እንዲሁም የፈቃድ ተሳትፎ ያለበት ነው። *አምልኮአችሁ፤* ፍጹም በመታዘዝ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ አምልኮ ነው።

12፥2 *ይህን ዓለም፤* በዓለም ውስጥ ያለውን ክፋትና ብልሹነት ሁሉ የሚጨምር ነው (ገላ 1፥4 ይመ)። *ተለወጡ፤* በአንድ ጊዜ ሳይሆን ደረጃ በደረጃ የሚሆነውን ለውጥ ያመለክታል። የጌታ መልክ በደብረ ታቦር ተራራ ላይ ስለ መለወጡ በሚናገሩ ክፍሎች ውስጥ (ማቴ 17፥2-8፤ ማር 9፥2-8) እንዲሁም 2ቆሮ 3፥18 ላይ ይህ ቃል ተጠቅሶአል። *በአእምሮአችሁ፤* ከበጎ ምግባር ጋር የተያያዘ ሐሳብንና ፈቃድን ያመለክታል (1፥28 ይመ)። *እንግዲህ፤* በክፍሉ የተገለጸው መንፈሳዊ ለውጥ ከተገኘ በኋላ ማለት ነው። *የእግዚአብሔር ፈቃድ፤* እግዚአብሔር አሁን በዚህ ምድር ከክርስቲያኖች የሚፈልገውን ያመለክታል። *መልካም፤* ክርስቲያንን ወደ መንፈሳዊና ሥነ ምግባራዊ እድገት የሚያደርስ ነው። *ደስ የሚያሰኝና፤* በመሠረቱ እኛን ሳይሆን፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ማለት ነው። *ፍጹም፤* የእግዚአብሔር ፈቃድ መሻሻል የሚያስፈልገው ፈቃድ አይደለም።

12፥3 *በሰጣችሁ እምነት መጠን፤* በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ አገለግሎቶችን ለመፈጸም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን የሚሰጠውን ኀይል ያመለክታል (ቍ 4-8 ይመ)። *እግዚአብሔር በሰጣችሁ፤* ኀይል የሚገኘው ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለ ሆነ፣ ለመመካትና ራስን ለማጽደቅ አንዳች ምክንያት አይኖርም።

*12፥4-8፤* ጳውሎስ ክርስቲያኖችን ከሰው አካል ብልቶች ጋር ያመሳስላል። የተለያየ ሥራ ያላቸው ብዙ ብልቶች ቢኖሩም፣ ሁሉም ለአካሉ ጤንነት አስፈላጊ ናቸው። የሐሳቡም ትኩረት አንድነትን በልዩነት ለማሳየት ነው (1ቆሮ 12፥12-12-31 ይመ)።

12፥5 *በክርስቶስ፤* ጳውሎስ ስለ ክርስቲያን አንድነት ላለው ሐሳብ ይህን ቃል መሠረት ያደርጋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት ሊኖር የሚችለው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። እውነተኛ አንድነት፣ በመንፈሳዊ ነገር ላይ የተመሠረተ ነው፤ የ6፥11 ማብ ይመ።

12፥6 *ስጦታዎች፤* ለዚህ ቃል የተተካው የግሪክ ቃል "ካሪዝማታ" የሚል ሲሆን፣ የአካሉን ፍላጎት ለማሟላት ከእግዚ አብሔር ዘንድ ለሕዝቡ በነጻ የሚሰጡ ልዩ ልዩ የሆኑ የጸጋ ስጦታዎችን ያመለክታል (የ1ቆሮ 1፥7፤12፥4 ማብ ይመ)። የ1ቆሮ 12፥10 ማብ ይመ። *ይናገር፤* የስጦታዎችን መኖር የሚክድ ወይም አልጠቀምባቸውም የሚል ዝቅተኛ ግምት መኖር የለበትም። *እንደ እምነቱ መጠን፤* በቍ 3 ላይ፣ "የእምነት መጠን" ከሚለው ጋር አንድ ሊሆን ይችላል (የቍ 3 ማብ ይመ)።

12፥7 *ማገልገል፤* በክርስቶስ አካል ወይም በማናቸውም የአካሉ ብልቶች የሚፈለገውን ማንኛውም አገልግሎት ማለት ነው። የ1ቆሮ 12፥28 ማብ፤ ኤፌ 4፥11 ይመ።

12፥8 *መምከር፤* አንድ ሰው የያዘውን ነገር ከግብ እንዲያደርስ በሚያነቃቃ ቃል ማበረታታትን ያመለክታል፤ መምህርም ብዙውን ጊዜ ይህን ተግባር ያከናውናል። በትምህርት ጊዜ ክርስቲያን ምን ማድረግ እንደሚገባ ይነገረዋል፤ በምክር ጊዜ ግን የተማረውን ተግባራዊ እንዲያደርግ ርዳታ ይሰጠዋል። *መለገስ፤* የራስ የሆነውን ወይም ከሌሎች የተገኘውን ነገር ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ማከፋፈል ሊሆን ይችላል። *ያስተዳድር፤* የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌን ሳያመለክት አይቀርም። በዚህ ወቅት የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሽማግሌዎች ነበሯት (የሐሥ 20፥17፤ 1ተሰ 5፥12፤ 1ጢሞ 5፥17 ይመ)። *ምሕረት ማድረግ፤* ለሕመምተኛና ለድኻ፣ እንዲሁም ለሸመገለው ሁሉ ጥንቃቄ ማድረግና ቸርነትን ማሳየት ማለት ነው። *በደስታ፤* ችግረኞችን መርዳት የሚሰለችና እንደ ሸክም የሚቈጠር ሳይሆን፣ ደስ በመሰኘት የሚደረግ ነው።

12፥9 *ፍቅራችሁ፤* ክርስቲያን፣ ለክርስቲያን ወይም ለሌላ ሰው የሚያሳየው እውነተኛ ፍቅር ነው። *ያለ ግብዝነት፤* ማስመሰል የሌለበትን እውነተኛ ፍቅር ያመለክታል። በማኅበራዊ ጕዳይ ላይ በማተኮር፣ ቀደም ሲል ከተጻፈው አንቀጽ አንጻር፣ ጳውሎስ እዚህ ላይ የሚጠቅሰው ስሜታዊውን ሳይሆን፣ በተግባር የሚገለጸውን ፍቅር ነው።

12፥10 *በወንድማማች መዋደድ፤* በእግዚአብሔር ቤተ ሰብ መካከል ያለ ፍቅር ነው። *አንዱ ሌላውን ከራሱ በማስበለጥ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤* ይህን ሊያደርግ የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ የታደሰ አእምሮ (ቍ 2 ይመ) ብቻ ነው (ፊል 2፥3 ይመ)።

12፥11 *በመንፈስ የጋላችሁ፤* መንፈስ የሚለው "መንፈስ ቅዱስ" ከሆነ፣ የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስ ስለሚሰጠው ታላቅ መንፈሳዊ ጥማት ነው።

12፥12 *በተስፋ ደስተኞች ሁኑ፤* የደስታው ምክንያት፣

ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ። 13ችግረኛ ለሆኑ
ቅዱሳን ካላችሁ አካፍሉ፤ እንግዶችን ተቀበሉ።
14የሚያሳድዷችሁን መርቁ፤ መርቁ እንጂ
አትርገሙ። 15ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበ
ላችሁ፤ ከሚያዝኑም ጋር እዘኑ። 16እርስ በርሳ
ችሁ በመስማማት ኑሩ። ዝቅተኛ ኑሮ* ውስጥ
ካሉ ጋር አብራችሁ ለመሆን ፍቀዱ እንጂ
አትኵራሩ፤ በራሳችሁም አትመኩ።
17ለማንም ክፉን በክፉ አትመልሱ፤ በሰው
ሁሉ ፊት በጎ የሆነውን ነገር ለማድረግ ትጉ።
18ቢቻላችሁስ በበኩላችሁ ከሰው ሁሉ ጋር
በሰላም ኑሩ። 19ወዳጆቼ ሆይ፤ ለእግዚአብሔር ቍጣ
ፈንታ ስጡ እንጂ አትበቀሉ፤ "በቀል የእኔ
ነው፤ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ" ይላል
ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና። 20ይልቁንስ፣

"ጠላትህ ቢራብ አብላው፤
ቢጠማም አጠጣው።
ይህን በማድረግህም የእሳት ፍም
በራሱ ላይ ትከምራለህ።"
21ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ
አትሸነፍ።

## ባለ ሥልጣናትን መታዘዝ

13 ማንኛውም ሰው በሥልጣን ላሉት
ሹማምንት መገዛት ይገባዋል፤ ከእግዚ
አብሔር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉ
ትም ባለ ሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ
ናቸው። 2ስለዚህ፣ በባለ ሥልጣን ላይ የሚ
ያምፅ በእግዚአብሔር ሥርዐት ላይ ማመፁ ነው፤
ይህን የሚያደርጉትም በራሳቸው ላይ ፍርድን
ያመጣሉ። 3ገዦች ክፉ ለሚሠሩ እንጂ መልካም
ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ
ሥልጣንን እንዳትፈራ ትፈልጋለህን? እንግዲ
ያስ መልካሙን አድርግ፤ እርሱም ያመሰግንሃል፤
4እርሱ ለአንተ መልካሙን ለማድረግ የእግ
ዚአብሔር አገልጋይ ነውና። ነገር ግን ክፉ
ብታደርግ ፍራ፤ ምክንያቱም ሰይፉን በከንቱ
አልታጠቀም፤ ክፉ የሚያደርገውን ለመቅ
ጣት የቍጣ መሣሪያ የሆነ፣ የእግዚአብሔር
አገልጋይ ነው። 5ስለዚህም ቅጣትን በመፍራት
ብቻ ሳይሆን፣ ለኅሊና ሲባል ለባለ ሥልጣናት
መገዛት ተገቢ ነው።
6ግብር የምትከፍሉትም ደግሞ ለዚህ ነው፤ ባለ
ሥልጣናቱ፣ በዚሁ ተግባር ላይ የተሠማሩ
የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና፤ 7ለእያንዳንዱ
የሚገባውን ስጡ፤ ግብር ከሆነ ግብርን፣ ቀረጥ
ከሆነም ቀረጥን፣ መፈራት ለሚገባው መፈራ
ትን፣ ክብር ለሚገባውም ክብርን ስጡ።

## ጊዜው ተቃርቦአልና ተዋደዱ

8እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር የማንም ዕዳ
አይኑርባችሁ፤ ባልንጀራውን የሚወድ እርሱ
ሕግን ፈጽሞአልና። 9"አታመንዝር"፣ "አትግ
ደል"፣ "አትስረቅ"፣ "አትመኝ" የሚሉትና ሌሎ
ችም ትእዛዛት ቢኖሩም፣ "ባልንጀራህን እንደ

12፥13 2ነገ14፥10፤ ኢዮ31፥32፤ ሐሥ 24፥17፤ 1ጢሞ3፥2፤5፥10፤ ዕብ13፥2፤1ጴጥ4፥9
12፥14 ማቴ5፥44
12፥15 ኢዮ30፥25
12፥16 ቍ3፤ ኢሳ5፥21፤ኤር45፥5፤ መዝ131፥11 ሮሜ11፥25፤15፥5፤
12፥17 ቍ19፤ ምሳ20፥22፤24፥29፤ 2ቆሮ8፥21
12፥18 ማር9፥50፤ ሮሜ14፥19
12፥19 ቍ17፤ ዘፍ50፥19፤ዘሌ19፥18፤ ዘዳ32፥35፤ 1ሳሙ26፥10፤ ምሳ20፥22፤24፥29፤ 94፥1፤ኤር51፥36
12፥20 ዘፀ23፥4፤ ምሳ25፥21:22፤ ማቴ5፥44፤ሉቃ6፥27
13፥1 ዳን2፥21፤ 4፥17፤ዮሐ19፥11፤ ቲቶ3፥1፤1ጴጥ2፥13: 14፤
13፥2 ዘፀ16፥8
13፥3 1ጴጥ2፥14
13፥4 1ተሰ4፥6
13፥5 ምሳ24፥21: 22
13፥6 ማቴ22፥17
13፥7 ማቴ7፥25፤ 22፥17:21፤ሉቃ23፥2
13፥8 ቍ10፤ ማቴ5፥43፤ ዮሐ13፥34፤ቈላ3፥14
13፥9 ዘፀ20፥13-15:17፤ዘዳ5፥17-19:21፤ ዘሌ19፥18፤ ማቴ5፥43፤ 7፥12፤

*16 ወይም *ዝቅተኛ ሥራ ለመሥራት ፍቀዱ*

የክርስቲያን ተስፋ አስተማማኝ መሆኑ ነው (5፥5 እንዲሁም 8፥16-25፤ 1ጴጥ 1፥3-9 ይመ)። *ታገሡ፤* ክርስቲያን በሕይወቱ ውስጥ መከራ መድረሱ ስለማይቀር፣ በአሸናፊነት መወጣት አስፈላጊው ነው (ዮሐ 16፥33 ይመ)። *በጸሎት ጽኑ፤* ክርስቲያን መጸለይ የሚገባው በችግር ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ ዘወትር በጸሎት አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት መፍጠር አለበት (ሉቃ 18፥1፤ 1ተሰ 5፥17 ይመ)።

12፥13 *ችግረኛ ... ቅዱሳን አካፍሉ፤* ክርስቲያን ለሰዎች ሁሉ በተለይም ለሌሎች ክርስቲያኖች ይህን ለማድረግ ማኅበራዊ ኀላፊነት አለበት (ገላ 6፥10 ይመ)።

12፥14 *የሚያሳድዷችሁን መርቁ፤* ኢየሱስ በማቴ 5፥44፣ በሉቃ 6፥28 ላይ ያስተማረውን ጳውሎስ እየደገመው ነው።

*12፥15፤* የሌሎችን ሰዎች ደስታና ሐዘን መካፈል የክርስቲያን ጥቅምና ኀላፊነት ነው።

12፥17 *ክፉን በክፉ አትመልሱ፤* ማቴ 5፥39-42: 41-45፤ 1ተሰ 5፥15፤ 1ጴጥ 3፥9 ይመ። *በሰው ሁሉ ፊት በጎ የሆነውን ነገር ለማድረግ ትጉ፤* ምሳሌ 3፥4 የተጠቀሰውን ሐሳብ ሳያንጸባርቅ አይቀርም። የክርስቲያን አርአያነት፣ በወንጌል ከተሰጠው የሥነ ምግባር መለኪያ ከቶ መላቅ የለበትም። ይህ ካልሆነ ግን የማያምኑ ሰዎች ክርስትናን ለማንቋሸሽ ምክንያት ይሆናቸዋል፤ የወንጌልንም ክብር ዝቅ ያደርጋል (2ቆሮ 8፥21፤ 1ጢሞ 3፥7 ይመ)።

12፥18 *ቢቻላችሁስ ... በሰላም ኑሩ፤* የሚያስተራርቁ፣ በረከት እንደሚያገኙ ኢየሱስ ተናግሮአል (ማቴ 5፥9)፤ ክርስቲ ያኖችም በተቻላቸው መጠን ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ለመኖር መጣር አለባቸው።

12፥20 *የእሳት ፍም በራሱ ላይ ትከምራለህ፤* ጠላትን ለመበቀል ከመሞከር ይልቅ፣ መልካም ነገር ማድረግ (ቍ 21)፣ ሰውየውን ወደ ንስሓ ሊያመጣ ይችላል (የምሳሌ 25፥22 ማብ ይመ)።

13፥1 *መገዛት፤* እስከ ሰባት ድረስ ባሉት ቍጥሮች ውስጥ ዐቢይ ቃል ነው። *በሥልጣን ላሉት ሹማምንት፤* የሕዝብ አስተዳ ዳሪዎች ናቸው፤ ጳውሎስ መልእክቱን በጻፈበት ጊዜ ሁላቸውም አረ ማውያን ሳይሆኑ አይቀሩም። ክርስቲያኖች ለባለ ሥልጣኖች መገዛቱን በመተው ለክርስቶስ ብቻ ታማኝ ሆነው ለመኖር አስበው ሊሆን ይችላል። *በእግዚአብሔር የተሾሙ፤* በክርስቲያኖች ላይ ስደት የሚያስነሣ መንግሥት ቢኖርም እንኳ፣ የመንግሥት ሥልጣን ከእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ጳውሎስ አልተጠራጠረም።

13፥2 *ፍርድን፤* መለኮታዊ ፍርድ ወይም ቍ 3 እንደሚገልጸው፣ በሥልጣን ላይ ካሉ ገዦች የሚሰጥ ቅጣት ሊሆን ይችላል፤ ቍ 4 ይመ።

13፥3 *መልካሙን አድርግ፤ እርሱም ያመሰግንሃል፤* ጳውሎስ፣ ይህ ሁልጊዜ እውነት ነው ብሎ መጻፉ ሳይሆን፣ ተገቢና ዐይነተኛ የሆነውን የገዦች ተግባር መግለጹ ነው። ገዦች ተገቢ የሆነውን ተግባር በመተው ማድረግ የማይገባቸውን ነገር ሲያደርጉ፣ ክርስቲያኖች ከሰው ይልቅ እግዚአብሔርን ሊታዘዙ ይገባቸዋል (የሐሥ 4፥19፤ 5፥29 ይመ)።

13፥4 *የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና፤* በመለኮታዊ አስተዳደር ሥርዐት ውስጥ፣ ባለ ሥልጣን የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው (ኢሳ 45፥1 ይመ)። *መልካሙን፤* ገዦች በሥልጣን ላይ የሚቀመጡት ኅብረተሰብን ለመጥቀም ነው፤ ይኸውም ጥሩ ሥርዐት እንዲኖር በማድረግ በአጠቃላይ ሕዝቡን ከሚጐዳ ነገር ለመጠበቅ ነው። *ሰይፉን፤* በአገርና በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ሮማውያን የነበራቸው ሥልጣን ምልክት ነው።

13፥5 *ለኅሊና፤* ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው፤ ክርስቲያኖችም ጥሩ ኅሊና ይኖራቸው ዘንድ፥ በተገቢው ሁኔታ ሊያከብሯቸው ይገባል።

13፥6 *ግብር የምትከፍሉም፤* ገዦች፣ የኅብረተሰብን አጠቃላይ ጥቅም ለማስጠበቅ የቆሙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስለ ሆኑ ነው።

13፥8 *ከመዋደድ ... ዕዳ፤* መውደድ ጨርሶ ሊከፈል የማይቻል ዕዳ ነው። አንድ ሰው ምንም ያህል ሰው ቢወድ፣ በመውደዱ የመቀጠል ግዴታ አለበት። *እርስ በርሳችሁ፤* ይህ አባባል ክርስቲያኖችን ብቻ ሳይሆን፣ በሁለተኛው የጥቅሱ አጋማሽ "ባልንጀራ" የሚለው ቃል እንደሚገልጸው ሁሉንም ሰው የሚያመለክት ነው። *ሕግን፤* የግብረ ገብነትንና የማኅበራዊ ኀላፊነትን መመሪያ የሚሰጠው የሙሴ ሕግ ማለት ነው።

*13፥9፤* ይህ ክፍል በቍ 8 መጨረሻ ላይ የተጠቀሰው ባልንጀራን መውደድ፣ ልናደርገው የሚገባንን ማኅበራዊ ኀላፊነት ሁሉ አጠቃሎ እንደሚይዝ በበለጠ ይገልጣል። *ባልንጀራህን፤* ተቸግሮ ርዳታ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፣ ባልንጀራችን እንደ ሆነ ኢየሱስ አስተምሮአል (ሉቃ 10፥25-37 ይመ)፤ እዚህም ላይ ጳውሎስ ያለው ሐሳብ በዚሁ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል። *እንደ ራስህ፤* ራሳችንን እንድንወድ የተሰጠ ትዕዛዝ ሳይሆን በተፈጥሮ እንደዚያ እንደምናደርግ ስለሚታወቅ ነው።

ራስህ አድርገህ ውደድ” በሚለው በዚህ በአንድ
ሕግ ተጠቃለዋል:: 10ፍቅር በባልንጀራው ላይ
ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ መፈጸሚያ
ነው::

11ዘመኑን በማስተዋል ይህን አድርጉ፤ ከእንቅ
ልፋችሁ የምትነቁበት ጊዜ አሁን ነው፤ መዳ
ናችን መጀመሪያ ካመንበት ጊዜ ይልቅ አሁን
ወደ እኛ ቀርቦአልና:: 12ሌሊቱ ሊያልፍ፣ ቀኑም
ሊጀምር ነው:: ስለዚህ የጨለማን ሥራ ጥለን፣
የብርሃንን ጦር ዕቃ እንልበስ:: 13በቀን እንደ
ምንመላለስ በአገባብ እንመላለስ:: በጭፈራና
በስካር አይሁን፤ በዝሙትና በመዳራት አይ
ሁን፤ በክርክርና በቅናትም አይሁን:: 14ይል
ቁንም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤
ምኞቱንም ይፈጽም ዘንድ ለሥጋ በሐሳባችሁ
አትመቻቹለት::

## በወንድምህ ላይ አትፍረድ

14 በእምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው፣ አከ
ራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአቋሙ
ሳትፈርዱበት ተቀበሉት:: 2የአንድ ሰው እም
ነቱ ማንኛውንም ነገር እንዲበላ ይፈቅድለታል፤
በእምነቱ ያልጠነከረው ሌላው ሰው ግን አትክ
ልት ብቻ ይበላል:: 3ማንኛውንም የሚበላ
የማይበላውን አይናቅ፤ የማይበላውም፣ የሚበ
ላውን አይኰንን፤ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና::
4ሌላውን በሚያገለግል ላይ የምትፈርድ አንተ
ማን ነህ? እርሱ ቢወድቅ ወይም ቢቆም ለጌ
ታው ነው፤ ጌታ ሊያቆመው ስለሚችልም
ይቆማል::

5አንድ ሰው አንዱን ቀን ከሌላው የተሻለ
ቅዱስ አድርጎ ይቈጥራል፤ ሌላው ደግሞ
ቀኖች ሁሉ እኩል እንደ ሆኑ ያስባል:: እያ
ንዳንዱ የራሱን ውሳኔ ልብ ብሎ ይወስን::
6አንድን ቀን ከሌላው የተለየ አድርጎ የሚያስብ
ሰው፣ እንዲህ የሚያደርገው ለጌታ ብሎ ነው፤
ሥጋ የሚበላውም ለጌታ ብሎ ይበላል፤
በእግዚአብሔር ምስጋና ያቀርባልና:: የማይበላም
ለጌታ ሲል አይበላም፤ በእግዚአብሔርም ምስጋና
ያቀርባል:: 7ከእኛ ማንም ለራሱ የሚኖር፣
ለራሱም የሚሞት የለምና:: 8ብንኖር ለጌታ
እንኖራለን፤ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን፤
ስለዚህ ብንኖርም ብንሞትም የጌታ ነን::

9ለዚሁ፣ የሙታንና የሕያዋን ጌታ ይሆን
ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአል፤ በሕይወትም ተነ
ሥቶአል:: 10ታዲያ አንተ በወንድምህ ላይ
ለምን ትፈርዳለህ? ለምንስ ወንድምህን ትን
ቃለህ? ሁላችንም በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር

13፥10 ቍ 8:9
13፥11 1ቆሮ7፥29-31፤10፥11፤ ኤፌ5፥14፤1ተሰ5፥5:6፤ ያዕ5፥8፤1ጴጥ4፥7፤ 1ዮሐ2፥18፤ራእ22፥10፤
13፥12 ኤፌ5፥11፤ 6፥11:13፤1ተሰ5፥8፤ ዕብ10፥25፤ 1ዮሐ 2፥8፤
13፥13 ሉቃ21፥34፤ ገላ5፥20:21፤ ኤፌ5፥18፤1ጴጥ4፥3
13፥14 ገላ3፥27፤ 5፥24፤ኤፌ4፥24፤ ቈላ3፥10:12፤
14፥1 ሮሜ15፥1፤ 1ቆሮ8፥9-12፤9፥22
14፥2 ቍ 14
14፥3 ቍ 10:13፤ ሉቃ18፥9፤ቈላ2፥16
14፥4 ማቴ7፥1
14፥5 ገላ4፥10፤ ቈላ2፥16
14፥6 ማቴ14፥19፤ 1ቆሮ10፥30:31፤ 1ጢሞ4፥3:4
14፥7 2ቆሮ5፥15፤ ገላ2፥20
14፥8 ፊል1፥20
14፥9 ሐሥ10፥42፤ 2ቆሮ5፥15፤ ራእ1፥18፤2፥8፤
14፥10 ቍ 3፤ማቴ7፥1፤2ቆሮ5፥10

°14 ወይም ለገጢተኛ ተፈጥሮ

*13፥11-14፤* በሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች እንደ ተጻፈው፣ በዚህም ክፍል ክርስቲያኖች የጽድቅ ሕይወት ይኖሩ ዘንድ ለማነሣሣትና ለማስጠንቀቅ፣ እርግጠኛ የሆነው የአሁኑ ዘመን መጨረሻ መቃረብ ተጠቅሶአል (ማቴ 25፥31-46፤ ማር 13፥33-37፤ ያዕ 5፥7-11፤ 2ጴጥ 3፥11-14 ይመ)::

13፥11 *ዘመኑን፤* የዘመን ፍጻሜ ከመድረሱ በፊት ያለውን የመዳን ጊዜ እንዲሁም የአሁኑን ዘመን ማብቂያ ያመለክታል:: *ጊዜ፤* መደረግ ያለበትን ለማድረግ ወሳኙ ጊዜ ነው:: *መዳናችን፤* መዳናችን ሙሉ በሙሉ የሚገለጸው በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ነው:: (8፥23፤ ዕብ 9፥28፤ 1ጴጥ 1፥5፤ 1ዮሐ 3፥2 ይመ):: *አሁን ... ቀርቦአልና፤* እያንዳንዱ ቀን ወደ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ያቀርበናል::

13፥12 *ሌሊቱ፤* አሁን ያለው ክፉ ዘመን ማለት ነው:: *ሊያልፍ፣ ... ነው፤ ቀኑም ሊጀምር ነው፤* አዲስ ኪዳን ስለሚያስተምረው የመጨረሻው ዘመን “መቃረብ” ይህ ግልጽ ምሳሌ ነው (ማቴ 24፥33፤ 1ቆሮ 7፥29፤ ፊል 4፥5፤ ያዕ 5፥8-9፤ 1ጴጥ 4፥7፤ 1ዮሐ 2፥18 ይመ):: ይኸውም የጥንት ክርስቲያኖች ኢየሱስ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ተመልሶ እንደሚመጣ ያምኑ ነበር ማለት አይደለም (እንዲህ ከሆነማ ተሳስተዋል ማለት ይሆናል)፤ ይልቁን የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የመጨረሻው ዘመን የጀመረበት ወሳኝ የታሪክ ክንውን እንደ ሆነ መገንዘባቸውን ያሳያል:: በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ቀጣይና ትልቁ ነገር የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ስለ ሆነ፣ በአፈጻጸም ቅደም ተከተል የቱንም ያህል ይዘግይ እንጂ “ሌሊቱ ሊያልፍ ተቃርቦአል”:: *ቀኑም፤* የዘመን ፍጻሜን የሚያስከትለው የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ማለት ነው::

13፥14 *ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤* ገላ 3፥27 ይመ:: ክርስቲያኖች በኑሮአቸው የክርስቶስን በጎነት እንዲገልጹ ጳውሎስ ይመክራቸዋል::

14፥1 *በእምነቱ ደካማ የሆነውን፤* የአመጋገብ ሥርዐትን መጠበቅ፣ ሰንበትንና ሌሎች ልዩ ቀናትን ማክበር፣ የመሳሰሉትን ሕግጋት ለማድረግ እንጂ ለመተው ፈቃደኞች ያልነበሩ በሮም የሚኖሩ ክርስቲያን አይሁዳውያን ሳይሆኑ አይቀሩም:: አስተሳሰባቸውም በገላትያ ከነበሩት አይሁዳውያን አስተሳሰብ ጋር ሙሉ በሙሉ አንድ አልነበረም:: በገላትያ የነበሩት ክርስቲያን አይሁዳውያን የጽድቅን ሥራ በመሥራት፣ እግዚአብሔርን ለመልካም ሥራቸው ባለ ዕዳ ለማድረግ ያስቡ ነበር:: ይህን የተሳሳተ ትምህርታቸውንም በገላትያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ተጽዕኖ ያደርጉ ነበር፤ “ደካማ” የተባሉት በሮም የነበሩ ክርስቲያኖች ግን አንዳንድ ሕግጋትን በመጠበቅ ጽድቅ ይገኛል አላሉም፤ ይህን እንዲጠብቁም ሌሎችን አላስገደዱም:: ከክርስቶስ መምጣት ጋር በተጀመረው በአዲስ ኪዳን ሥርዐት ውስጥ፣ የብሉይ ኪዳን ሕግ ድርሻ ምን እንደ ሆነ በግልጽ የተረዱ ሰዎች አልነበሩም:: *አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአቋሙ ሳትፈርዱበት፤* የክርስቲያኖች ኅብረት፣ አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሳይቀር እያንዳንዱ ሰው በሚኖረው የሐሳብ ስምምነት ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም:: ክርስቲያናዊ ኑሮን በተመለከተ፣ ክርስቲያኖች በሁሉ ነገር ይስማማሉ ማለት አይደለም፤ የግድ መስማማትም የለባቸውም::

14፥2 *የአንድ ሰው እምነቱ፤* በአንጻሩ ጳውሎስ ስለ “ጠንካራ” ክርስቲያን ይገልጻል:: እዚያ ላይ እምነት የሚለው ቃል የገባው እርግጠኛ ወይም አስተማማኝ ለማለት ነው:: ወንጌልን የተረዳ ጠንካራ ክርስቲያን፣ ምግብ በአንድ ሰው መንፈሳዊ ሁኔታ ላይ ለውጥ እንደማያመጣ ይገነዘባል::

14፥4 *ሌላውን በሚያገለግል ላይ፤* የእግዚአብሔርን አገልጋይ ማለት ነው:: ክርስቲያን የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነውን ሌላውን ክርስቲያን ማጥላላት ወይም ማራቅ የለበትም:: *ቢወድቅ ወይም ቢቆም ለጌታው ነው፤* ደካማው ክርስቲያን “ጠንካራ” ለሆነው ወንድሙ ጌታ አይደለም፤ “ጠንካራውም” “የደካማው” ጌታ አይደለም:: ጌታ፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ክርስቲያኖችም ሁሉ ተጠያቂነታቸው ለማንም ሳይሆን ለእርሱ ነው::

14፥5 *አንዱን ቀን ከሌላው የተሻለ ቅዱስ አድርጎ ይቈጥራል፤* አንዳንዶች ይህ የሚያመለክተው የሰንበትን ቀን ነው ብለው ያስባሉ፤ ነገር ግን በብሉይ ኪዳን የበዓላት አከባበር ሥርዐት ውስጥ የተጠቀሱትን ለየት ያሉ ቀኖችን ሁሉ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል:: *ቀኖች ሁሉ እኩል እንደ ሆኑ ያስባል፤* በቅድስና በመመላለስና እግዚአብሔርን በማገልገል ቀኖችን ሁሉ ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት ይገባል:: *የራሱን ውሳኔ ልብ ብሎ ይወስን፤* አከራካሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የግል አቋም መያዝ አስፈላጊ መሆኑ በዚህ ክፍል ተደጋግሞ ተጠቅሶአል (ቍ 14:16:22-23 ይመ)::

*14፥6፤* የብርቱውም የደካማውም ዐላማ መሆን ይኖርበታል፤ ሁለቱም ጌታን የማገልገልና ስለ ስጦታውም የማመስገን ፍላጎት ሊኖራቸው ይገባል::

14፥7 *ከእኛ ማንም ለራሱ የሚኖር ... የለምና፤* “እኛን” ክርስቲያኖችን የሚመለከት ነው፤ ይኸውም ጌታን እንጂ ራሳችንን ደስ ለማሰኘት መኖር እንደሌለብን ለማሳየት ነው:: *ለራሱም የሚሞት የለምና፤* በሞት ጊዜ እንኳ ቢሆን ዋናው ቁም ነገር፣ አንድ ሰው ከጌታ ጋር ያለው ግንኙነት ነው:: ጳውሎስ የዚህን ጥቅስ እውነታ በቍ 8 ላይ ይደግመዋል::

14፥9 *ጌታ፤* የ10፥9 ማብ ይመ:: ክርስቶስ በሕያዋንና በሙታን ላይ ያለው ጌትነት፣ በሞቱና በትንሣኤው የተገኘ ነው::

14፥10 *በወንድምህ ላይ ለምን ትፈርዳለህ?* ደካማ ለሆኑ ክርስቲያኖች የተጻፈ ነው:: *ለምንስ ወንድምህን ትንቃለህ?*

ፊት እንቀርባለንና፤ [11]እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤
“ ‘እኔ ሕያው ነኝና’፤
‘ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፤
ምላስም ሁሉ በእግዚአብሔር ይመሰክራል’ ”
ይላል ጌታ።

[12]ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን በእ
ግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።
[13]ስለዚህ እርስ በርሳችን፣ አንዱ በሌላው
ላይ ከመፍረድ እንቈጠብ፤ በዚህ ፈንታ ግን
በወንድምህ መንገድ ላይ የማሰናከያ ድንጋይ
ወይም ወጥመድ እንዳታስቀምጥ ቍርጥ ሐሳብ
አድርግ። [14]በጌታ በኢየሱስ ሆኜ በራሱ ንጹሕ
ያልሆነ ምንም ምግብ[፩] እንደሌለ ተረድቻ
ለሁ፤ ነገር ግን አንድ ሰው አንድን ነገር ንጹሕ
እንዳልሆነ የሚቈጥር ከሆነ፣ ያ ነገር ለእርሱ
ንጹሕ አይደለም። [15]ወንድምህ በምትበላው
ምግብ የሚያዝን ከሆነ፣ በፍቅር አልተመላ
ለስህም፤ ክርስቶስ የሞተለትን ወንድምህን
በመብልህ አታጥፋው። [16]መልካም ነው ብለህ
የምታስበው ነገር ክፉ ተብሎ እንዲነቀፍ
አታድርግ። [17]የእግዚአብሔር መንግሥት በመን
ፈስ ቅዱስ የሆነ ጽድቅ፣ ሰላምና ሐሤት
ነው እንጂ፣ የመብልና የመጠጥ ጕዳይ አይ
ደለም፤ [18]በዚህ ሁኔታ ክርስቶስን የሚያ
ገለግል እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛልና፤ በሰውም
ዘንድ የተመሰገነ ነው።
[19]ስለዚህ ሰላም የሚገኝበትንና እርስ በርሳ
ችንም የምንታነጽበትን ማንኛውንም ጥረት
እናድርግ። [20]ለምግብ ስትል የእግዚአብሔርን
ሥራ አታፍርስ። ሁሉ ንጹሕ ነው፤ ነገር
ግን ለሌላው ሰው የመሰናከያ ምክንያት
የሚሆነውን መብላት ስሕተት ነው። [21]ለወ
ንድምህ መሰናከል ምክንያት የሚሆነውን
ሥጋን አለመብላት፣ ወይንን አለመጠጣት፣
ወይም አንዳች ነገርን አለማድረግ መልካም
ነው።
[22]እንግዲያስ ስለ እነዚህ ነገሮች ያለህ
እምነት በአንተና በእግዚአብሔር መካከል
የተጠበቀ ይሁን፤ ትክክል ነው ብሎ በተቀ
በለው ነገር ራሱን የማይኰንን የተባረከ
ሰው ነው። [23]ነገር ግን የሚጠራጠር ሰው
ቢበላ በእምነት ስላልሆነ፣ ተፈርዶበታል፤
በእምነት ያልተደረገ ሁሉ ኀጢአት ነውና።

15 እኛ ብርቱዎች የሆንን፣ የደካሞችን
ጕድለት መሸከም እንጂ ራሳችንን
ማስደሰት የለብንም። [2]እያንዳንዳችን ባልን
ጀራችንን ለማነጽ፣ እርሱንም ለመጥቀም ደስ
የሚያሰኘውን ነገር ማድረግ ይገባናል፤
[3]ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤ ነገር
ግን፣ “አንተን የሰደቡበት ስድብ በእኔ ላይ
ደረሰብኝ” ተብሎ እንደ ተጻፈው ሆነበት።

14፥11 ኢሳ49፥18፤ 45፥23፤ፊል2፥10:11
14፥12 ማቴ12፥36፤ 1ጴጥ4፥5
14፥13 ቍ1፤ ማቴ7፥1፤2ቆሮ6፥3
14፥14 ቍ20፤ ሐሥ10፥15፤ 1ቆሮ 8፥7
14፥15 ቍ20 ኤፌ5፥2፤1ቆሮ8፥11
14፥16 1ቆሮ10፥30
14፥17 ኢሳ32፥17፤ ሮሜ15፥13፤1ቆሮ 8፥8፤ገላ5፥22
14፥18 ሉቃ2፥52፤ሐሥ24፥16፤ 2ቆሮ8፥21
14፥19 መዝ34፥14፤ ሮሜ12፥18፤15፥2፤ 1ቆሮ7፥15፤14፥3-5:12:17:26፤2ቆሮ12፥19፤ኤፌ4፥12:29፤ 2ጢሞ2፥22፤ ዕብ12፥ 14፤
14፥20 ቍ13፤ 14:15፤ሐሥ10፥15፤ 1ቆሮ8፥9-12
14፥21 ማቴ5፥29
14፥22 1ዮሐ3፥21
14፥23 ቍ5
15፥1 ሮሜ14፥1፤ 1ተሰ5፥14
15፥2 ሮሜ14፥29፤ 1ቆሮ10፥24፤

15፥3 መዝ69፥9፤ 2ቆሮ8፥9፤

[፩]14 *ወይም ምንም ነገር*

ጠንካራ ለሆኑ ክርስቲያኖች የተጻፈ ነው። *ሁላችንም፤* እያንዳንዱን ክርስቲያን ይመለከታል። *በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር፤* ክርስቲያኖች ሁሉ ለፍርድ ይቀርባሉ፤ ፍርዱም እንደየሥራቸው ይሆናል (2ቆሮ 5፥10 ይመ፤ 1ቆሮ 3፥10-15 ጋር ያነጻጽሩ)።

14፥13 *በዚህ ፈንታ፤* ከዚህ ቀጥሎ ያለው ሐሳብ ለጠንካራ ክርስቲያኖች የተጻፈ ነው። *የማሰናከያ ድንጋይ፤* ለአንድ ሰው በኀጢአት መውደቅ ምክንያት የሚሆን ነገር ማለት ነው።

14፥14 *በጌታ በኢየሱስ ሆኜ ... ተረድቻለሁ፤* ጳውሎስ ክርስቲያን እንደ መሆኑ፣ የተወሰነ ምግብን የሚከለክለው የቀድሞ እምነት በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት የለውም (ማቴ 15፥10-11፡16-20፤ ማር 7፥14-23 ይመ)። *በራሱ ንጹሕ ያለሆነ ምንም ምግብ ...፤* ጳውሎስ በሌላ ቦታ የሰጠውን ተመሳሳይ ትምህርት በ 1ጢሞ 4፥4፤ ቲቶ 1፥15 ላይ ይመ። *አንድ ሰው አንድን ነገር ንጹሕ እንዳልሆነ የሚቈጥር ከሆነ ያ ነገር ለእርሱ ንጹሕ አይደለም፤* እዚህ ላይ ኀጢአት የግል አመለካከት ወይም የኅሊና ጕዳይ ብቻ ነው ብሎ በጥቅሉ መውሰድ ትክክል አይደለም። ጳውሎስ፣ ከእግዚአሔር ቃል አንጻር በግልጽ ኀጢአት መሆኑ ስለታወቀው ነገር መናገሩ ሳይሆን፣ በብሉይ ኪዳን ስለ ምግብ ከተሰጠው ሕግ አንጻር በክርስቲያኖች ዘንድ ስላለው የተለያየ አመለካከት ለማሳየት ነው። እንደዚህ ስላሉት ጕዳዮች ውሳኔ ለማድረግ በኅሊና መመራት ይገባል።

14፥15 *በፍቅር፤* አለመግባባትን በተገቢው መንገድ ለማስ ወገድ ዋና መፍትሔ ነው። *ክርስቶስ የሞተለትን ወንድምህን፤* ክርስቶስ ለደካማው ክርስቲያንም እስከ ሞት ድረስ ዋጋ ከፍሎአል። ጠንካራው ክርስቲያንም ለእንደነዚህ ዐይነት ደካማ ወንድሞች ጥንቃቄ ለማድረግ ሲል በሁኔታዎች ሁሉ ዝግጁ ሆኖ ለመገኘት ፈቃደኛ መሆን ይኖርበታል (1ቆሮ 9፥19-23 ይመ)።

14፥16 *መልካም ነው ብለህ የምታስበው ነገር፤* ስለ ክርስቲያናዊ ነጻነት ካለህ መረዳት አንጻር ማለት ነው። *ክፉ ተብሎ እንዲነቀፍ፤* ኀላፊነት በጐደለው ሁኔታ ነጻነትን መጠ ቀም፣ መጥፎ ውጤት ያስከትላል።

14፥17 *የእግዚአብሔር መንግሥት፤* የማቴ 3፥2፤ የሉቃ 4፥43 ማብ ይመ። *የመብልና የመጠጥ ጕዳይ አይደለም፤* እንደነዚህ ላሉ አላስፈላጊ ነገሮች ትኵረት መስጠት፣ የክርስትናን ኑሮ ዋና ሐሳብ ሙሉ በሙሉ መዘንጋት ነው። *ጽድቅ፤* በቅድስና መኖር ማለት ነው። ጳውሎስ ለክርስቲያናዊ ሕይወት ሥነ ምግባር እንደሚገደው በመልእክቶቹ ሁሉ ጐልቶ ይታያል። *ሰላምና፤* 5፥1 እና ማብ ይመ። *በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ... ሐሤት፤* ከመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ደስታ ማለት ነው።

14፥19 *እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን፤* የእያንዳንዱን ክርስቲያንና የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ መታነጽ ያመለክታል (1፥11-12 ይመ)።

14፥20 *የእግዚአብሔርን ሥራ፤* ደካማው ክርስቲያን ወንድም የዳነ ሰው እንደ መሆኑ፣ የእግዚአብሔር ሥራ ነው፤ እግዚአብሔርም በእርሱ ሥራውን መሥራቱን ይቀጥላል (ከኤፌ 2፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። *ለሌላው ሰው የመሰናከያ ምክንያት የሚሆነውን፤* ጠንካራው ክርስቲያን አንዳንድ ነገሮችን ለማድረግ መብት እንዳለው ጳውሎስ ያውቃል፤ ነገር ግን የደካማውን ክርስቲያን መንፈሳዊ ጥቅም ከመጠበቅ አንጻር መሆን እንዳለበት ይገልጻል።

14፥22 *በአንተና በእግዚአብሔር መካከል የተጠበቀ ይሁን፤* ጠንካራው ክርስቲያን እምነቱን የሚቃረን ነገር እንዲያደርግ ወይም ያለውን የእምነት ደረጃ እንዲለውጥ አይጠበቅም፤ ክርስቲ ያናዊ ነጻነቱንም በግሉ ሊኖርበት እንጂ፣ ለታይታ ሊጠቀምበት አይገባም። *ትክክል ነው ብሎ በተቀበለው ነገር፤* አንዳንድ ምግቦችን ስለ መብላት የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም።

14፥23 *ሁሉ፤* ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች፣ በተለይም በመቻቻል ሊታለፉ የሚገቡ፣ በክርቲያኖች መካከል የተፈጠሩ ማናቸውንም የሐሳብ ልዩነቶች የሚያመለክት ነው።

15፥1 *ብርቱዎች የሆን፤* በግል ያላቸው እምነት ከደካማው ይልቅ ነጻነት ከሚሰጣቸው ጠንካራ ክርስቲያኖች ጋር ጳውሎስ ራሱን ይመድባል። *መሸከም፤* ዝም ብሎ መሸከም ሳይሆን፣ በፍቅር መደረግ አለበት። *ጕድለት፤* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ክፍል ስላለው ሐሳብ በግልጥ የተጻፈ ነገር ስለ ሌለ፣ ኀጢአትን የሚያመለክት አይደለም። *ራሳችንን ማስደሰት የለብንም፤* ክርስቲያን ፈጽሞ ራሱን ደስ ማሰኘት የለበትም ለማለት ሳይሆን፣ ለሌሎች ክርስቲያኖች መሰናክል ለሚሆንባቸው ነገር ሳይጠነቀቅ፣ ራሱ የሚፈልገውን ነገር ብቻ በማድረግ ላይ የሚያተኵር መሆን እንደሌለበት ለማሳየት ነው።

15፥3 *ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤* ክርስቶስ የራሱን ሳይሆን፣ የአባቱን ፈቃድ ሊያደርግ መጣ፤ ይህም መከራ መቀበልና ሞትም እንኳ ያለበት ነበር (ማቴ 20፥28፤ ማር 10፥45፤ 1ቆሮ 10፥33-11፥1፤ 2ቆሮ 8፥9፤ ፊል 2፥5-8 ይመ)። *አንተን የሰደቡበት ስድብ በእኔ ላይ ደረሰብኝ፤* በመዝ 69፥9 ላይ “አንተ” የሚለው፣ እግዚአብሔርን የሚያመለክት ሲሆን፣ “እኔ” የሚለው ደግሞ ጳውሎስ ክርስቶስ እንደ ሆነ የሚገልጠውን፣ መከራ የሚቀበለውን

4በጽናትና ቅዱሳት መጻሕፍት በሚሰጡት
መጽናናት ተስፋ እንዲኖረን፣ ቀደም ብሎ
የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።
5ብርታትንና መጽናናትን የሚሰጥ አምላክ፣
ክርስቶስ ኢየሱስን ስትከተሉ፣ በመካከላችሁ
የአንድነትን መንፈስ ይስጣችሁ፤ 6ይኸውም
በአንድ ልብና በአንድ አፍ ሆናችሁ፣ የጌታ
ችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክና አባት
ታከብሩ ዘንድ ነው።

7እንግዲህ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሆን ዘንድ
ክርስቶስ እንደ ተቀበላችሁ፣ እርስ በርሳችሁ
ተቀባበሉ። 8ለአባቶች የተሰጠውን የተስፋ
ቃል ያጸና ዘንድ ስለ እግዚአብሔር እውነት ሲል
ክርስቶስ የአይሁድ[T] አገልጋይ እንደ ሆነ
እነግራችኋለሁና፤ 9እንዲሁም አሕዛብ እግዚ
አብሔርን ስለ ምሕረቱ ያመሰግኑት ዘንድ ነው፤
እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤

"ስለዚህ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ለስምህም እዘምራለሁ።"
10ደግሞም፣
"አሕዛብ ሆይ፤ ከሕዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ"
ይላል።
11እንደ ገናም፣
"አሕዛብም ሁላችሁ ጌታን አመስግኑ፤
ሕዝቦች ሁሉ ወድሱት" ይላል።
12ኢሳይያስም እንዲሁ፣
"በሕዝቦች ሁሉ ላይ የሚነግሠው፣
የእሴይ ሥር ይመጣል፤
በእርሱም አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ" ይላል።

13በእርሱ በመታመናችሁ የተስፋ አምላክ
ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ፤ ይኸ
ውም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተስፋ ተትረ
ፍርፎ እንዲፈስላችሁ ነው።

## የአሕዛብ አገልጋይ የሆነው ጳውሎስ

14ወንድሞቼ ሆይ፤ እናንተ ራሳችሁ በበ
ጎነት የተሞላችሁ፣ በዕውቀት ሁሉ እንደ
ተሞላችሁና አንዱ ሌላውን ለመምከር ችሎታ
ያላችሁ መሆናችሁን እኔ ራሴ እርግጠኛ
ሆኜአለሁ። 15እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ መሠ
ረት፣ እንደ ገና ዐሳስባችሁ ዘንድ በአንዳንድ
ጕዳዮች ላይ በድፍረት የጻፍሁላችሁ፣ 16በእግ
ዚአብሔር ወንጌል የክህነት ተግባር፣ ለአሕዛብ
የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ ለመሆን ነው፤
ይኸውም አሕዛብ በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው
በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት
እንዲሆኑ ነው።

17ስለዚህ እግዚአብሔርን በማገልገሌ በክርስቶስ
ኢየሱስ እመካለሁ። 18በተናገርሁትና በአደረ
ግሁት ነገር አሕዛብ ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ፣
ክርስቶስ በእኔ ሆኖ ከፈጸመው በቀር ሌላ
ነገር ለመናገር አልደፍርም፤ 19ይህም የሆነው
በመንፈስ ቅዱስ ኀይል፣ በምልክቶችና በታ
ምራት ነበር። በዚህም ሁኔታ ከኢየሩሳሌም

[T]8 ግሪኩ *የመገረዝ* ይላል

15፥4 ሮሜ4፥23፡24
15፥5 ሮሜ12፥16፤ 1ቆሮ1፥10፤ 2ቆሮ13፥11፤ ኤፌ4፥3፤ፊል2፥2፤ ቈላ3፥14፤1ጴጥ3፥8
15፥6 መዝ34፥3፤ ራእ1፥6
15፥7 ሮሜ14፥1
15፥8 ማቴ15፥24፤ ሐሥ3፥25፡26፤ 2ቆሮ 1፥20
15፥9 2ሳሙ22፥50፤ መዝ18፥49፤ ማቴ9፥8፤ሮሜ3፥29፤
15፥10 ዘዳ32፥43፤ ኢሳ 66፥10
15፥11 መዝ117፥1
15፥12 ኢሳ11፥10፤ ራእ 5፥5፤ማቴ12፥21
15፥13 ቍ19፤ ሮሜ14፥17፤ 1ቆሮ2፥4፤4፥20፤ 1ተሰ1፥5
15፥14 ኤፌ5፥9፤ 2ቆሮ8፥7፤2ጴጥ1፥12
15፥15 ሮሜ12፥3
15፥16 ቍ19፤ ኢሳ 66፥20፤ ሐሥ9፥15፤ሮሜ1፥1፤
15፥17 ፊል3፥3፤ ዕብ2፥17
15፥18 ሐሥ15፥12፤ 21፥19፤ሮሜ1፥5፤ 16፥26
15፥19 ቍ13፤ የሐ4፥48፤

ጻድቃን ሰው ያመለክታል። ከመዝሙር የተጠቀሰው ክፍል፣ ክርስቶስ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ጠላትነት በፈቃደኝነት መሸከሙን እንጂ፣ ራሱን ደስ እንዳላሰኘ ለማሳየት ይረዳል።

*15፥4፤* በመዝ 69፥9 ላይ የተጠቀሰው ሐሳብ ክርስቶስን የሚያመለክት መሆኑን ጳውሎስ እዚህ ላይ ይደግፋል። በዚህም መሠረት፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ዐላማ በሚመለከት አንድን ታላቅ እውነት ይገልጣል፤ ይኸውም መከራን በመታገሥ በክርስቶስ ያለንን ተስፋ አጽንተን ለመያዝ ድፍረት እንዲሆንልን፣ ለትም ህርታችን መጻፉ ነው (1ቆሮ 10፥6፡11 ይመ)።

15፥5 *በመካከላችሁ የአንድነትን መንፈስ፤* ቀደም ሲል በተጠቀሱት ከኅሊና ጋር በተያያዙ ጕዳዮች ላይ፣ ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ አንድ ዐይነት ድምዳሜ መድረስ ይገባቸዋል ለማለት ሳይሆን፣ ሳለመስማማትም ቢሆን የሚያደርጉትን ተስማምተው በፍቅር ሊያደርጉ እንደሚችሉ ለማሳየት ነው።

15፥7 *ክርስቶስ እንደ ተቀበላችሁ፤* 14፥3፡4፡15 ይመ።

15፥8 *ክርስቶስ የአይሁድ አገልጋይ እንደ ሆነ፤* ይህም በምድራዊ አገልግሎቱ ታይቶአል። ክርስቶስ የተላከው በቅድሚያ ለአይሁድ ሕዝብ በመሆኑ፣ አገልግሎቱ በአብዛኛው በእነርሱ ላይ ያተኰረ ነበር (ማቴ 15፥24 ይመ)፤ እግዚአብሔር ለአይሁድ የተለየ ዕድል ሰጥቶአቸዋል (3፥1-8 ይመ)። *ለአባቶች የተሰጠውን የተስፋ ቃል፤* ለአብርሃም (ዘፍ 12፥1-3፤ 17፥7፤ 18፥19፤ 22፥18)፣ ለይስሐቅ (ዘፍ 26፥3-4) እና ለያዕቆብ (ዘፍ 28፥13-15፤ 46፥2-4) የተሰጠ የቃል ኪዳን ተስፋ ነው።

15፥9 *አሕዛብ እግዚአብሔርን ... ያመሰግኑት ዘንድ፤* ከመጀመሪያው እግዚአብሔር ለእስራኤል ያዘጋጀውን የማዳን ሥራ፣ አሕዛብን የማዳን ዕቅድንም ያካተተ ነበር (ዘፍ 12፥3 ይመ)። አሕዛብ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገለጠውን ታላቅና ጸጋን የተሞላ ሥራ ያያሉ፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ነገር ክብር ሲሰጡም ምስጋናቸውን ይሰማሉ (በመዝ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግሞ የተጠቀሰ ዋና ሐሳብ ነው፤ ጳውሎስ በቍ 9-12 ላይ የጠቀሰውንና የመዝ 9፥1 ማብ ይመ)። ስለዚህ እውነተኛውን አምላክ ያውቁታል፤ ስለ ምሕረቱም ያከብሩታል (የመዝ 46፥10፤ የ47፥9 ማብ ይመ)። እግዚአብሔር እስራኤልን ለማዳን ያደረገው ትልቁና የመጨረሻው ተግባር ለእስራኤል የነገድ አባቶች የተሰጠውን ተስፋ ለመፈጸምና ከአሕ ዛብ ወገንም እጅግ ብዙ ሕዝብ ወደ ራሱ ለመሰብሰብ መሲሑን መላኩ ነበር።

15፥12 *የእሴይ ሥር፤* እሴይ የዳዊት አባት ሲሆን (1ሳሙ 16፥5-13፤ ማቴ 1፥6 ይመ)፣ መሲሑ ደግሞ "የዳዊት ልጅ" ነበር (ማቴ 21፥9)፤ ኢሳ 11፥1፤ ራእይ 5፥5 ይመ። *በእርሱም አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ፤* የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ለአሕዛብ የነበራት ተልእኮ፣ ወንጌልን ባለማቋረጥ በመስበክ፣ ይህንን ትንቢት እንዲፈጸም ማድረግ ነበር።

15፥13 *የተስፋ አምላክ፤* ክርስቲያን ያለው ማንኛውም ተስፋ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ነው፤ የ5፥5 ማብ ይመ። *በመንፈስ ቅዱስ ኀይል፤* ተስፋ በሰው ጥረት የሚፈጠር ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (8፥24-25 ይመ)።

15፥15 *እንደ ገና ዐሳስባችሁ ዘንድ፤* ጳውሎስ በሮም ፈጽሞ ስላልሰበከ ወይም ስላላስተማረ፣ በቤተ ክርስቲያን ስለ ታወቀው አጠቃላይ መሠረታዊ የእምነት ትምህርት መናገሩ ሊሆን ይችላል።

15፥16 *ለአሕዛብ የክርስቶስ ኢየሱስ አገልጋይ፤* የ11፥13 ማብ ይመ። *ለእግዚአብሔር ወንጌል በክህነት አገልግሎት፤* የጳውሎስ የክህነት አገልግሎት ከሌዋውያን የክህነት አገልግሎት የተለየ ነበር። የእነርሱ አገልግሎት በቤተ መቅደሱ ሥርዐት ላይ ያተኰረ ሲሆን፣ የጳውሎስ ግን ወንጌልን በመስበክ ነበር። *በመንፈስ ቅዱስ ተቀድሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት፤* ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት፣ የአሕዛብን ቤተ ክርስቲያን ነበር።

15፥17 *እመካለሁ፤* የጳውሎስ ትምክሕት ራሱ በፈጸመው ነገር ሳይሆን፣ ክርስቶስ በእርሱ ውስጥ ባደረገው ነገር ነበር።

15፥19 *በምልክቶችና በታምራት፤* ሐሥ14፥8-10፤ 16፥16-18፤ 20፥9-12፤ 28፥8-9፤ 2ቆሮ 12፥12፤ ዕብ 2፥3-4 ይመ። *ከኢየሩሳሌም፤* ወንጌል በመጀመሪያ የተሰበከባት፣ መስፋፋትም የጀመረባት የእናት ቤተ ክርስቲያን ከተማ ናት (ሐሥ 1፥8 ይመ)። *እልዋሪቆን፤* ከመቄዶንያ በስተ ሰሜን የሚገኝ የሮማ ግዛት የነበረ ሲሆን፣ አሁን ግን በሁለት ተከፍሎ አልባንያና ዩጎዝላቪያ ተብሎአል። ጳውሎስ በዚህ ሥፍራ ስለ ሰጠው አገልግሎት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ምንም የተጠቀሰ ነገር የለም፤ ምናልባትም እዚህ ላይ የሚናገረው ሁሉ እስከዚያች አገር ድንበር ድረስ መዝለቁን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። *ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ፤* ከሜድትራኒያን በስተ ምሥራቅ ባሉ አገሮች የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ወንጌልን ሰምተዋል ማለት ሳይሆን፣ ጳውሎስ በዚያ አካባቢ የሚሠራውን ሥራ ስለ ጨረሰ፣ ወደ ሌላ ስፍራ መሄድ እንዳለበት ለማሳየት ነው።

እስከ እልዋሪቆን ዙሪያ ድረስ የክርስቶስን
ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ:: 20ሌላው በጣለው
መሠረት ላይ እንዳልገነባ ብዬ፣ ክርስቶስ
ባልተጠራበት ስፍራ ወንጌልን መስበክ የዘወ
ትር ምኞቴ ነበር:: 21ይልቁንም፣

“ስለ እርሱ ያልተነገራቸው ያያሉ፤
ያልሰሙም ያስተውላሉ” ተብሎ
እንደ ተጻፈ ነው::

22በዚህም ምክንያት ወደ እናንተ እንዳል
መጣ ብዙ ጊዜ ተከለከልሁ::

## ሮምን ለመጐብኘት የጳውሎስ ዕቅድ

23አሁን ግን በእነዚህ አካባቢዎች የምሠ
ራው ስለሌለ፣ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ
እናንተን ለማየት እናፍቅም ስለ ነበር፣
24ይህን ዕቅድ ወደ እስጳንያ በምሄድበት
ጊዜ ልፈጽመው አስባለሁ:: በማልፍበትም
ጊዜ ልጐበኛችሁና ከእናንተ ጋር ለጥቂት
ጊዜ ቈይቼ ናፍቆቴን ከተወጣሁ በኋላ በጕ
ዞዬ እንደምትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ:: 25አሁን
ግን በዚያ የሚገኙትን ቅዱሳን ለማገልገል
ወደ ኢየሩሳሌም በመጓዝ ላይ ነኝ:: 26ምክንያ
ቱም መቄዶንያና አካይያ፣ በኢየሩሳሌም
ካሉት ቅዱሳን መካከል የሚገኙትን ድኾች
ለመርዳት ተነሣሥተዋልና:: 27ርዳታ ለማድረግ
ወደዋል፤በእርግጥም ባለ ዕዳዎቻቸው ናቸው::
አሕዛብ የአይሁድ መንፈሳዊ በረከት ተካፋዮች
ከሆኑ፣ ያገኙትን ምድራዊ በረከት ከአይሁድ
ጋር ይካፈሉ ዘንድ የእነርሱ ባለ ዕዳዎች
ናቸው:: 28ስለዚህ ሥራውን ከጨረስሁና
ይህን ፍሬ መቀበላቸውን ካረጋገጥሁ በኋላ
ወደ እስጳንያ እሄዳለሁ፤ እግረ መንገዴንም
እናንተን አያለሁ:: 29ወደ እናንተም ስመጣ፣
በክርስቶስ በረከት ሙላት እንደምመጣ ዐው
ቃለሁ::
30ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እኔ ወደ እግዚአ
ብሔር በመጸለይ የተጋድሎዬ አጋር እንድ
ትሆኑ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመ
ንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ:: 31በይሁዳ
ካሉት ከማያምኑት እጅ እንድድንና በኢ
የሩሳሌም ያለው አገልግሎቴም በዚያ ባሉት
ቅዱሳን ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጸልዩ
ልኝ፤ 32ይኸውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ
እናንተ በደስታ እንድመጣና ከእናንተም
ጋር እንድታደስ ነው:: 33የሰላም አምላክ
ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን::

ሐሥ22፥17-21፤ 19፥11፤2ቆሮ 2፥12
15፥20 ሮሜ1፥15፤ 2ቆሮ10፥15:16
15፥21 ኢሳ52፥15
15፥22 ሮሜ1፥13
15፥23 ሐሥ19፥21፤ ሮሜ1፥10:11
15፥24 ቍ28፤ 1ቆሮ16፥6፤ ቲቶ 3፥13
15፥25 ሐሥ19፥21፤ 24፥17፤9፥13
15፥26 ሐሥ16፥9፤ 18፥12፤24፥17
15፥27 1ቆሮ9፥11
15፥28 ቍ24
15፥29 ሮሜ1፥10:11
15፥30 2ቆሮ1፥11፤ ገላ5፥22፤ቈላ1፥8፤ 4፥12
15፥31 ቍ25፤ ሐሥ 9፥13፤24፥17፤ 2ቆሮ1፥10፤2ተሰ3፥2፤ 2ጢሞ3፥11፤2ጢሞ2፥9፤
15፥32 ሐሥ18፥21፤ ሮሜ1፥10:13፤ 1ቆሮ16፥18፤ፊሞ 7
15፥33 ሮሜ16፥20፤ 2ቆሮ13፥11፤ ፊል4፥9፤1ተሰ5፥23፤ 2ተሰ3፥16፤ዕብ13፥20
16፥1 ሐሥ18፥18፤ 2ቆሮ3፥1፤
16፥2 ሐሥ9፥13፤ ፊል2፥29፤
16፥3 ቍ7:9:10፤ ሐሥ18፥2፤ ሮሜ8፥1:39፤ 1ቆሮ1፥30፤ 2ቆሮ5፥17፤ገላ1፥22፤ 5፥6፤ኤፌ1፥13፤ ፊል 2፥25፤
16፥5 ሐሥ2፥9፤ 1ቆሮ16፥15፤19፤ ቈላ 4፥15፤ፊሞ2፤

## የግል ሰላምታ

16 በክንክራኦስ ቤተ ክርስቲያን አገል
ጋይ[ሀ] የሆነችውን እኅታችንን ፌቤ
ንን ዐደራ እላችኋለሁ:: 2ለቅዱሳን ተገቢ
በሆነው አቀባበል በጌታ እንድትቀበሏትና
ከእናንተም የምትፈልገውን ማንኛውንም
ርዳታ እንድታደርጉላት አሳስባችኋለሁ፤
ለብዙ ሰዎችና ለእኔም ጭምር ታላቅ ድጋፍ
ነበረችና::
3በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚያገለ
ግሉት ለጵርስቅላና[ለ] ለአቂላ ሰላምታ አቅር
ቡልኝ:: 4እነርሱም ለእኔ ሲሉ ሕይወታቸ
ውን ለአደጋ አጋልጠው ሰጡ፤ እኔ ብቻ ሳል
ሆን የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ
ያመሰግኗቸዋል::
5በእነርሱ ቤት ላለች ቤተ ክርስቲያንም
ሰላምታ አቅርቡልኝ::
ከእስያ አገር ለመጀመሪያ ወደ ክርስቶስ
ለተመለሰው፣ ለወዳጄ ለአጤኔጦን ሰላምታ
አቅርቡልኝ::
6ለእናንተ ብዙ ለደከመችው ለማርያ ሰላ
ምታ አቅርቡልኝ::

[ሀ]1 ወይም ዲያቆን
[ለ]3 በግሪኩ ጵርስቃ የጵርስቅላ ተለዋጭ ስም ነው::

15፥22 *ወደ እናንተ እንዳልመጣ ... ተከለከልሁ፤* ጳውሎስ፣ ከሜድትራኒያን በስተ ምሥራቅ ባሉ አገሮች የወንጌል ተልእኮውን ለመፈጸም ከነበረው ከፍተኛ ፍላጎት የተነሣ ጕዞውን ወደ ሮም ማድረግ አልቻለም::

15፥23 *በእነዚህ አካባቢዎች የምሠራው ስለ ሌለኝ፤* ይህም በቍ 20 ላይ በተጠቀሰው ምክንያት ነው:: *ከብዙ ዓመታት ጀምሮ እናንተን ለማየት እናፍቅም ስለ ነበር፤* 1፥11-15 ይመ::

15፥24 *በጕዞዬ እንደምትረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤* ጳውሎስ በእስጳንያ ለነበረበት የወንጌል ተልእኮ፣ ከጊዜያዊ ማረፊያው ከሮም ቤተ ክርስቲያን እየተነሣ ለማገልገል ፈለገ:: *ከእናንተ ጋር ለጥቂት ጊዜ ቈይቼ፤* በሮም ለአጭር ጊዜ መቈየት እንደሚችል ማሰቡን ያሳያል (1፥11-12 ይመ)::

15፥25 *በዚያ የሚገኙትን ቅዱሳን ለማገልገል፤* ጳውሎስ በኢየሩሳሌም ላለችው ቤተ ክርስቲያን የተላከውን ስጦታ (ቍ 26 ይመ) ራሱ ለማቅረብ ፈለገ፤ ስጦታውም መግለጫ መስጠት የሚጠይቅ ነበር፤ ስጦታው ገንዘብ ብቻ ሳይሆን የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት ለአይሁድ ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው ያላቸውን ፍቅርና መተሳሰብ የሚገልጥ ነበር:: *ቅዱሳን፤* በጠቅላላው በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትን ክርስቲያኖች ያመለክታል (የ1፥7 ማብ ይመ)::

15፥26 *ለመርዳት፤* 1ቆሮ 16፥1-4፤ 2ቆሮ 8-9 ይመ::

15፥27 *የአይሁድ መንፈሳዊ በረከት፤* በተለይ ክርስቶስና ወንጌሉ ናቸው::

15፥28 *ይህን ፍሬ፤* ከአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት የተሰበሰበውን ስጦታ ለማለት ነው::

15፥31 *በይሁዳ ካሉት ከማያምኑት ሰዎች እጅ እንድድን ... ጸልዩልኝ፤* ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንደ ፈለገ ያመለክታል፤ የተሰበሰበውን ስጦታ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ቢያገኘውም፣ በዚያ ሊደርስበት ስለሚችል መከራ ማስጠንቀቂያ ደርሶት ነበር (ሐሥ 20-22-23 ይመ):: *ተቀባይነት እንዲያገኝ፤* ይዞ የሄደውን ስጦታ በደስታ እንዲቀበሉት ወይም በኢየሩሳሌም ያለው አጠቃላይ የወንጌል አገልግሎቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሊሆን ይችላል::

15፥32 *ከእናንተም ጋር እንድታደስ፤* 1፥11-12 ይመ::

15፥33 *የሰላም አምላክ፤* የ5፥1 የ1ተሰ 5፥23 ማብ ይመ::

16፥1 *እኅታችንን፤* ክርስቲያን እኅት ከመሆኗ አንጻር ነው:: *ፌቤን፤* ይህን መልእክት ወደ ሮም ያደረሰችው እርሷ ልትሆን ትችላለች:: *አገልጋይ፤* በማንኛውም መንገድ የሚያገለግልን ሰው ሊያመለክት ይችላል፤ እዚህ ላይ እንደ ተጠቀሰው ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጋር በማያያዝ ከታየ፣ የሴት ዲያቆናን የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም:: *ክንክራኦስ፤* ከቆሮንቶስ በስተ ምሥራቅ ዐሥር ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በሳሮኒክ የባሕር ሰላጤ የሚገኝ ወደብ ነው::

16፥3 *ጵርስቅላና አቂላ፤* የጳውሎስ የቅርብ ጓደኞች የነበሩ፣ ባልና ሚስት ናቸው:: *ሥራቸው* እንደ ጳውሎስ ድንኳን መስፋት ነበር (ሐሥ 18፥2-3 ይመ)::

16፥4 *ለእኔ ሲሉ ሕይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠው ሰጡ፤* ከዚህ ውጭ፣ በአዲስ ኪዳን ወይም በሌላ ቦታ ስለዚህ ጕዳይ የተጻፈ ነገር የለም፤ ነገር ግን የጥቅሱ መጨረሻ እንደሚያመለክተው፣ በስፋት የሚታወቅ ነገር መሆን አለበት::

16፥6 *ማርያ፤* በአዲስ ኪዳን በዚህ ስም የሚጠሩ ስድስት ሴቶች አሉ፤ ይህችኛዋ ግን ከዚህ ስፍራ በስተቀር በሌላ ቦታ አልተጠቀሰችም::

7ከእኔ ጋር ታስረው ለነበሩት ዘመዶቼ
ለአንዲራኒቆንና ለዩልያን ሰላምታ አቅርቡ
ልኝ፤ እነርሱ በሐዋርያት መካከል ስመጥሮ
ችና በክርስቶስ በማመንም እኔን የቀደሙ
ናቸው::
8በጌታ ለምወደው ለጵልያጦን ሰላምታ
አቅርቡልኝ::
9በክርስቶስ አብሮን ለሚሠራው ለኢሩባኖ
ንና ለውድ ወዳጄ ለስንጣክን ሰላምታ አቅር
ቡልኝ::
10በክርስቶስ ያለው እምነቱ ተፈትኖ ለተ
መሰገነው ለኤጤሌን ሰላምታ አቅርቡልኝ፤
ከአርስጣባሉ ቤተ ሰብ ለሆኑትም ሰላምታ
አቅርቡልኝ::
11ለዘመዴ ለሄሮድዮና ሰላምታ አቅርቡልኝ፤
በጌታ ላሉት ለንርቀሱ ቤተ ሰቦች ሰላምታ
አቅርቡልኝ::
12በጌታ ሆነው በትጋት ለሚሠሩት ሴቶች፣
ለፕሮፊሞናና ለጢሮፊሞሳ ሰላምታ አቅርቡልኝ::
በጌታ ሆና እጅግ ለደከመችው ለሌላዋ
ሴት፣ ለተወደደችው ለጠርሲዳ ሰላምታ አቅ
ርቡልኝ::
13በጌታ ለተመረጠው ለሩፎንና የእኔም
እናት ለሆነችው ለእናቱ ሰላምታ አቅርቡልኝ::
14ለአስቀሬጦንና ለአፍለሶንጳ፣ ለሄሮሜን፣
ለጳጥሮባን፣ ለሄርማን፣ ከእነርሱም ጋር ላሉት
ወንድሞች ሰላምታ አቅርቡልኝ::
15ለፍሊጎን፣ ለዩልያ፣ ለኔርያና ለእኅቱ፣
እንዲሁም ለኦልንጦን፣ ከእነርሱም ጋር ላሉት
ቅዱሳን ሰላምታ አቅርቡልኝ::
16በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ:: የክ
ርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ

16፥7 ቍ3፥11:21፡ ቈላ4፥10፤ፊሞ23፤
16፥9 ቍ3
16፥10 ቍ3፤ ሐሥ11፥14
16፥11 ቍ7:21፤ ሐሥ11፥14
16፥13 ማር15፥21፤ 2ዮሐ1
16፥15 ቍ2፥14፤ ሐሥ9፥13፤
16፥16 1ቆሮ16፥20፤ 2ቆሮ13፥12፤ 1ተሰ5፥26፤1ጴጥ5፥14
16፥17 ማቴ18፥15-17፤ ገላ1፥8:9፤1ቆሮ5፥11፤ 2ተሰ3፥6:14፤ 1ጢሞ 1፥3፤6፥3፤ 2ጢሞ3፥5፤ቲቶ3፥10፤ 2ዮሐ10
16፥18 2ሳሙ15፥6፤ መዝ12፥2፤ኢሳ30፥10፤ ሮሜ14፥18፤ ፊል3፥19፤ቈላ2፥4
16፥19 ሮሜ1፥8፤ 1ቆሮ14፥20
16፥20 ዘፍ3፥15፤ ማቴ4፥10፤ ሮሜ15፥33፤ 2ቆሮ13፥14፤ ገላ6፥18፤1ተሰ5፥28፤ ራእ22፥21
16፥21 ቍ7፥11፤ ሐሥ16፥1፤13፥1፤ 17፥5፤
16፥23 ሐሥ19፥22: 29፤2ጢሞ4፥20
16፥25 ኢሳ48፥6፤ ሮሜ2፥16፤2ቆሮ9፥8፤ ኤፌ1፥9፤3፥20፤ ቈላ1፥26:27፤2፥2፤ 1ጢሞ3፥16፤ 2ጢሞ2፥8፤3፥3-6:9፤

ያቀርቡላችኋል::
17ወንድሞች ሆይ፤ መለያየትን ከሚፈ
ጥሩትና የተማራችሁትን ትምህርት በመቃ
ወም በጕዞአችሁ መሰናክል ከሚያደርጉት
እንድትጠነቀቁ አሳስባችኋለሁ፤ ከእነርሱም
ራቁ:: 18እንደ እነዚህ ያሉት ሰዎች የሚያገ
ለግሉት ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይ
ሆን፣ የራሳቸውን ሆድ ነው፤ በለሰለሰ አንደ
በታቸውና በሽንገላ፣ የዋሆችን ያታልላሉ::
19የእናንተን ታዛዥነት ሁሉም ሰምተዋል፤
በዚህም እኔ እጅግ ተደስቻለሁ:: ሆኖም በጎ
ስለ ሆነው ነገር ጥበበኞች፣ ክፉ ስለ ሆነውም
የዋሆች እንድትሆኑ እፈልጋለሁ::
20የሰላም አምላክ፣ ሰይጣንን ከእግራችሁ
በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል::
የጌታችን የኢየሱስ ጸጋ ከእናንተ ጋር
ይሁን::
21አብሮኝ የሚሠራው ጢሞቴዎስ፣ እንዲ
ሁም ዘመዶቼ የሆኑት ሉቂዮስ፣ ኢያሶንና
ሱሲጴጥሮስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል::
22ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥ
ዮስ፣ በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ::
23በመልካም መስተንግዶው እኔና በዚህ
የምትገኘዋ መላዋ ቤተ ክርስቲያን ደስ የም
ንሰኝበት ጋይዮስ፣ ሰላምታ ያቀርብላችኋል::
የከተማዪቱ ግምጃ ቤት ሹም የሆነው ኤር
ስጦስ፣ ወንድማችንም ቍአስጥሮስ ሰላምታ
ያቀርቡላችኋል:: 24የጌታችን የኢየሱስ ክር
ስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን::*
25በዘላለማዊ አምላክ ትእዛዝ ሕዝቦች ሁሉ
አምነው እንዲታዘዙ፣ በነቢያት መጻሕፍት

*24 ቍጥር 24 የሚገኘው በአንዳንድ ቅጆዎች ብቻ ነው::

16፥7 *ዩልያን፤* የሴት ስም ነው:: *በሐዋርያት መካከል፤* ሐዋርያት ሲባል ሁለት ትርጕሞች አሉ:: 1) "ሐዋርያት" የሚለው ቃል በዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ብቻ ሳይወሰን፣ በአብያተ ክርስቲያናት ደረጃ የታወቁ የወንጌል ሰባኪዎችንም የሚያካትት ሊሆን ይችላል:: (የሐሥ 14፥4:14፤ 1ተሰ 2፥6 ይመ)፤ 2) "ሐዋርያት" የሚለው ቃል በአገባቡ ዐሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ብቻ የሚያመለክት ሆኖ ሊቀርብ ይችላል:: በዚህ ቦታ ትርጕሙ እነዚህ ሁለቱ ሰዎች "በሐዋርያት ዘንድ" በሚገባ የታወቁ ነበሩ ለማለት ነው::

16፥8-10 *ጵልያጦን ... ኢሩባኖን ... ስንጣክን... ኤጤሌን፤* እነዚህ ሁሉ የቤተ መንግሥት ባሮች የሚጠሩባቸው ስሞች ነበሩ::

16፥10 *ከአርስጣባሉ፤* ምናልባት የታላቁ ሄሮድስ የልጅ ልጅ እንዲሁም የቀዳማዊው ሄሮድስ አግሪጳ ወንድም ሊሆን ይችላል::

16፥11 *ለዘመዴ፤* ምናልባት አይሁዳዊ ከመሆኑ አንጻር ሊሆን ይችላል:: *ለንርቀሱ፤* ከሮሙ ንጉሠ ነገሥት ከጢባርዮስ ባርነት ነጻ ወጥቶ ሀብታም የሆነው ጢባርዮስ ቀላውዴዎስ ንርቀሱ ነው የሚሉ አሉ::

16፥12 *ፕሮፊሞናና ጢሮፊሞሳ፤* መንትዮችን፣ ግንዱ አንድ ዐይነት በሆነ ስም መጥራት የተለመደ ስለ ነበር፣ ምናልባት እነዚህም ሁለት እኅትማማቾች መንትዮች ሊሆኑ ይችላሉ:: *ለጠርሲዳ፤* ትርጕሙ "የፋርስ ሴት" ማለት ነው::

*16፥14-15፤* በዚህ ክፍል፣ የተጠቀሱት ሰዎች በሮም ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ባሮች ወይም ከባርነት ነፃ የወጡ ሰዎች ከመሆናቸው በስተቀር ስለ እነዚህ ሰዎች የሚታወቅ ነገር የለም::

16፥16 *በተቀደሰ አሳሳም፤* 1ቆሮ 16፥20፤ 2ቆሮ 13፥12፤ 1ተሰ 5፥26፤ 1ጴጥ 5፥14 ይመ:: በ150 ዓ.ም. ይኖር የነበረው ዮስጢን ማርቲር የተባለ ሰው፣ የተቀደሰ አሳሳም በእርሱ ዘመን የአምልኮ አንዱ ክፍል እንደ ነበረ ይነግረናል፤ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አሁንም የተለመደ ነው::

*16፥17-20፤* በዘፍ 3 የተነገረው የሰው ውድቀት ታሪክ በትምህርተ መለኮት መልክ ለቤተ ክርስቲያን ቀርቦአል::

16፥17 *መለያየትን ከሚፈጥሩትና ... በጕዞአችሁ መሰናክል ከሚያደርጉት፤* እነዚህ ሰዎች እነማን እንደ ነበሩ ለይቶ መናገር ያስቸግራል፤ ነገር ግን አንዳንድ ባሕርያቸው በቍ 18 ላይ ተገልጾአል::

16፥19 *በጎ ስለ ሆነው ነገር ጥበበኞች፤* ለክርስቲያኖች በጎ ነገር ማድረግ ልማዳቸው ሊሆን ይችላል::

16፥20 *የሰላም አምላክ፤* 15፥33 ይመ:: *ሰይጣንን ... ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል፤* በሰይጣን ላይ የሚደርሰውን የመጨረሻ ፍርድ ያመለክታል (ከዘፍ 3፥15 ጋር ያነጻጽሩ)፤ "ፈጥኖ" ለሚለው ቃል የ 13፥12 ማብ ይመ::

16፥21 *ኢያሶን፤* ምናልባት በሐሥ 17፥5-9 የተጠቀሰው ኢያሶን ሊሆን ይችላል:: *ሱሲጴጥሮስ፤* ምናልባት የጲረስ ልጅ፣ የቤርያው ሱሲ ጴጥሮስ ሊሆን ይችላል::

16፥22 *ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥዮስ፤* የጳውሎስ ጸሓፊ ሆኖ ይሠራ የነበረ ሰው ሲሆን፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከዚህ ውጭ በሌላ ስፍራ አልተጠቀሰም::

16፥23 *ጋይዮስ፤* ቆሮንቶስ በነበረበት ጊዜ ጳውሎስን በቤቱ እንዲያርፍ ያደረገው፣ እግዚአብሔርን የሚፈራው ቲቶስ ኢዮስጦስ እንደ ሆነ የሚናገሩ አሉ (ሐሥ 18፥7፤ 1ቆሮ 1፥14 ይመ)፤ ሙሉ ስሙም ጋይዮስ ቲቶስ ኢዮስጦስ ይሆናል:: *በዚህ፤* በቆሮንቶስ ማለት ነው:: *ኤርስጦስ፤* የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች ባደረጉት ቍፋሮ የሕዝብ ጕዳይ ኀላፊ የሆነው ኤርስጦስ፣ ለዚህ መንገድ ንጣፍ የወጣውን ወጪ ሸፍኖአል የሚል በላቲን የተጻፈ አራት ማእዘን ጥርብ ድንጋይ በቆሮንቶስ አግኝተዋል:: ይህም ምናልባት በዚህ ስፍራ የተጠቀሰውን ኤርስጦስን፣ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል፤ ስሙ የተለመደ ስለ ነበር፣ እርግጠኛ መሆን ቢያስቸግርም በሐሥ 19፥22 እና በ2ጢሞ 4፥20፣ የተጠቀሰው ይህ ሰው ሊሆን ይችላል:: *ቍአስጥሮስ፤* ትርጕሙ "አራተኛ ልጅ" ማለት ነው::

16፥25 *ወንጌልና፤* ሌሎች ከሰበኩት ወንጌል የተለየ ነው ለማለት ሳይሆን፣ ጳውሎስ ቀጥታ በመገለጥ የተቀበለው መሆኑን ለማመልከት ነው (ገላ 1፥12 ይመ)፣ *በኢየሱስ ክርስቶስ መሰበክ፤* ለወንጌል የተሰጠ አገላለጽ ሲሆን፣ በውስጡ የተጻፈው ሁሉ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: *ምስጢር፤* የ11፥25 ማብ ይመ:: *ረጅም ዘመናት፤* ከዘላለም ዘመናት ጀምሮ ማለት ነው (1ቆሮ 2፥6-10 ይመ)::

አሁን በተገለጠው፣ 26ላለፉት ረጅም ዘመናት
ተሰውሮ በነበረው ምስጢር መገለጥ መሠ
ረት፣ በአስተማርኩት ወንጌልና በኢየሱስ
ክርስቶስ መሰበክ ሊያጸናችሁ ለሚችለው፣

ይሁ 24፤
16፥26 ሮሜ 1፥2፡5
16፥27 ሮሜ 11፥36

27እርሱ ብቻ ጥበበኛ ለሆነ አምላክ፣ በኢየሱስ
ክርስቶስ በኩል ለዘላለም ክብር ይሁን፤
አሜን።

16፥26 *በነቢያት መጻሕፍት አሁን በተገለጠው፤* 1፥2 ይመ። *ሕዝቦች ሁሉ፤* ወንጌል ለሁሉም ሕዝብ እንደ ሆነ ያሳያል (ማቴ 28፥19 ይመ)።

16፥27 *ለ … አምላክ … ክብር ይሁን፤* የሁሉም ነገር የመጨረሻ ዐላማ ይህ ነው።